ከመምህርነት እስከ ግዙፉ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ባለቤትነት
ገጽ 10

ነፍሰ ገዳዩ ደፋሪ
ገጽ 11

የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ እምርታ - በሶማሌ ክልል
ገጽ 18

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 278 ሰኔ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የሕግ ማዕቀፉን በማሻሻል ተቀባይነት ያለውና ሰላማዊ ምርጫ ለማካሄድ እየተሠራ ነው

ፎቶ፡ ዳኜ አበራ



ወይዘሮ ሜላተወርቅ ኃይሉ

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የሕግ ማዕቀፉን በማሻሻል ተቀባይነት ያለው፣ ውጤታማና ሰላማዊ ምርጫ ለማካሄድ እየተሠራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስታወቀ።

ቦርዱ በቀጣይ የሚደረጉ ምርጫዎችን ፍትሐዊ፣ ግልጽ፣ ነጻና ተዓማኒ ለማድረግ የሚረዳ የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ትናንት ይፋ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ወይዘሮ ሜላተወርቅ ኃይሉ እንደገለጹት፤ የሕግ ማዕቀፉን ማሻሻል ለቦርዱ ከተሰጡት ዋና ዋና ኃላፊነቶች አንዱ ነው።

ላለፉት አምስት ዓመታት ሲሠራበት በቆየው የሕግ ማዕቀፉ ያሉትን ክፍተቶች በመለየት የቦርዱን ተቋማዊ ጥንካሬ የሚያስቀጥል፣ ተቀባይነት ያለውና ሰላማዊ ምርጫን ማካሄድ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንደሚዘረጋ አስታውቀዋል።

በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ለውጤታማና ሰላማዊ ምርጫ መሠረት መሆኑን ገልጸው፤ የሕግ ማዕቀፉን ለሁሉም መራጮችና የምርጫ ባለድርሻዎች ተደራሽና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ አሁን ያሉትን የምርጫ ሕግ ማዕቀፎች ለማሻሻል ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ሜላተወርቅ ገለጻ፣ ስለ ምርጫው የሕግ ማዕቀፍና በሕጉ ላይ ስለሚደረጉ ማንኛውም ለውጦች ለዜጎች በግልጽ የማሳወቅ ሥራ ይሠራል። በለውጡ ሂደትም ሕዝቡ ግብዓት እንዲሰጥ እድል በመፍጠር የምርጫ ሕጎችም ሆነ ሕጎቹ በሥራ ላይ ሲውሉ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ

የሕግ ማዕቀፉን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ቋሚ ኮሚቴው የመለኪያ መሳሪያዎች ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ለዳግም እይታ መራ

**ታደሠ ብናልፈው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የመለኪያ አሀዶች የመቆጣጠሪያና የማመሳከሪያ መለኪያ መሳሪያዎችን አጠቃቀምና ተዓማኒነት የሚያረጋግጠው ሕጋዊ ሥነ-ልክ ረቂቅ አዋጅ መካተት ያለባቸውን ግብአት አሟልቶ እንዲቀርብ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ፡፡

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የተዘጋጀው የመለኪያ አሀዶች የመቆጣጠሪያና የማመሳከሪያ መለኪያ መሳሪያዎች አጠቃቀምና ተዓማኒነትን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ሥነ-ልክ ረቂቅ አዋጅ በትናንትናው ዕለት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ለባለድርሻ አካላት ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡

በውይይቱ የታደሙት ባለድርሻ አካላት የረቂቅ አዋጁን ይዘት፣ አተገባበርና ጠቀሜታ በጥልቀት መርምረው ከሌሎች የቁጥጥር

ቋሚ ኮሚቴው ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ጥራት ችግሮችን ለመፍታት የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ነድፎ እየሠራ ነው

**ዘላለም ግዛው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ከትምህርት ጥራት ችግር ለመውጣት የሚያግዝና መፍትሔ የሚያመለክት የአምስት ዓመታት ስትራቴጂክ እቅድ ቀርጾ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡ በትምህርት ጥራት ለደረሰው ችግር መፍትሔ ማመንጨት እና ስብራቱን ማከም የሚቻለው የዘርፉ ምሁራን በጋራ ሲመካከሩ እና ሲወያዩ መሆኑንም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ገልጸዋል፡፡

የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ያዘጋጀውና ዛሬ በሚጠናቀቀው ሁለተኛው ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ፕሬዚዳንቱ ብርሃነ መስቀል(ዶ/ር)፤ መምህራንና የዘርፉ

ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ብርሃነ መስቀል(ዶ/ር)



# በዞኑ ሰላም በመስፈኑ ውጤታማ የልማት ሥራዎች እየተካሄዱ ነው

**በኃይሉ አበራ**

<u>መንዲ</u>፡- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን አንጻራዊ ሰላም በመስፈኑ ውጤታማ የልማት ሥራዎች እየተካሄዱ ነው ሲሉ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሰለሞን ታምሩ ተናገሩ።

አቶ ሰለሞን ታምሩ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በምዕራብ ወለጋ ዞን አንጻራዊ ሰላም በመስፈኑ ሕዝቡ ፊቱን ወደ ልማት በማዞር እንደ አቮካዶ፣ በቆሎና ሙዝ የመሳሰሉትን ፍራፍሬዎችና ሰብሎች በክላስተር እያለሙ ነው።

በዞኑ ሰላም ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





# የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 35ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው መንግሥት ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር የ2ኛ ዙር የከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው።

ብድሩ የዘርፉን የማስፈጸም አቅም ለማጠናከር የሚውል ሲሆን፤ ወለድ የማይታሰብበት፣ ዜሮ ነጥብ 75 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልበት ሆኖ ስድስት ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ38 ዓመት ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑ ተመላክቷል።

ምክር ቤቱ ብድሩ ከሀገራችን የብድር አስተዳደር ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ረቂቅ አዋጁ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በተጨማሪም የንብረት ታክስ ረቂቅ አዋጅ ላይ ውይይት ያካሄደ ሲሆን፤ የንብረት ታክስ በከተማ ነዋሪው ሕዝብ መካከል ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ለማስፈን እንደሚያስችል ተጠቁሟል፡፡

አዋጁ በሀገሪቱ በሚገኙ ከተሞች ውስጥ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው የተገለጸ ሲሆን፤ ክልሎችም አዋጁን መሠረት አድርገው የየራሳቸውን የንብረት ታክስ ሕግ እንዲያወጡ ያስችላል ተብሏል።

ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በቀጣይነት ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሪፎርምና የካፒታል ማሳደጊያ ዕቅድ ላይ ነው፡፡ የባንኩን የሀብት ጥራት ለማሻሻልና በአስተማማኝ መልኩ የካፒታል መጠኑን በማሳደግ ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ዘላቂነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ የውሳኔ ሃሳቦች ለምክር ቤቱ ቀርበዋል፡፡

የባንኩን አስተዳደራዊ ውጤታማነት ማጎልበት፤ የሂሳብ መግለጫዎቹን ጠንካራና ተቀባይነት ባለው መልኩ እንዲዋቀር ማድረግና የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ የሚረዳ የመንግሥት የፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል መሆናቸው ተመላክቷል። ምክር ቤቱ በማሻሻያ እቅዱ ላይ ተወያይቶ ወደ ተግባር እንዲገባ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ሌላኛው ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን፤ በሥራ ላይ የቆየው አዋጅ ሁሉንም የልማት ተዋናዮች ያሳተፈ የብልጽግና ዕቅድ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ፣ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮና መርሆዎች አንጻር፣ ከገንዘብ ፖሊሲ ውጤታማነት እንዲሁም በፋይናንስ ራስን ከመቻል አንጻር ክፍተቶች እንዳሉበት ተጠቁሟል።

ባለፉት ዓመታት በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ የኢኮኖሚ፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የጂኦ-ፖለቲካ ለውጦች በመኖራቸው፤ የባንኩን ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት የማስፈን፣ ዋጋን የማረጋጋት እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ የማድረግ ተልዕኮ ለማሳካት ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ተወያይቶ ግብአቶች ታክለው ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ስለባንክ ሥራ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት በርካታ የኢኮኖሚ፣ የቴክኖሎጂ፣ የአደረጃጀት፣ የአሠራርና የመንግሥት ፖሊሲ ለውጦች በመኖራቸው፤ ሀገራችን ለረጅም ጊዜ ዝግ አድርጋው የነበረውን የባንክ ሥራን ለውጭ ሀገራት ክፍት ማድረጓን ተከትሎ ይህንን ለመምራት፣ የፍቃድ አሰጣጥን ለመወሰን እና ለማስተዳደር የሚያስችል የሕግ እና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጁ መዘጋጀቱ ተመላክቷል።

ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ግብአቶች ታክለውበት ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በመጨረሻም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን፤ የልማት ፕሮጀክቶች ከመተግበራቸው በፊት ተጽእኖዎቹን አስቀድሞ በመተንበይ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥር አሠራርን በተቀናጀ መልኩ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ወጥ የሆነ ሀገራዊ የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

# በክልሉ ከ1 ሺህ 180 በላይ
## ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢንቨስትመንት ተሸጋግረዋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ ባለፉት 10 ወራት ከአንድ ሺህ 180 በላይ ኢንተርፕራይዞች ወደተሻለ ኢንቨስትመንት መሸጋገራቸውን የኦሮሚያ ሥራ እድል ፈጠራና ክህሎት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው ኃላፊ ኤባ ገርባ (ኢ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሸጋገሩና ምርቶቻቸውን በስፋት እንዲያቀርቡ እየሠራ ነው፤ ባለፉት 10 ወራት አንድ ሺህ 182 ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

ኢንተርፕራይዞች አቅማቸውን በማሳደግ የተለያዩ ምርቶችን ወደማዘጋጀት መሸጋገራቸውን ጠቁመው፤ በኢንዱስትሪ፣ በግብርና ማቀነባበሪያዎች፣ በአገልግሎትና በተለያዩ ዘርፎች እራሳቸውን በማሳደግ ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በክልሉ በሚገኙ ወጣቶችና ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ከውጭ የሚገቡ በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ማዘጋጀት ተችሏል ብለዋል።

ቢሮው በየጊዜው ለሚሠሩ ቴክኖሎጂዎች የሙከራ መድረክ በማዘጋጀት ውጤታማነታቸው የሚለካ ሲሆን፤ በቀን እስከ ሰባት ኩንታል የሻይ ቅጠል ቆርጦ አድርቆ የሚያዘጋጅ ማሽን፣ የሩዝ ምርትን ሰብስቦ የሚያዘጋጅ ማሽን እንዲሁም ሌሎች ቴክኖሎጂዎች ሳይት ላይ ፍተሻ መደረጉን አንስተዋል፡፡

በክልሉ በቴክኖሎጂ ላይ የሚሠሩ ወጣቶችና ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍና የማብቃት ሥራ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ የተመረጡና ውጤታማ የሆኑት ቴክኖሎጂዎች ለሙከራ ለተለያዩ አካላት በማስተላለፍ ኅብረተሰቡ እየተጠቀመበት መሆኑን አስረድተዋል።

ቴክኖሎጂዎቹ ከተሠሩ በኋላ አስፈላጊነታቸው ተረጋግጦም ወደ ማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግና ጥቅም ላይ ለማዋል ከፍተኛ ክፍተት መኖሩን ገልጸዋል፡፡ በመፍትሔነት የቴክኖሎጂ ፈጣሪዎችና ኢንተርፕራይዞች ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ ኢንተርፕራይዞች አባዝተው ለኅብረተሰቡ ተደራሽ የሚያደርጉበት መንገድ መፈጠሩን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ለሥራ ፈጣሪዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት የቢዝነስ ሃሳብ ይዘው ለገበያው ፍላጎት መልስ እንዲሰጡ ታሳቢ ተደርጎ መሠራቱን አስረድተዋል። በቀጣይም በኢንቨስትመንት ቦርድ የተወሰነላቸውን መሬት ተረክበው ወደ ምርት እንደሚገቡ አብራርተዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ቴክኖሎጂዎች የውጭ ምንዛሬ እጥረትን የሚቀንሱ እንዲሁም ማህበረሰቡን ከአላስፈላጊ ወጪ የሚታደጉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ኅብረተሰቡ ለሀገር ውስጥ ምርት ያልተገባ አመለካከት መኖሩና ይህም አምራቾች ሥራቸውን እንዳያስፋፉ እንቅፋት እንደሆነባቸው አንስተዋል።

ቴክኖሎጂዎቹ ከውጭ ከሚገቡት የተሻሉ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ማህበረሰቡ የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም አኩሪ መሆኑን በመገንዘብ አምራቾችን እንዲያበረታታ ኢንጂነር ኤባ ጥሪ አቅርበዋል።




# ስልጠናው ለኢትዮጵያ የዲጂታል
## ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል

**አመስወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘርፍ ለተማሪዎች የተሰጠው ስልጠና ለኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ስኬት ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥር ተገለጸ።

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግና ሒሳብ ትምህርቶች ላይ የሚሠራው ስቲም ፓወር በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘርፍ በዘጠኝ የስልጠና አይነቶች በበይነ መረብ ለሶስት ወራት ያሰለጠናቸውን 741 ሴት ተማሪዎች ትናንት አስመርቋል፡፡

በኢትዮጵያ የስቲም ፓወር ዋና ዳይሬክተር ስሜነው ቀስቅስ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቀርጻ በዘርፉ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነች ነው።

ተማሪዎቹ ያገኙት ስልጠና ሀገሪቱ በቴክኖሎጂ ዘርፍ እያከናወነች ባለው መርሀ ግብር የራሳቸውን ሚና እንዲጫወቱ ዕድል ይፈጥራል ሲሉም አስረድተዋል፡፡

ሰልጣኞቹ በድረ ገጽ ግንባታ፣ የሞባይል መተግበሪያዎችን በማልማት እና በተለያዩ የቴክኖሎጂ ዘርፎች መሰማራት የሚያስችላቸውን ክህሎት ማግኘታቸውን ጠቁመዋል።

በሳይበር ደህንነት የሰለጠኑ ተማሪዎች የራሳቸውን የመረጃ ደህንነት ከማስጠበቅ አልፈው፤ ሀገሪቱ ላይ የሚቃጡ የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን በመከላከል ረገድ የራሳቸውን ሚና መጫወት እንደሚችሉ አመላክተዋል።

ዶክተር ስሜነው እንደተናገሩት፤ ተማሪዎቹ በሰለጠኑባቸው ዘርፎች ዓለም አቀፍ የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።

በስልጠናው አማካኝነት ባሉበት ሆነው በተለያዩ ሀገራት የሚዘጋጁ የበይነ መረብ ሥራዎች ላይ መሳተፍ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሥራ ዕድል መፍጠር ይችላሉ ብለዋል።

ስልጠናው በቀጣይም የሚሰጥ መሆኑን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በመጀመሪያው ዙር አቅምን ባገናዘበ መልኩ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚማሩና የሚሠሩ ሴት ተማሪዎችን አወዳድሮ ማሰልጠን እንደተቻለ አስረድተዋል።

የስልጠና ፕሮጀክቱ ኃላፊ አቶ አቤል ተፈራ በበኩላቸው፤ ስልጠናው በፕሮጀክት አስተዳደር፣ ድረገፅ ልማት፣ በሳይበር ደህንነት፣ ዲጂታል ማርኬቲንግ፣ ዳታ ትንታኔ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና በሌሎች የትምህርት አይነቶች መሰጠቱን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ስልጠናው የሥራ ዝግጁነትና ሌሎች አስፈላጊ የኮምፒውተር ክህሎቶችን ያካተተ መሆኑን አስረድተዋል።

ሰሞኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ባቀረበው የ100 እቅድ ከ600 በላይ የመንግሥት ድርጅቶች የኦንላይን አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን አስታውቋል፡፡ ለአገልግሎቱ በርካታ ወጣቶች ሰልጥነው ወደሥራ ገብተዋል።

# በ11 ወራት ከ312 ሺህ በላይ ዩኒት ደም ተሰበሰበ

**አመለወርቅ ከበደ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በ2016 በጀት ዓመት 11 ወራት ከ312 ሺህ በላይ ዩኒት ደም መሰብሰብ እንደተቻለ የኢትዮጵያ ደምና ህብረህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ።

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር አሸናፊ ታዘበው (ዶ/ር) ሰሞኑን እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በሚገኙ 43 የደም ባንኮች በ11 ወራት ውስጥ ከ312 ሺህ በላይ ዩኒት ደም ተሰብስቧል። ይህም የእቅዱ 84 በመቶ ነው፡፡

በመደበኛነት ደም የሚለግሱ ግለሰቦች ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጠውን የአንድ በመቶ መስፈርት ለማሟላት ብዙ ሥራ ይጠበቃል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዶክተር አሸናፊ እንዳሉት፤ጥራቱ የተጠበቀ የደም አቅርቦት የበርካታ እናቶች ፣ ሕፃናት እና የወጣቶችን ህይወት ያድናል። በዚህም ተቋሙ በቋሚነት ደም የሚለግሱ ግለሰቦችን የማበረታታትና ጤንነቱ የተጠበቀ የደም አቅርቦት እንዲኖር እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የዘንድሮው የዓለም የደም ለጋሾች ቀን ከሰኔ ሰባት እስከ 22 ቀን 2016 ዓ.ም በተለያዩ መርሀ ግብሮች እንደሚከበር የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለቋሚ ደም ለጋሾ የማበረታቻ ዝግጅት መደረጉንና ጤንነቱ ስለተጠበቀ የደም አቅርቦትና አስፈላጊነት ለማህበረሰቡ ግንዛቤ እየተሰጠ መሆኑን አንስተዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳመላከቱት፤ በክልሎች ወደሚገኙ የደም ባንኮች በመንቀሳቀስ ታዋቂ ሰዎች የሚሳተፉበት የግንዛቤ ማስጨበጫ የንቅናቄ መድረኮች፣ የፓናል ውይይትና የባለሙያ ገለጻዎች እየተደረጉ ነው።

በክረምት ወቅት ደም የማሰባሰብ መርሀ ግብር ከኢትዮጵያ ወጣት የደም ለጋሾች ማህበር ጋር በመሆን ሰኔ አንድ መጀመሩን አስታውሰው፤ የተለያዩ ግለሰቦችም ደም በመለገስ ተሳትፏቸውን እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



አሸናፊ ታዘበው (ዶ/ር)



አርቲስት ይገረም ደጀኔ

የአገልግሎቱ አምባሳደር የሆነው አርቲስት ይገረም ደጀኔ በበኩሉ እንደተናገረው፤ ከደም ልገሳ ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ አለ። ነገር ግን ደም መለገስ ብዙ ጊዜ የማይፈጅና የጤና ጉዳት የማያደርስ በጎ ተግባር መሆኑን ይበልጥ ማስረዳት ይገባል ብሏል።

በርካታ ሰዎች በደም እጦት ሕይወታቸው ያልፋል ያለው አርቲስት ይገረም፤ አንድ ሰው በተወሰኑ ደቂቃዎች ልዩነት ደም ለግሶ ወደ ሥራው መመለስና የሰውን ሕይወት ማዳን ይችላል ሲል ተናግሯል።

የግንዛቤ ፈጠራው መጠናከር እንዳለበት ጠቁሞ፤ ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገ ቅስቀሳ በአንድ ቀን 14 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰቡን አስታውሷል። ደም መለገስ ጊዜ ጠብቆ የሚደረግ ተግባር መሆን እንደሌለበት ገልጿል።

ማህበረሰቡ በቋሚነት ደም የመለገስ ልምድ ሊያዳብር እንደሚገባ አንስቶ፤ አርቲስቱ ደም ከመለገስ ባለፈ ሕይወቱ ሲያልፍ የዓይን ብሌኑን ለመለገስ ቃል ገብቷል።

በኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የደም ለጋሾች ቀን ለ20ኛ ጊዜ እየተከበረ ይገኛል።

# መድኃኒቶች በጀርሞች በመለመዳቸው በዓለም በየዓመቱ አምስት ሚሊዮን ሰዎች ይሞታሉ

**መዓዛ ማሞ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች በመለመዳቸው የተነሳ በዓለም ላይ በየዓመቱ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች እንደሚሞቱ የጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

12ኛው ሀገር አቀፍ የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቀን "የፀረ-ተህዋስያን በጀርሞች መለመድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነትን ማጠናከር" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተከብሯል።

በመርሀ ግብሩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የጤና ሚኒስቴር ተወካይ አቶ ረጋሳ ባይሳ እንደገለጹት፤ የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ በሰውና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተለ የሚገኝ ዓለም አቀፍ ችግር ነው።

በችግሩ ምክንያት በዓለም ላይ በየዓመቱ ወደ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ምክንያቶች እንደሚሞቱ የጠቆሙት አቶ ረጋሳ፤ ችግሩን ለመቀነስ አስፈላጊው ርምጃ ካልተወሰደ እ.አ.አ. በ2050 የሟቾች ቁጥር ወደ 10 ሚሊዮን እንደሚያሻቅብ ይገመታል ሲሉ አመላክተዋል።

ችግሩ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ እስከ 3 በመቶ ወይም 10 ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ እንደሚያስከትል ገልጸው፤ በታዳጊ ሀገሮችም ከ5 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ ኪሳራ እንደሚያደርስ አንስተዋል።

የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች ከበሽታው ጋር ከተላመዱ የማዳን አቅም እንደማይኖራቸው አስረድተው፤ ችግሩን ለመቅረፍ ኅብረተሰቡ የታዘዘለትን መድኃኒት በታዘዘው መጠንና ጊዜ በመውሰድ እንዳለበት ገልጸዋል። መድኃኒት አቅራቢ ድርጅቶችም መድኃኒቶቹን ሲያጓጉዙና ሲያከማቹ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት በመሥራት በመድኃኒቶች ውጤታማነት ላይ መሥራት እንዳለባቸው የተናገሩት አቶ ረጋሳ፤ መላው ዜጋ መድኃኒቶችን በጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ ብቻ መጠቀም እንዳለበት አሳስበዋል።

የዓለም የጤና ድርጅት፣ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት፣ የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ድርጅት ችግሩን ለመቅረፍ የሚረዳ የመከላከያና መቆጣጠሪያ ስትራቴጂክ እቅድ አውጥተው አባል ሀገራት እንዲተገብሩት ጥረት እያደረጉ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያም የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍ ሀገራዊና ክልላዊ አማካሪ ኮሚቴ እንዲሁም ቴክኒካል ቡድን በማዋቀር ባለፉት ዓመታት በርካታ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች መሥራቷን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ተወካይ የሆኑት ወይዘሮ አስናቀች አለሙ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚሸጡ መድኃኒቶችን ለማስቀረት የሚረዳ አሠራር ተግባራዊ ተደርጓል። በቀጣይ የቁጥጥር ሥራዎች ከክልሎች ጋር በመሆን ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

የግንዛቤ ማስጨበጫ ቀኑን የጤና ሚኒስቴር፣ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣንና የግብርና ሚኒስቴር ከአጋር አካላት ጋር በጋራ አዘጋጅተውታል።

# ወረዳው የዘንድሮውን የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለማከናወን ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቋል

**ስምስም መንግሥቱ**

<u>ጊምቦ ወረዳ</u>:- በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፋ ዞን ጊምቦ ወረዳ ስድስተኛውን ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለመጀመር ዝግጅት ማጠናቀቁን አስታወቀ::

በክረምቱ ለሚከናወነው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር እየተደረገ ያለውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ ለማየት በሥፍራው ለተገኘው የጋዜጠኞች ቡድን የወረዳው አካባቢ ጥበቃና ኅብረት ሥራ ጽህፈት ቤት የተፈጥሮ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ተሾመ ሽባባው እንደገለጹት፤ በወረዳው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርን በሦስት ዙሮች እቅድ ተይዞ ሲሠራ የቆየ ሲሆን፤ በዚሁ መሠረትም በበጋ የተለያየ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኙ የፍራፍሬ ልማት ሥራዎችና በአንድ ጀንበር ከ300ሺ በላይ የተለያዩ የዛፍ ችግኞች ተከላ መርሀ ግብር ነው::

በሦስተኛው ዙር ደግሞ በክረምት ወይንም በመኸር እየተደረገ ለሚከናወነው መርሀ ግብር የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል::




በአጠቃላይ ዘርፈብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ ለሚከናወነው የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር በወረዳው ከአራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል በእቅድ መያዙን የጠቆሙት አቶ ተሾመ፤ ከእቅዱ ውስጥም በበጋው ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የፍራፍሬ ችግኝ ተከላ መከናወኑንና ጽድቀቱ በጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑን አስረድተዋል:: በቀሪው ጊዜ የተለያየ ዝርያ ያላቸው ሀገር በቀል የዛፍ ችግኞች ተከላ እንደሚከናወንም ገልጸዋል::

ወረዳው ካሉት 35 ቀበሌዎች በ30ዎቹ የአየር ላይ ካርታ (ጂፒኤስ) በመጠቀም ከ300 ሄክታር መሬት በላይ ለተከላው መለየቱን አመልክተዋል::

የጉድጓድ ዝግጅቱም ጎን ለጎን እየተከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ በክረምቱ ለደን የሚሆኑ ጥድ፣ ግራቪሊ፣ አኬሺያ፣ የተባለ ዝርያ ያላቸው ሀገር በቀል የዛፍ ችግኞች እንደሚተከሉ ጠቁመዋል::

በዚህ መልኩ ለመርሀ ግብሩ ከተዘጋጁት አካባቢዎች አንዱ የሆነውን ገሬ ቀበሌ ለጋዜጠኞች ቡድን አስጎብኝተዋል:: የክረምቱ የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብርም ከያዝነው ሰኔ ወር ጀምሮ እንደሚከናወን አስታውቀዋል::

የወረዳው ዓመታዊ ዝናብ ጥሩ የሚባል መሆኑንና ይህም ለሚከናወኑት የፍራፍሬና የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብሮች ተስማሚ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ተሾመ፤ ዝናቡ በበጋ የተተከሉት ፍራፍሬዎች ጽድቀት ጥሩ እንዲሆን እንዳስቻለም አመልክተዋል::



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

አቶ ተሾመ ሽባባው

# መመሪያው ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓትን ለማስፈን ያግዛል

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- የመንደር ንግድን ለመቆጣጠር የወጣው መመሪያ ፍትሐዊ የሆነ የንግድ ሥርዓትን ለማስፈን እንደሚረዳ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ፡፡

ቢሮው የመንደር ንግድ ቁጥጥር የአሠራር ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016 ተፈጻሚነት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት ውይይት አካሂዷል፡፡

በመድረኩ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ሰውነት አየለ እንደገለጹት፤ የመንደር ንግድ ቁጥጥር መመሪያው ወረዳዎችን እንደየስፋታቸው መጠን በመንደር በመከፋፈል የንግድ ተቋማትን ለመከታተል ያስችላል፡፡

መመሪያው ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ወደ ሕጋዊነት በማምጣት ፣ የንግዱን ማህበረሰብ ከአላስፈላጊ ወከባ ለመታደግና ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል ይረዳል ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት በክፍለ ከተማዎች የሚወሰዱ የቁጥጥር ርምጃዎች ወጥነት እንዳልነበራቸው አስታውሰው፤ በመመሪያው መሠረት እንደከተማ ወጥ በሆነ መልኩ በየትኛው አስተዳደር እርከን ምን አይነት ቅጣት እንደሚሰጥ በግልጽ በመቀመጡ አላስፈላጊ አሠራሮችን ያስቀራል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በአንድ አካባቢ ላይ የተለያዩ ባለሙያዎች ተመድበው ክትትል እንደሚያደርጉ ጠቁመው፤ በመመሪያው መሠረት በአንድ መንደር የተወሰኑ ቋሚ ባለሙያዎች ብቻ የንግድ ቁጥጥር እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል። ይህም ባለሙያዎች ላይ ተጠያቂነትን በማስፈን ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል እንደሚያግዝ አመላክተዋል።



የቁጥጥር ባለሙያዎች የንግድ ፍቃድ የሌለው፣ ባልታደሰ ፣በታገደና በተሰረዘ ንግድ ፍቃድ ብቻ የሚሰሩ ነጋዴዎች ላይ የማሸግና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት መብት እንዳላቸው ገልጸዋል። ሌሎች ጥፋቶች ላይ ግን የሚወሰደውን ርምጃ የሚወስነው ንግድ ቢሮ ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል። አሠራሩ ነጋዴውን ከአላስፈላጊ ውክቢያ የሚከላከል መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ዘሀራ መሀመድ በበኩላቸው፤ መመሪያው በንግዱ ማህበረሰብ ላይ ያሉ ችግሮችን ለመቀነስ እንደሚረዳ ይጠበቃል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም አነስተኛ የንግድ ሥራ የሚያከናውኑ ግለሰቦች ሳያጠፉ ተቆጣጣሪው አካል ደስ ባለው ሰዓት የንግድ ቤታቸውን የሚያሽግበትና ዘርፉ ለሙስና የሚጋለጥበት ችግር እንደነበር አንስተዋል።

በተጨማሪ ሕጋዊው ነጋዴ ባልተገባ የቁጥጥር ሂደት የተነሳ ሕገወጥነት የሚመርጥበት ሁኔታ እንደነበር ጠቁመው፤ መመሪያው ግን ሕገወጦቹን ደግሞ ወደ ሕጋዊነት የሚያመጣና ለሁሉም በፍትሐዊነት ለማገልገል የሚረዳ ነው ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ማህበር በመርካቶ አካባቢ ብቻ 24 ሺህ ነጋዴዎች ወደ ሕጋዊነት እንዲመጡ መሥራቱን ገልጸዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው...

ከ1ናው ገጽ የዞረ

አመራሮች በጋራ ስንመካከርና ስንወያይ ለደረሰው የትምህርት ጥራት ችግር መፍትሔ እናመጣለን ብለዋል፡፡

ዶክተር ብርሃነመስቀል እንደተናገሩት፤ ሁሌ ችግር የምናወራ ሳይሆን ከችግር የምንወጣበትን መፍትሔ አመልካቾችና ተግባሪዎች መሆን አለብን፤ ለዚህም ኮተቤ ዩኒቨርሲቲ የመፍትሔው አካል ለመሆን እየሠራ ነው፡፡

ለደረሰው ችግር ጥናትና ምርምርን ዋና ጉዳይ አድርገናል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ችግሩን ለማከም በጥናት ላይ የተመሠረተ ትግበራ ያስፈልጋል፤ የሚሠሩ ጥናቶችና ምርምሮችን ተከትሎ መፍትሔ መስጠት ይገባል ብለዋል፡፡

ምሁራን የሚሠሯቸው ምርምሮችና ምክክሮች የትምህርት ጥራት ስብራትን ለማከም ያግዛሉ፤ ውይይቱም ለችግሩ መፍትሔ ያስቀምጣል ብለዋል፡፡

የስብራቱ ባለቤቶች ራሳችን ነን፣ ለመፍትሔው መመካከርና የጋራ መፍትሔ ማስቀመጥ ያስፈልገናልም ብለዋል፡፡ ጊዜውን የዋጀ የዘርፍ አመራር፣ ዘመኑን የሚመጥን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የሚያውል መምህር እንደሚያስፈልግም ነው ያመለከቱት፡፡

የትምህርት ጥራት ስብራትን ለማከም በሚደረገው ሂደት የዘርፉ ምሁራን የሚሰሯቸው ጥናትና ምርምሮች፣ ምክክሮች ለመፍትሔ ግብአትነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱም ተናግረዋል፡፡

ጥራት ያላቸው መምህራንን ለማፍራት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች ቅበላ እየተከተልን እንገኛለን፣ ዩኒቨርሲቲው የሚመጥነውን መሠረተ ልማት ግንባታም እያካሄድን እንገኛለን ነው ያሉት፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የምርምር ስርጸት ዴስክ ኃላፊ ሰራዊት ሃንዲሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ምሁራን የሚሰሯቸው ምርምሮችና የሚያደርጓቸው ምክክሮች የትምህርት ጥራት ስብራትን ለማከም በሚደረገው ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል፡፡

ሰራዊት (ዶ/ር)፤ ምርምር ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ ውጤታማ ለመሆንና ተወዳዳሪነትን ለማስፈን የጎላ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በምርምርና ጥናት የሚገኝ ሃሳብ የትምህርት ጥራትን ለማከም፣ ለመንግሥት ውሳኔ ሰጪነትና ለፖሊሲ እንደግብአት እንደሚያገለግልም ተናግረዋል፡፡

ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ከተሰጡት ተልዕኮዎች መካከል የመማር ማስተማር ሂደቱን በማገዝ ብቁና ተወዳዳሪ መምህራንን ማፍራት መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

ሂደቱን በማሳለጥ በትምህርት ጥራት የደረሰውን ስብራት ሊጠግኑ የሚችሉ ባለሙያዎች እንደሚያፈራም ተስፋ ተጥሎበታል ብለዋል፡፡

ከምርምር እና ከውይይቱ የሚገኘው ሃሳብ ለፖሊሲ ዝግጅት ግብአት ይሆናል፡፡ በዘርፉ የደረሰውን የትምህርት ጥራት ስብራት ለማከም በሚደረገው ሂደትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል ሲሉም ተስፋቸውን ገልጸዋል፡፡

ዛሬ በሚጠናቀቀውና ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተጋበዙ ምሁራን በሚወያዩበት መድረክ፤ በመማር ማስተማር፣ በመምህራን የትምህርት ዝግጅቶችና በአጠቃላይ በዘርፉ ላይ የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎችን የሚያመለክቱ ከ23 ያላነሱ ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚቀርቡ ተገልጿል፡፡

# በዞኑ ሰላም...

ከ1ናው ገጽ የዞረ

ከዚህ ቀደም በመነሲቡ፣ ቆንዳላና ቤጊ በተባሉ የዞኑ ወረዳዎች ከፍተኛ የጸጥታ ችግር እንደነበር አስታውሰው፤ በተሠራው የተቀናጀ የሕግ ማስከበር ሥራዎች በአንጻራዊ ሰላም ሰፍኖ በወረዳዎቹ ልማት እየተካሄደባቸው መሆኑን አስረድተዋል።

በምዕራብ ወለጋ ዞን ቆንዳላ ወረዳ በእንስሳት ማደለብ፣ በንብ ማነብ፣ በበቆሎ ምርት፣ ሩዝ፣ አቮካዶ፣ ለውዝ፣ የአኩሪ አተር፣ የሸንኩርት ምርት ጨምሮ የተለያዩ የግብርና ልማት ሥራዎች በስፋት የሚመረትበት ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ በዞኑ መነሲቡ፣ ቆንዳላና ቤጊ ወረዳዎች የታዩት የልማት እንቅስቃሴዎች ኅብረተሰቡ ልማት ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዞኑ ለእርሻ የሚሆን ሰፊ መሬት፣ ከፍተኛ የውሃ ሀብት፣ ዕብነበረድና ወርቅን ጨምሮ በማዕድን ሀብትም የበለፀገ ዞን መሆኑን ጠቅሰው፤ ሀብቱ ለዞኑ ብሎም ለሀገራዊ ፋይዳ እንዲውል ባለሀብቶች ካለምንም ስጋት በዞኑ ኢንቨስት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በበኩላቸው፤ የአካባቢው ኅብረተሰብ ጥያቄ አሁን ላይ የምርጥ ዘር፣ የአፈር ማዳበሪያ ፣ የትራክተር ፣ የኮምባይነር የሰብል ማጨጃ መሳሪያዎች ይቅረብልን ማለታቸውን አስታውቀዋል።

የምዕራብ ወለጋ ዞን ወረዳዎች በጸጥታ ችግር ምክንያት ከመልማት ተስተጓጉለው የቆዩ መሆኑን አስታውሰው፤ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት በወሰዷቸው ርምጃዎች የአካባቢው ልማት ሥራ እየተሻሻለ መምጣቱን ተናግረዋል።

ከዞኑ አቮካዶና ሙዝ ወደ ውጭ መላክ መጀመሩን ጠቁመው፤ በወረዳዎቹ የሚደረገው የልማት ሥራ ተጠናክሮ ከቀጠለ የተለያዩ የልማት ጥያቄዎችም በአፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ ይጠናከራል ሲሉ አመላክተዋል።

# ቋሚ ኮሚቴው የመለኪያ መሳሪያዎች...

ከ1ናው ገጽ የዞረ

አዋጆች ጋር የይዘት መመሳሰል፣ የጥቅም ግጭትና የስልጣን መደራረብ ሳይኖረው ለአተገባበር ግልጽ በሆነ መንገድ ከመቅረብ አንጻር ያለበትን ደረጃ አስመልክተው ጥያቄዎች አንስተዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ ሰጥቶ የተነሱ ጥያቄዎችን እንደግብአት እንደሚወስድ አስታውቋል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ የተከበሩ ወይዘሮ አሻ ያህያ፤ ረቂቅ አዋጁ በተሻለ መልኩ አድጎና ዳብሮ እንዲፀድቅ በባለድርሻ አካላት የተነሱት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተካተው እንዲቀርቡ ጠይቀዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ለማህበራዊ እድገት ጠቀሜታና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ያለው እምርታ ከፍ ያለ በመሆኑ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ከማህበረሰብ ጋር ውይይት ይደረግበታል ያሉት ዋና ሰብሳቢ፤ ማህበረሰቡ የሚያነሳቸው ሃሳቦች በግብአትነት ተካተው እንዲቀርብ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ረቂቁ ከሀገር ውስጥ ወደ ውጪ የሚላከውና ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ምርት በመጠን ምንም አይነት ልዩነት እንዳይኖር በማድረግ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ ሚና አለው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሕጋዊ ሥነ-ልክ ረቂቅ አዋጅ ሀገሪቱ ወደ ውጪ በምትልከው ምርት ላይ የተጣራ መጠን እንዲኖር ስለሚያደርግ ከመጠን በላይ እየተላከ የምታጣውን ገቢ እንድታገኝ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ አሻ ገለጻ፤ ረቂቅ አዋጁ ለንግድ ልውውጥ፣ ለሰውና ለእንስሳት ጤና፤ ለአካባቢ ጥበቃ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመለኪያ መሣሪያዎችና ልኬቶች ወጥነትና ትክክለኝነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፤ የታሸጉ ምርቶች ላይ የተጣራ መጠን እንዲኖር በማድረግ ማህበረሰቡ ለከፈለው ዋጋ ተመጣጣኝ የምርት አገልግሎት እንዲያገኝ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ፍትሐዊ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ከማድረግ ባለፈ ከዓለም አቀፍ ጋር የሚደረገው የንግድ ግንኙነት የተመጣጠነ እንዲሆን ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

አዋጁ በአተገባበሩና በይዘቱ ከሌሎች የቁጥጥር አዋጆች ጋር የጥቅም ግጭትና የስልጣን መደራረብ እንዳይኖረው ለማድረግ የቀሩ ግብዓቶች ተካትተው መቅረብ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሪቂቁ ከባለድርሻ አካላት የተሰጠውን ግብዓትና ወደ ፊት ከማህበረሰቡ ጋር በሚደረገው ውይይት የሚነሱ ሃሳቦችን አካትቶ አሁን ካለው አተገባበርም በይዘትም ግልጽ ሆኖ እንዲቀርብ ጠይቀዋል፡፡

# የሕግ ማዕቀፉን በማሻሻል ተቀባይነት...

ከ1ናው ገጽ የዞረ

መካሄዱን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቦርዱ በቀጣይ የሚደረጉ ምርጫዎችን ፍትሐዊ፣ ግልጽ፣ ነጻና ተዓማኒ ለማድረግ የሚረዳ የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ይፋ ማድረጉን ገልጸው፤ ስትራቴጂካዊ ዕቅዱ የምርጫ የሕግ ማዕቀፍ፣ የዜጎች ተሳትፎና የግብ ትስስር፣ የምርጫ ሥራዎች፣ የምርጫ ባለድርሻዎች ትስስርና አጋርነት፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ምርጫ ቦርዱ ዕቅዱን ለማስፈጸም ቁርጠኛ ነው ያሉት ወይዘሮ ሜላተወርቅ፤ በዚህም በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ምርጫን ተዓማኒ በሆነ መልኩ ማካሄድ፣ ሁሉንም የምርጫ ሂደት ማዘመንና ማሻሻል እንደሚቻል አንስተዋል፡፡

ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ግልጽ የሆኑ ጠቅላላ ምርጫና የአካባቢ ምርጫ ለማድረግ ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ዕቅዱን ለማዘጋጀት 10 ወራት የጨረሰ ሲሆን፤ የፖለቲካ ፓራቲች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ተዘጋጅቶ የካቲት 2016 ዓ.ም ጸድቋል ብለዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም፣ የአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል፣ የምርጫ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ፋውንዴሽን የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸውን አመላክተዋል፡፡

ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ከምርጥ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችና ከ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ የተገኙ ትምህርቶች፣ ጥንካሬና ድክመቶችን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ተዓማኒነት ያለውና አርዓያ የሚሆን ምርጫን ለማካሄድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እቅዱን ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የኢድ አልአድሃ በዓል የመረዳዳት እና የመደጋገፍ በዓል ነው››

- ሀጅ ጦሃ ሃሩን -የአንዋር መስጊድ ኢማም

እስማኤል አረቦ

በእስልምና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል የኢድ አልአድሃ (አረፋ) በዓል አንዱ ነው። ኢድ አል አድሃ ወይም አረፋ ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸው እስማኤልን በአላህ ትእዛዝ ለመስዕዋት ሲያዘጋጁ በምትኩ ሙክት በግ መቅረቡን የሚያስታውስ በመሆኑ የመስዋዕት በዓል ተብሎም ይከበራል። አዳምና ሄዋን ከገነት ወጥተው ለረጅም ዘመናት ተለያይተው ከቆዩ በኋላ በአራራት ተራራ ላይ መገናኘታቸው የሚዘከርበት በዓል መሆኑንም የሃይማኖቱ አባቶች ይናገራሉ።

ኢድ አልአድሃ የመተሳሰብና መረዳዳት በዓል ከመሆኑም ባሻገር ሙስሊሞች የመስዋዕትነት በዓሉን አረፋ እርድ በመፈጸም፣ በጋራ በመጸለይ እና ከፈጣሪ ምህረትን የሚያስገኙ በጎ ተግባራትን በማከናወን ያሳልፉታል። ይህም ያጡ ወገኖች የሚደገፉበትና መረዳዳትና መደጋገፍ የሚታይበት በመሆኑ በዓሉ የተለየ ገጽታ ይዞ ይከበራል።

**አዲስ ዘመን - የኢድ አልአድሃ በዓል የሚከበርበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**ሀጅ ጦሃ ሃሩን -** ሀጅ ማድረግ ከአምስቱ የእስልምና መሠረቶች አንዱ ነው። ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ቢያንስ አንድ ጊዜ መካን ዘይረው መመለስ አለባቸው። መካ በመገኘትም የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ያከናውናሉ።

ቅዱስ ቁርዓንና ሌሎች ተያያዥ ጽሁፎች እንደሚያብራሩት የዒድ አል-አድሃ ታሪካዊ ዳራ ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸውን ለአላህ ለመሰዋት ያደረጉት ቁርጠኝነት የተመላበት ውሳኔ እና ለመስዋዕትነት የቀረበው ልጅ ያሳየው የተለየ ጽናት ነው። ነቢዩ ኢብራሂም የበኩር ልጃቸው የሆነውን ዒስማኢልን ያገኙት በእርጅና ዘመናቸው ነው። ታላቅ ሚስታቸው ሳራ ለፍሬ ባለመብቃቷ “ያ አላህ ያለ ዘር አታስቀረኝ፤ እኔን የሚተካ ሷሊህ የሆነ ልጅ ስጠኝ” በማለት ዱዓ አደረጉ። በዚሁ መሠረት በሳራ ፈቃደኝነት ሐጀራ የምትባለውን የቤት ሠራተኛቸውን አገቡ። ሐጀራም ዒስማኢል የተባለ ልጃቸውን ወለደችላቸው። ይህ ልጅ በአላህ ፈቃድ በመካ ከተማ እንዲያድግ የተወሰነ ስለነበረ ኢብራሂም ሐጀራን እና ዒስማኢልን ወደ ዐረቢያ ከተማ ወሰዷቸው።

ዒስማኢል ካደገ በኋላ ደግሞ አላህ “ልጅህን እንድትሰዋ ታዘሃል” የሚል ትዕይንት በህልማቸው አሳያቸው። የነቢያት ህልም ደግሞ ከራዕይ የሚቆጠር ነው። ስለዚህ ኢብራሂም በህልማቸው ያዩትን በዝምታ አላለፉትም። በወቅቱ የሆነውን ቅዱስ ቁርዓን እንዲህ ይተርካል።

ከርሱ ጋር ለስራ በደረሰ ጊዜም “ ልጄ ሆይ! እኔ በህልሜ የማርድህ ሆኜ አይቻለሁ፤ (እስቲ አንተም ነገሩን) ተመልከት። “ምን ይታይሃል” አለው። (ልጁም) አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ፈጽም፤ አላህ ቢሻ ከታጋሾቹ ሆኜ ታገኘኛለህ አለ” (ሱረቱ -ሷፍፋት፤ 102)

አባትና ልጅ በዚህ መንገድ ከአላህ የተላለፈውን ትዕዛዝ ሊፈጽሙ ተነሱ፤ ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸውን እንዲሰው የታዘዙት ከአረፋት መሬት ብዙም ባልራቀ ቦታ ላይ ስለነበረ ወደዚያው ጉዞ ጀመሩ። በመንገዳቸው ግን ኢብሊስ በሰው ተመስሎ በጣም ተፈታተናቸው፤ ሶስት ጊዜ ያህል እየወጣ “ ከስንት ዓመት በኋላ ያገኘኸውን አንድዬ ልጅህን ስትሰዋ ምንም አይጸጽትህም?... እንዴት ጅል ትሆናለህ” እያለ ሞገታቸው። ከአላህ ትዕዛዝ ፍንክች የማይሉት ኢብራሂም ግን ድንጋይ ከመሬት በማንሳት “አዑዙቢላሂ ሚነ-ሽይጣኒ ረጂም” እያሉ ኢብሊስን ወገሩት።

በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ነብዩ ኢብራሂም ዒስማኢልን ሊያርዱት አጋደሙት። ልጁም ምንም ሳያንገራግር ከመሬቱ ላይ ተኛ። ኢብራሂም ልጁን ሊያርዱት ሲሞክሩ ግን ቢላዋው አላርድ አላቸው። ኢብራሂም እንደገና ቢላዋውን ገዘገዙት። ነገር ግን ፈጽሞ ዶለዶመ። ልጁ የሆነው ነገር አልገባውም። አባቱ ቶሎ ስላላረደው ተገረመና “አባዬ! ፣ ምናልባት የአባትነት ፍቅር ይዞህ ይሆናል በቶሎ ያላረድከኝ፤ እስቲ ዓይኔን በጨርቅ ሸፍነውና እርዱንሞክር” የሚል አስተያየት ሰጠ።

በዚህን ጊዜ ግን ከወደ ሰማይ ጥሪ መጣ። የአላህ መልአክ “ኢብራሂም ታላቅነትህን አስመስክረሃልና እርዱን አቆየው” በማለት አወጀ። በምትኩም መልአኩ ከገነት ያመጣውን በግ እንዲያርድና ልጁን ወደቤቱ እንዲወስደው ነገረው። በዚህም መሠረት በጉ ታረደ። ኢብራሂምና ዒስማኢልም ወደ መካ ከተማ ተመለሱ። ሁለቱ ሰዎች ለፈጣሪ መታዘዝን በግልጽ ያሳዩባት ያቺ ዕለት የዒድ አል-አድሃ በዓል ሆና እንድትከበርም ተወሰነ። ዒስማኢል ለመስዋእትነት የቀረበበት ድርጊት ደግሞ በዚሁ ዕለት የሚታረደው “ኡድሒያ” መነሻ ሆነ።”

ይህን ታሪክ መነሻ በማድረግ ኢድ አል-አደሃ ይከበራል። በዓሉ የመስዋዕት፣ የእርድ በዓል ነው። በተለይም የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ቀን ከብት የማረድ ግዴታ አለበት። በተለይም በግ ማረድ የበለጠ የተወደደ ተግባር ነው።

ይህን ታሪክ መነሻ በማድረግ ኢድ አል-አደሃ ይከበራል። በዓሉ የመስዋዕት፣ የእርድ በዓል ነው። በተለይም የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ቀን ከብት የማረድ ግዴታ አለበት። የተቀረውም ሙስሊም ዕለቱን አቅሙ በፈቀደ ከብት በማረድ ከቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ጋር ያሳልፈዋል። ለኢድ አል አድሃ አንድ ሰው ከሚያርደው ከብት ሲሶውን ብቻ እንዲወስድ ነው ደንቡ። የተቀረው ሲሶው ለዘመድ አዝማድ፣ ሲሶው ደግሞ አቅም ለሌለው ደሃ እንዲከፋፈል እስልምና ያዛል።

የአረፋ በዓል ታላቅ በዓል ነው። ከበዓሉ ቀን አንድ ቀን አስቀድሞ ወይንም የዋዜማው ቀን አረፋ ይባላል። የእስልምና እምነት እንደሚያስተምረው አረፋ የሚለው ቃል በዐረብኛ “አወቀ” እንደማለት ነው። ይህም ታሪክ አለው። አዳምና ሔዋን ወይንም አደምና ሃዋ ከጀነት ወደ ምድር ከወረዱ በኋላ ለብዙ ዘመናት ተጠፋፍተው ነበር። ለረጅም ጊዜ ሲፈላለጉ ከቆዩ በኋላ በዚህ ዕለት በሳዑዲ ዐረቢያ ባለው የአረፋ ተራራ ላይ ተገናኙ። እዚያም “ዐረፍቱከ... ዐረፍቱኪ" ተባባሉ። “አወቅኩህ! አወቅኩሽ” ማለታቸው ነው። ይህንን ታሪክ ለመዘከር ሲባል ነው የዐረፋን በዓል ማክበር የተጀመረው ይህ በዙልሂጃ ዘጠነኛው ቀን የሚከበር በዓል ነው።

**አዲስ ዘመን - የኢድ አልአድሃ በዓል እንዴት ይከበራል ?**

**ሀጅ ጦሃ ሀሩን -** የኢድ አልአድሃ በዓል በሁለት አይነት መልኩ ይከበራል ብለን መውሰድ እንችላለን። አንደኛው ኃይማኖታዊ መስፈርቶችን ጠብቆ ወደ መካ በመሄድ የሚደረግ የጸሎት ሥነሥርዓት ነው። የሃጂ ተጓዦች ከሚከውኗቸው አበይት ሃይማኖታዊ ተግባራት አንዱና ወሳኙ የአራፋት ተራራን መውጣት ነው። ከመካ በስተምስራቅ 20 ኪሎሜትር ርቆ የሚገኘውን ቅዱስ ተራራ መመልከትና ሃይማኖታዊ ሥነርዓቶችን በዚያው መፈጸም እንደሚገባ የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ ያዛል። በአረፋ ቀን (ከበዓሉ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ) የሃጂ ተጓዦች ከሚና ወደ አራፋት ተራራ ይወጣሉ። ጸሀይ እስክትጠልቅ ድረስም ቅዱስ ቁርአን እያነበቡ፣ ፈጣሪን እያወደሱና እና የምህረት እጁን እንዲዘረጋ እየለመኑ ይቆያሉ።

ሁለተኛው ደግሞ ወደ መካ ለመሄድ ዕድልን ያላገኙ በሀገር ውስጥ የኢድ አልአድሃን በዓል በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ። በሀገር ውስጥ በአዲስ አበባ ስታዲየምና በክልል የመስገጃ ሜዳዎች ሰፊው ሕዝበ ሙስሊም በተገኘበት ይከበራል። ከሰላት በኋላ አቅም ያላቸው ሰዎች በግና ሌሎች እንስሳትን በማረድ አቅም ለሌላቸው ጎረቤቶቻቸ በማካፈል በዓሉን በጋራ ያሳልፋሉ።



ፎቶ ዳኜ አበራ

ዒስማኢል ካደገ በኋላ ደግሞ አላህ “ልጅህን እንድትሰዋ ታዘሃል” የሚል ትዕይንት በህልማቸው አሳያቸው፡፡ የነቢያት ህልም ደግሞ ከራዕይ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለዚህ ኢብራሂም በህልማቸው ያዩትን በዝምታ አላለፉትም

**አዲስ ዘመን - በኢድ አልአድሃ የሚታየው መረዳዳት ምን ይመስላል?**

**ሀጅ ጦሃ ሃሩን ፤** የኢድ አልአድሃ በዓል የእርድ በዓል ነው ። አቅሙ ያለው ለበዓሉ በግ ወይም ከብት አርዶ ከድሆች ጋር ተካፍሎ መብላት ይጠበቅበታል። በየቤቱ አቅም እንደፈቀደ ምግብ አዘጋጅቶ ከዘመድ ወዳጅ ከጎረቤት ጋር መብላት መጠጣትም በዚህ በዓል የተለመደ ነው ።

የዕርድ በዓል በመባል ለሚታወቀው የአረፋ በዓል ከተገኘ በግ፣ ፍየል፣ በሬ የመሳሰሉትን ማረድ ግድ ይላል። አቅሙ ለሌላቸው ሰደቃ መስጠት ኢስላማዊ ግዴታ ነው። በዓሉ እርድና የመረዳዳት በዓል ተብሎ ይታወቃል።

የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል የእርድ ሥነ ሥርዓቱ የሚፈጸመው የኢድ ሶላት ከተሰገደ በኋላ ነው። ነብዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ) የአምላካቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ልጃቸውን ለመስዋእትነት እንዳቀረቡ ሁሉ ሙስሊሞችም ፈጣሪያቸውን ለማስደሰት ትዕዛዙን በአግባቡ እየተገበሩ ይገኛሉ። በአረፋ መረዳዳትና መደጋገፍ ቢስተዋልም በዚህ ወቅት ሚስተዋለው መደጋገፍ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የሚከናወን ተግባር ሊሆን ይገባል። የደካሞችን ቤት በማደስ፣ ለጦም አዳሪዎች የዕለት ጉርሳቸውን ማቅረብ ፤የታረዙትን ማልበስና ወላጅ አልባዎችን መጎብኘት በኢድ አልአድሃ የሚወደድ ተግባር ቢሆንም በሌሎችም ቀናት እነዚህ በጎ ተግባራት ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው ናቸው።

ማኅበረሰቡ በበዓል ወቅት ከመረዳዳት ባሻገር ሀገራዊ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በጋራ መቆምም ይጠበቅበታል። ሰዎች በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ጉዳት ሲደርስባቸው፤ ከአካባቢያቸው ሲፈናቀሉ፤ ሲራቡና ሲጠሙ ዝም ብሎ መመልከት ከእስልምና አስተምሮ አንጻር የሚያስጠይቅ ነው። በተለይም ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ስንመለከት በርካቶች ቤት ንበረታቸውን ጥለው የተሰደዱበትና የተፈናቀሉበት ሁኔታ ነው ያለው። ስለዚህም የኢድ አልአድሃ በዓልን ስናከብር እነዚህን ወገኖች በመጎበኘነትና ወገናዊ ፍቅር በመስጠት ሊሆን ይገባል።

አሁን አሁን የድሆችን ቤት በማደስ፤ ማዕድ በማጋራትና የተጀመሩ ሥራዎች የሚያስደስቱ ናቸው።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹የኢድ አልአድሃ በዓል የመረዳዳት...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

እስልምና በጣም የሚደግፏቸውና አብዝቶም የሚሠራባቸው ናቸው። ወቅቱ ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ መረዳዳት የሚያስፈልግበት በመሆኑ የተለያዩ ድጋፎች ለተፈናቃዮችና ችግር ለደረሰባቸው ሰዎች ማድረስ የግድ ይላል።

በእርግጥ በአሁኑ የመተሳሰብ ፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በተለይም አቅመ ደካማ ለሆኑ ዜጎች ማዕድ ማጋራትና ድሃ ድሃ ቤት እድሳት በዚህ ረገድ ተጠቃሾች ናቸው።

በዝቅተኛ ኑሮ ሕይወታቸውን ሲገፉ የቆዩ ነዋሪዎችን ቤት በማደስ ዜጎች በተለይም በኋለኛ ዘመናቸው በተሻለ መጠለያ ውስጥ እንዲኖሩ የሚደረጉ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ዛሬ የእኛነታችን መገለጫዎች እየሆኑ ነው።በየአመቱም ክረምት በመጣ ቁጥር የበርካታ አቅመ ደካማ ዜጎች ቤቶች እየታደሱ ዜጎችን ከዝናብና ከብርድ የመታደጉ ተግባር በመንግሥት፤ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በነዋሪው ተሳትፎ እውን እየሆነ ነው።

በሌላም በኩል በአቅም ማነስ ምክንያት በቀን አንድ ጊዜ እንኳን እራሳቸውን መመገብ የማይችሉ ዜጎችን በጋራ ማእድ እንዲቆርሱ በማድረግ ረገድ የተጀመሩት በጎ ተግባራት የኢትዮጵያውያንን በጎ እሴቶች ማስቀጠያዎች እየሆኑ ነው። በተለይም በበዓላት ወቅት አቅመ ደካሞች በዓላትን በእኩል ተደስተው እንዲያሳልፉ በበጎ ፈቃድ ወጣቶች ጭምር የሚከናወኑ የማዕድ ማጋራት በጎ ሥራዎችን ለተመለከተ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን መተሳሰብና መረዳዳት የሚያመላክት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የአይሁድ፤ የክርስትናና የእስልምና ኃይማኖቶችን ተቀብላ ያስተናገደችና ለዘመናትም በመከባበር ሳይ እንዲኖሩ ያደረገች ሀገር ናት። በዚህ ረገድ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**ሀጂ ጦሃ ሀሩን** ፤ ኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ በርካታ አኩሪ እሴቶች አሏቸው። ከእነዚህ ውስጥ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴቶቻችን በዋነኝነት ተጠቃሾች ናቸው። ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲያጋጥሙ መሰናክሎችን በመረዳዳትና በመደጋገፍ የማለፍ ጥበብን ከማዳበራቸውም በላይ ለተበደሉት መሸሸጊያ፤ ለተሰደዱት መጠለያ ሆነው ዘልቀዋል።

ኢትዮጵያውያን ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲያጋጥማቸው በመረዳዳትና በመደጋገፍ የማለፍ ጥበብን የታለበሱ ሕዝቦች ናቸው። በርሃብም ሆነ በድርቅ፤ በግጭትም ሆነ በጦርነት ወቅት በመረዳዳት አስከፊ ጊዜያቶችን አሳልፈዋል።

ኢትዮጵያውያን የእምነት ልዩነት ሳይበግራቸው ደስታንም ሆነ ኀዘንን በጋራ ያሳልፋሉ። የሀገራችውንም ዳር ድንበር ይጠብቃሉ፤ ወራሪን በጋራ ድል ይመታሉ፤ በልማት ይሳተፋሉ ፤ ሀገራቸውን ጥሪ ስታደርግላቸው ያለምንም ማመንታት ከጎኗ ይቆማሉ። ይህ አንድነታቸውን አብሮነታቸውም ከበርካታ የዓለም ሕዝብ ዘንድ ትልቅ ክብርና ግርማ ሞገስ አጎናጽፏቸዋል። በአርአያነትም እንዲወሰዱ አድርጓቸዋል።

ኢትዮጵያውያን ዘር ፤ ቀለምና ኃይማኖት ሳይለዩ የተቸገረን መርዳት፤ የተራበን ማብላት፤ የተጠማን ማጠጣትና የታረዘን ማልበስ ያውቁበታል። እንኳን እርስ በእራሳቸው ይቅርና ባህር አቋርጦ፤ ድንበር ተሻግሮ ለመጣ ስደተኛ ጭምር በራቸውን ክፍት አድርገው ፤ ያላቸውን አካፍለውና ፍቅር ለግሰው ማኖር የሚችሉ ሕዝቦች መሆናቸውን በርካታ የታሪክ መዛግብት የሚያወሱት ሃቅ ነው።

ኢትዮጵያውያን ከመካ የተሰደዱ የነብዩ መሃመድ ተከታዮችንና ቤተሰቦችን ተቀብላ በማስተናገድና በማኖርና የጎላ ታሪክ ያላትና ለእስልምና ኃይማኖትም ባለውለታ ተደርጋ የምትቆጠር ሀገር ከመሆኗም ባሻገር ይህ አኩሪ ታሪክ ሺ ዘመናትን



ተሻግሮ ዛሬም ድረስ ከ 1 ሚሊዮን በላይ ስደተኞች ተቀብላ በእንክብካቤ የምታስተናግድ ሀገር ነች።

ሀገሪቱ ውስጥ አይሁድ ነበሩ አሁንም አሉ ይባላል፤ ክርስትናም ቀድሞ የነበረ ሲሆን እስላም ደግሞ ከ አንድ ሺ አራት መቶ አርባ አራት አመተ ሂጀራ በፊት ነበረ የመጣው። እንግዲህ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ኃይማኖቶች አብረው ኖረዋል። በእርግጥ አብረው ይኑሩ እንጂ የሚበላለጡ ነገሮች ነበሩ። መንግሥታት ሲቀያየሩ ከፍና ዝቅ የሚያስበሉ ነገሮች ነበሩ። ሕዝብ እንደ ሕዝብ ግን በአብሮነት ተቻችሎ ተከባብሮ አብሮ መአድ ቆርሰው አብረው ኖረዋል። አሁን ግን በሀገራችን ኃይማኖቶች እኩል መብት አግኝተዋል ብዬ አስባለሁ። ሁላችን በጋራ በመሆን የኃይማኖቶች ጉባዔ ላይ አብረን እየሠራን ነው።

ሕዝቡ የእስልምና ኃይማኖት በአል ሲመጣ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በአብሮነት ተከባብሮ ተደጋግፎ መአድ የሚቆርስበት ሁኔታ ነው ያለው። ሀገራችን ከዚህ ረገድ የዓለም ምሳሌ የምትሆን ሀገር ናት። ሕዝቡ ውስጥ ያለው መከባበርና መቻቻል በየትኛውም ሀገር የሚታይ አይደለም። ሕዝቡ ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ ማስቀጠል ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡- የቀደሙ የሀገር እሴቶችን አስከብሮ ከማስቀጠል አንፃር ከሕዝበ ሙስሊሙ ምን ይጠበቃል?**

**ሀጂ ጦሃ ሀሩን** ፤ እኛ ለሕዝበ ሙስሊሙ እያስተላለፍን ያለው መልእክት ሀገራችን በተለይም በዚህ ጊዜ ሁሉም የኃይማኖት አባል ችግሩንም ደስታውን በጋራ እየተቀበለበት ያለበት ሁኔታ መኖሩን ነው። ሁላችንም የግል ኃይማኖት ቢኖረንም ሀገራችን ግን አንድ ናት፤ ይህችን ሀገር ደግሞ ሰላሟን መጠበቅ፤ ልማቷን ማስቀጠል፤ ከዚህ በፊት ይዘነው የመጣነውን የአብሮነት ባህል ማሳደግ ይኖርብናል።

ከበፊቱ የበለጠ መቻቻል ከሚለው እሳቤ ወጥተን መደጋገፍና መተባበር መፈቃቀር ሕዝቡ መገለጫው እንዲሆን መሠራት ይኖርበታል። የነበረን እሴት አሳድገን እጅ ለእጅ ተያይዘን ማደግ ማለፍ ይኖርብናል እላለሁ። በዓሉ የመረዳዳት በዓል በመሆኑ ያለው ለሌለው ያካፍልበታል፤ ያግዝበታል፤ የፈጣሪውን ትዕዛዝ ይፈጽምበታል ብለዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ሰላም የሁሉም ኃይማኖቶች አስተምህሮ ነውና በሰላም ችግሮችን ከመፍታት ረገድ አማኞችም ሆኑ የሃይማኖቱ መሪዎችም ምን ማድረግ አለባቸው?**

**ሀጂ ጦሃ ሀሩን ፡-** ሁሉም ሃይማኖቶች፤ ሰላምን ፍቅርን አብሮነትን ይሰብካሉ። ያንን አስተምህሮ ደግሞ ወደ ኽዝቡ የሚያስተላልፉት የተማሩ የበቁ አባቶች ናቸው። እነዚህ አባቶች በመመሪያ ውስጥ ያለውን ነው ሕዝቡ ጋር የሚያደርሱት።

እርግጥ በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ የፖለቲካ አካላት ሰላምን የማይፈልጉ ጥላቻን የሚዘሩ ከሌላ በኩል አልሳካ ሲላቸው የመጣላት ጥላቻን የመዝራት ሁኔታዎች ይታይባቸዋል። እኛ ግን እንደ ኃይማኖት አባት ኃይማኖት የግል ነው ፖለቲካ አይግባ በማለት ሕዝቡን ንፁህ የሆነ መንፈሳዊ አስተምህሮ ማስተላለፍ ይኖርብናል። የኃይማኖት አባት እንደ ስሙ የኃይማኖት አባትነቱን ተርድቶ ከፖለቲካና ከሌሎች ዓላማዎች ማስፈፀሚያ ከመሆን ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል።

ሕዝቡም ባለችው አንድ ሀገር እምነቱን በተገቢው መልኩ ለማስፈፀም የሀገር ሰላም ላይ ትኩረት ሰጥቶ በአብሮነት መሥራት ይጠበቅበታል። ለመኖርም፤ በነፃነት ኃይማኖቱን ለማምለክም ቅድሚያ ሀገር መኖር ይኖርባታል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን አሁን ይህንን የቆየ የመከባበር ባህል ለመበረዝ የሚሞክሩ አልጠፉም። ለእነዚህ ሰዎች የሚያስተሳልፉት መልዕክት ምንድን ነው ?**

**ሀጂ ጦሃ ሀሩን፡-** እኛ የምናስተላልፈው መልእክት ሃይማኖታዊ ነው። የፖለቲካ ችግራችሁን ሌሎች ጥያቄዎቻችሁን ወደ ኃይማኖታችን አታምጡብን እያልን ነው መልእክት የምናስተላልፈው። በአላህ ፀሎት አድርገን አደብ እንዲሰጣቸው ዱኣ ነው የምናደርገው።

እኛ በእድሜያችን ብዙ መንግሽታትን አይተናል። ብዙ የፖለቲካ አስተሳሰብ የነበራቸውን መንግሽታትን ተመለከተናል። ሁሉም በጊዜ ሂደት አልፏል። የማያልፈው ሕዝብ ነው፤ የማይጠፋው ሀገር ነው፤ የማይጠፋው ኃይማኖት ነው ይሄንን ሕዝቡ ጠንቅቆ ማወቅ ይገባዋል፤ ሁሉንም ነገር በሰከነ አእምሮ መመልከት ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን - ሀገራችን ብሄራዊ ምክክር እያካሄደች ነው።ይህ ምክክር እንዲሳካ ከኃይማኖት አባቶች ምን ይጠበቃል ?**

**ሀጂ ጦሃ ሀሩን ፡-** ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል። የእስልምና ኃይማኖትም ችሮችን በምክክር መፍታትን አጥብቆ ይደግፈዋል። ሰዎች በትንሽ በትልቁ ከሚጣሉ ይልቅ በንግግር እና በውይይት ቢፈቱ የተሻለ ነው። ውጤትም የሚያመጣው እሱ ነው። ንትርክና ጭቅጭቅ የሰይጣን መንገድ ነው። ስለዚህም ይህንን መጥፎ መንገድ መዝጋት አለብን። በግለሰብም ይሁን በሀገር ደረጃ ችግሮች ሲያጋጥሙ መፍትሄ ማግኘት የሚቻለው በምክክር እና በውይይት ብቻ ነው። ከዛ ውጪ ያለው መንገድ አክሳሪ ነው።

በሀገራችን ውይይት እና ምክክር መጀመሩ በጣም የምደግፈው ነው። ከወዲሁ እንኳን በርካታ ችግሮችን እየቀረፍን መጥተናል። በቀጣይም ብዙ መፍትሄዎች ይመጣሉ ብዬ አስባለሁ።

ይህ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን ደግሞ የኃይማኖት አባቶች ከፍተኛ ሚና አላቸው። የኃይማኖት አባቶች ሲናገሩ ሁሉም ስለሚሰማቸው በአግባቡ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል። ሆኖም እኔን ጨምሮ በርካታ የኃይማኖት አባቶች በምክክሩ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ አለመሆናችን አግባብ አይደለም። ይህ በቀጣይ ሊታሰብበት የሚገባው ነው።

**አዲስ ዘመን - ስነበረን ቆይታ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ሀጂ ጦሃ ሃሩን -** እኔም አመሰግናለሁ።

**ነብዩ ኢብራሂም ዒስማኢልን ሲያርዱት አጋደሙት። ልጁም ምንም ሳያንገራግር ከመሬቱ ሳይ ተኛ። ኢብራሂም ልጁን ሲያርዱት ሲሞክሩ ግን ቢላዋው አላርድ አላቸው፡፡ ኢብራሂም እንደገና ቢላዋውን ገዘገዙት። ነገር ግን ፈጽሞ ዶለዶመ**

# ማህደረ ጤና

# አርማወር ሀንሰን በግማሽ ክፍለ ዘመን ጉዞ

**አስናቀ ፀጋዬ**

የህክምና ምርምር ተቋም የሆነው አርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት የተቋቋመው በሲውዲንና ኖርዌይ ህፃናት አድን ድርጅትና በበርገን ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በተደረገ ትብብር እ.ኤ.አ በ1970 ነበር። ስያሜውንም ያገኘው በእውቁ ሳይንቲስትና ለመጀመሪያ ጊዜ የስጋ ደዌ በሽታ መንስኤ ‹‹ማይክሮባክቴሪየም ሊፕሬ›› መሆኑን ባረጋገጠው ኖርዌያዊ ጄራርድ ሄነሪክ አርማወር ሀንሰን ነው።

ኢንስቲትዩቱ ከሀገር ባለፈ ለአፍሪካና ለዓለም የሚተርፉ በርካታ ሳይንሳዊ ምርምሮችን አድርጎ በዓለም አቀፍ መፅሄቶችና ጋዜጦች ላይ አሳትሟል። ዛሬም ወቅታዊና አንገብጋቢ በሆኑ ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ የምርምር አብርክቶዎችን እያደረገ ይገኛል።

የአርማወር ሀንሰን ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ እንደሚናገሩት፣ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ይዘታቸውን፣ መልካቸውንና ዓላማቸውን እየቀየሩ ዛሬ ላይ ደርሰዋል። የአርማወር ሃንሰን የህክምና ምርምር ኢንስቲትዩት ግን ስያሜውንና ዋናውን ተልእኮውን ሳይቀይር አምስት አስርት ዓመታትን ተሻግሯል። ኢንስቲትዩቱ የስጋ ደዌ በሽታ የሰውነት መከላከል ሃይልን ለመመራመር ተብሎ ለአንድ በሽታ ምርምር ነበር የተቋቋመው። ስሙንም ያገኘው ያንን በሽታ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም ካሳወቀው ኖርዌያዊ ሳይንቲስት ከሆነው አርማወር ሀንሰን ነበር።

ኢንስቲትዩቱ ይህን ሥራ ሲያከናውን ሌሎች ተግዳሮቶች ወደ ኢትዮጵያ መጡና በስጋ ደዌ የምርምር የተጀመረው መሠረተ ልማት፣ የሰው ሃይል፣ የተቋም የምርምር ባህል ወደሌሎችም በቀላሉ መሄድ ስለቻለ ወደ ቲቢ፣ ኤች አይ ቪ፣ ቁንጭር፣ ወባ፣ ተላላፊ ያልሆኑና ወደሌሎች የአንጀት ትላትል በሽታዎች ምርምር በሂደት መግባት ችሏል። እነዚህ የምርምር ሥራዎች አርማወር ሀንሰን የምርምር ተቋም እንደመሆኑ በታዋቂ የዓለም የምርምር መፅሄቶች ላይ የሚታተሙ ናቸው። መታተማቸው ብቻውን ግን ለኢትዮጵያ ብዙ ጥቅም አይሰጥም።

ብዙ ጥቅም እንዲሰጥ አሁንም የውስጥ አሠራር ሥርዓትን ቀይሮ የምርም ውጤት ምክረ ሃሳቦች የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦች ሆነው ተሰንደው ለፖሊሲ አውጪዎች እንዲደርሱ፣ በጤናው ዘርፍ ሥራ ላይ ላሉ የጤና ባለሙያዎች እንዲደርሱና ተግበራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ተብሎ አደረጃጀት ተፈጥሮ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። እነዚህ ሥራዎችም አድገው ኢንስቲትዩቱን ዛሬ ያለበት ደረጃ ላይ አድርሰውታል። ይህ የሃምሳ አራት ዓመት የአርማወር ሀንሰን ምርምር ኢንስቲትዩት ትሩፋት በተለይ በበሽታ ምርምርና ጥናት ዙሪያ የተገኙ ውጤቶች ለኢትዮጵያና ለዓለም መታወቅ ስላለባቸው ይህን የማስተዋወቅ ሥራ ኢንስቲትዩቱ ሠርቷል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚያብራሩት፣ አርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት በሃምሳ አራት ዓመታት ጉዞው በርካታ ነገሮችን አሳክቷል። የመጀመሪያው እውቀትን ማበልፀግ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ በ1962 ዓ.ም ሲመሠረት ከታተመው የመጀመሪያው የስጋ ደዌ በሽታ የሰውነት የመከላከል ሃይል እውቀት ጀምሮ አሁን በቀጣዮቹ ሳምንታት ከሚወጡ የምርምር ህትመቶች ሁሉ ለዓለም የሳይንስ ቋት እውቀትን ማበርከት ችሏል። ብዙ ጊዜ ሳይንሳዊ እውቀቶች የሚወጡት ካደጉት ሀገራት ቢሆንም ኢትዮጵያም እንደ አደጉት ሀገራት በእነርሱ ተርታ የሚሰለፍ እውቀት በልጆቿ ሥራ ከኢትዮጵያ ምድር ታወጣለች የሚለውን ኢንስቲትዩቱ አሳይቷል።

ከ1 ሺ በላይ የሚሆኑና ኢንስቲትዩቱ የወጡ የምርምር ፅሁፎች በታዋቂ የዓለም የምርምር መፅሄቶች ላይ ታትመዋል። የዛሬ ዓመት የወባ በሽታን በሚመለከት ‹‹ኔቸር ሜዲስን›› በሚባል በዓለም አንቱ በተባለ የምርምር መፅሄት ላይ ማሳተም ተችሏል። ኒዮርክ ታይምስም ይህን ሥራ ጠቅሶ በጋዜጣው የፊት ገፅ ላይ ይዞ ወጥቷል። የኢንስቲትዩቱ መሪ ተመራማሪ በአሜሪካ ኮንግረንስ ላይ ተጠርቶ ንግግር እንዲያደርግ ተደርጓል። በተመሳሳይ የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማም ተመራማሪውን ጠርቶ ንግግር እንዲያደርግ ጋብዟል። ከዚህ አንፃር እውቀትን ማበልፀግና ተደራሽ ማድረግ ትልቁ የምርምር ሥራ ስለሆነ አርማወር ሀንሰን ምርምር ኢንስቲትዩት ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በርካታ በሽታዎች እውቀትን የማበልፀግ ሥራ ሠርቷል።

እነዚህ እውቀቶች ታዲያ እውቀት ብቻ ሆነው አልቀሩም። እውቀቶቹ ወደ ሥራ ተቀይረዋል። የዛሬ ሃያ ዓመት አካባቢ ‹‹ኢሳት ፋይፍ›› የተሰኘና ከኢንስቲትዩቱ የወጣ የምርምር ውጤት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለህክምና አገልግሎት ወደ ሥራ ገብቷል። በሌላ በኩል ከሰባት ሀገሮች ጋር በጋራ በመሆን ኢንስቲትዩቱ ኢትዮጵያን ወክሎ ከአለርት ሆስፒታልና ከቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ጋር በመተባበር መድሃኒቱን የተላመደ ቲቢ የሚወስደው የህክምና ጊዜ ከሃያ አራት ወር ወደ ዘጠኝ ወር በምርምር እንዲወርድ አድርጓል።

በቅርቡ ደግሞ በተሠራ ሁለተኛ ዙር ጥናትና ምርምር ሥራ መድሃኒቱን የተላመደ ቲቢ ህክምና ከዘጠኝ ወር ወደ ስድስት ወር መውረድ እንደሚችል አሳይቶ ይህንኑ የምርምር ሥራ በታወቀውና ‹‹ላንሴት›› በተሰኘው የምርምር መፅሔት ላይ አሳትሟል። የዓለም ጤና ድርጅትም ይህን ምክረ ሃሳብ ወስዶ መድሃኒቱን የተላመደ ቲቢ የምርመራ ፕሮቶኮልን ቀይሯል። ቲቢ የሁሉም ሀገር በሽታ እንደመሆኑ ይህ የምርመር ተፅዕኖ ዓለም አቀፋዊ ነው። ኢንትቲትዩቱም በዚህ የምርምር ሥራ ለዓለም ጤና መጠበቅ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በተመሳሳይ በኤች አይ ቪ ዙሪያም በኢንስቲትዩቱ በኩል ትልልቅ የምርምር ውጤቶች ወጥተዋል። በጉበት በሽታም ዙሪያ እንደዚሁ ሰፋፊ የምርምር ሥራዎች ተሠርተዋል። ከዚህ በሻገር የኢትዮጵያ ጤና ሚኒስቴር የሀገሪቱን የጤና ልማት ሥራ የሚመራ በመሆኑ በምርምር የሚገኙ ምክረ ሃሳቦች ወደ ፖሊሲ ተቀይረው ፤ ፖሊሲዎቹ ደግሞ ወደ ስትራቴጂ ተለውጠው እንዲተገበሩ በአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት በኩል ሰፋፊ ሥራዎች ተከናውነዋል። ለአብነትም ‹‹አኖፍሊስ ስቴፊንሲያ›› በተሰኘችውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የተከሰተችውን አዲስ የወባ ትንኝ ዝርያ ለመከላከል ልዩ ስትራቴጂ እንደሚያስፈልግ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ምክረ ሃሳብ ወጥቶና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

ይህች አዲስ የወባ ዝርያ ፓራሳይት ባህሪዋን ቀይራ ዘረመልን በማጥፋት ለምርመራ ጥቅም ላይ የሚውለውን አፋጣኝ የምርመራ ዘዴን ታልፈዋለች። አትታይም፤ ትደበቃለች። የዚህ አይነት ችግር በኢትዮጵያ ውስጥ በመታየቱ ትኩረት እንዲደረግ በኢንስቲትዩቱ በኩል ምክር ሃሳብ ቀርቧል። በዚህ መሠረት ጤና ሚኒስቴር ፖሊሲ ቀይሮና ስትራቴጂ ነድፎ አዲስ የመመርመሪያ ቴክኖሎጂ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ አድርጓል።

ክትባትን በሚመለከት የማጅራት ገትር ክትባት አይታወቁም ነበር። ይሁንና የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች በሰሯቸው ሥራዎች ‹‹ስትሬን ኤክስ፣ ስትሬን 135›› የተሰኙ የማጅራት ገትር ባክቴሪያ አይነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ ታውቆ ከዛ በፊት የነበረው ክትባት የሚሸፍናቸው እነዚህን የሚይዝ እንዳልነበርና እነዚህን እንዲይዝ አድርገዋል። በዚህም ክትባቱ ሥራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ይገኛል። ኒሞኒያ ላይ የተሠራው ሥራም ተመሳሳይ ነው። የኒሞኒያ ክትባትም አስር የተለያዩ የክትባት አይነቶችን የሚይዝ ነበር። በኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች አማካኝነት በተደረገ ምርምር ክትባቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን እንዲይዝና ክትባቱ ገብቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚገልፁት በዓለም ዙሪያ ያሉ የመንግሥት የምርምር ተቋማት በመንግሥት ይደገፋሉ። መሠረተ ልማት በመንግሥት ይሠራል። ግብዓቶች በመንግሥት ይገዛሉ። የሠራተኛ ደሞዝ በመንግሥት ይሸፈናል። ነገር ግን ፕሮጀክቶች በሀገር ሀብት ብቻ አይሸፈኑም። በአሜሪካን ያሉ ትላልቅ ተቋማት ድጋፍ አግኝተው ነው የምርምር ሥራ የሚሠሩት። አርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትም ከመንግሥት በሚያገኘው በጀት ሰፋፊ የምርምር ሥራዎችን ይሠራል።

ነገር ግን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እንደልምድ በዓለም ዙሪያ የሚወጡ ማስታወቂያዎችን እየተከታተለ ማስታወቂያዎቹ የእርሱን የምርምር መስክ የሚመለከቱ ከሆኑ የምርምር ፕሮፖዛል መነሻ ሃሳቦች ይዘጋጃሉ። እነዚህ መነሻ ሃሳቦች ሰፊ ፕሮፖዛል ተደርገውና ተፅፈው ለነዚህ አካላት ይላካሉ። ከተገመገሙ በኋላ ሚዛን የሚደፉ ከሆነ ይመረጣሉ። ሲመረጡ ገንዘብ ይገኛል። በውድድር ሚገኙ የምርምር ሥራ ማስኬጃ ገንዘቦችን ነው ኢንስቲትዩቱ ሲያገኝ የኖረው። ዘንድሮም በርካታ ገንዘብ ከተለያዩ ድርጅቶች አግኝቷል።

ኢንስቲትዩቱ የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ለሃምሳ አራት ዓመታት ዘልቋል። ይሁንና የሚያከናወናቸውን ሥራዎች በመገናኛ ብዙሃን ከማስተዋወቅ አንፃር ሰፊ ሥራ አልሠራም። ይህንን እንደ አንድ ክፍተት በማየትም ነው በምርምር፣ ፈጠራ፣ ልማትና ምርት ለሀገርና ለዓለም እያበረከተ ያለውን አስተዋፅኦ ለመገናኛ ብዙሃንና ለክልል የሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ባለሙያዎች ከሰሞኑ ያስተዋወቀው። የምርምር ተቋማት ከሕዝብ ጋር አብረው ሆነው እንደመስራታቸው ሥራቸውን ለሕዝብ ካላስተዋወቁ ሕዝብ መጠራጠሩ አይቀርም። ስለዚህ የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎችን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ከዚህ ባለፈ አርመማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት የገጠሙት በርካታ ተግዳሮቶች አሉት። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ለምርምር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ እንደልብ አለመገኘት ነው። ስለዚህ በዚህ ዘርፍ ያለውን ክፍተት በማየት ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት ማድረግ ይገባል። በርካታ ያደጉ ሀገራት እዛው ቤተ ሙከራቸው ውስጥ ተቀምጠው የሚፈልጉትን ነገር ያዛሉ። አቅራቢ ኩባንያዎች የሚፈልጉትን ግብዓት ያመጡላቸዋል። ኢንስቲትዩቱም ወደዚህ ደረጃ መድረስ ይገባዋል። የጨረታ ሥርዓቱም ጠንካራ ሊሆን ይገባል። የግዢ ሥርዓቱም የምርምር ተቋማትን ተግዳሮት ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። ስለዚህ ኩባንያዎች የምርምር ግብዓቶች ክፍተት መኖሩን ተገንዝበው የምርምር ግብዓቶችን ማሟላት የሚችሉ ከሆነ የምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ችግር ይፈታል።

ሌላው የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት እየገጠመው ያለው ችግር ገንዘብ ነው። ምርምር ሰፊ ገንዘብ ይፈልጋል። ለምርምር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጣም ውድ ናቸው። እነዚህ ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ ካልተሟሉ የዘረ መል ትንተና ሥራ መሥራት አይቻልም። የክትባት ምርምር ሥራዎችን ማከናወን አይቻልም። የመድሃኒት ምርምር ሥራ መሥራት አይቻልም። የህክምና መገልገያ መሣሪያ ምርምር ሥራ መሥራት አይቻልም። ከዚህ አንፃር ለየትኛው የህክምና ዘርፍ ምርምር ሥራ በቂ ገንዘብ ያስፈልጋል።

ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ከዓመታዊ የተጣራ ገቢያቸው ላይ እስከ 1 ከመቶ ድረስ ለምርምር ሥራ ይመድባሉ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ባለፉት አምስት ዓመት በነበረው መረጃ መሠረት እስከ 0 ነጥብ 6 ከመቶ ያህል ለምርምርና ልማት ሥራ መድቧል። ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር እንደመሆኗና በርካታ የከፍተኛ ትምህርትና የምርመር ተቋማት እንደመኖራቸው ገንዘቡ በቂ አይደለም። ከዚህ አኳያ መንግሥት ለምርምር ሥራ የሚመድበውን ገንዘብ ከፍ ቢያደርግ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል።

ከዚህ ባለፈ በዓለም ዙሪያ ያሉ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ሠራተኞች ስለ ህክምና ምርምር እንዲያስተዋውቁ ኢንስቲትዩቱ ይፈልጋል። የቢዝነስ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ እንደሚሠሩ ሁሉ ምርምርና የሳይንስ ልማት ሀገርን ስለሚቀይር የኢትዮጵያ የምርምር ተቋማት እነርሱ ካሉባቸው ሀገራት ውስጥ ያሉ ተቋማት ጋር አብረው በትስስር እንዲሠሩ መንገድ የሚከፍቱ ከሆነ በዛ ትስስር ውስጥ ሀብት ይገኛል። እነዚህንና መሰል ተግዳሮቶችን ወደ እድል በመቀየር ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ መሥራት የሚቻል ከሆነ ኢትዮጵያ እንድትቀየር ሳይንስና ምርምር ትልቅ መሠረት ይጥላል።

**‹‹ይህ የሃምሳ አራት ዓመት የአርማወር ሀንሰን ምርምር ኢንስቲትዩት ትሩፋት በተለይ በበሽታ ምርምርና ጥናት ዙሪያ የተገኙ ውጤቶች ለኢትዮጵያና ለዓለም መታወቅ ስላለባቸው ይህን የማስተዋወቅ ሥራ ኢንስቲትዩቱ ሠርቷል፡፡››**

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ከመምህርነት እስከ ግዙፉ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ባለቤትነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የተወለደችው በጎጃም ደብረ ማርቆስ ከተማ ሲሆን፣ ያደገችው ደግሞ በአዲስ አበባ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በአዲስ አበባ፣ የከፍተኛ ትምህርቷን በቀድሞ አጠራሩ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ (በአሁኑ ኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርስቲ) እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተከታትላለች።

ወደ ሥራ ለመሰማራትና በሁለት እግሯ ለመቆም ከፍተኛ ፍላጎት ነበራትና የኮሌጅ ትምህርቷን በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በዲፕሎማ እንዳጠናቀቀች ወዲያውኑ የስራውን ዓለም ተቀላቅላለች። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተዘዋውራም ሰርታለች።

ዛሬ ደግሞ አልባሳትን የሚያመርተው የኢቲኤም ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ ናት። የዛሬዋ የስኬት እንግዳችን የሆነችው ይህች ግለሰብ ወይዘሮ መሰረት አውራሪስ ትባላለች።

የወይዘሮ መሰረት የስራ ጥንካሬ የሚጀምረው እንዲህ ነው። ከኮሌጅ በዲፕሎማ እንደተመረቀች ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ አበባ ወጥታ አሰላ ከተማ ላይ ለሁለት ዓመት፣ በአዳማ ከተማም እንዲሁ ለሁለት ዓመት በድምሩ ለአራት ዓመታት በመምህርትነት አገልግላለች። ከአራት ዓመት የመምህርነት ሥራ በኋላም መንግሥታዊ ባልሆነ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅት የመቀጠር ዕድል ያገኘችው ወይዘሮ መሰረት የመጀመሪያ የውጭ ድርጅት ሥራዋን አህዱ ያለችው ስልጤ አካባቢ ነበር።

መንግሥታዊ ባልሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች ለ15 ዓመታት አገልግላለች። በእነዚህ ድርጅቶች የምታከናውነውን ተግባር ውጤታማ ለማድረግ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከአልካን ዩኒቨርሲቲ በሶሺዎሎጂ፣ ሁለተኛ ዲግሪዋን ደግሞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በልዩ ፍላጎት (special need) አግኝታለች። መሰረት ሁለተኛ ዲግሪዋን በተቀበለች ማግስት ትሰራበት የነበረው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የስራ ጊዜው ያበቃል፤ እሷ ግን ሌላ ድርጅት ፍለጋ አላማተረችም፤ በቀጥታ የግል ሥራዋን ለመስራት ማሰብ ጀመረች።

‹‹ምንጊዜም ቢሆን የራሴን ሥራ መስራት እንዳለብኝ አስብ ነበር›› የምትለው መሰረት፤ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥራ በምትሰራበት ወቅት የተለያዩ ቢዝነስ ፕላኖችን ታዘጋጅ ነበር። መጠነኛ ክፍያ በማስከፈል ለተለያዩ ሰዎች ትሰራ የነበረው ቢዝነስ ፕላን ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ አስተዋጽኦ ማድረጉን ገልጻለች። በዚህ ጊዜ ነው እርሷም የራሷን ቢዝነስ ፕላን አዘጋጅታ መስራት እንዳለባት ማሰብ ውስጥ ገባች፤ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት በማሰብ እውን ለማድረግ ማሰብ ጀመረች። ከሰራቻቸው ቢዝነስ ፕላኖች መካከልም የጋርመንት ቢዝነስ ፕላን ውስጧ እንደቀረ ታስታውሳለች።

ትሰራበት የነበረው ድርጅት ሊዘጋ አካባቢ የጋርመንት ሥራ የምትሰራ አንዲት ግለሰብ ለሥራዋ ማስፋፊያ የሚሆን ቢዝነስ ፕላን እንድትሰራላት ትጠይቃታለች። ይህን ጊዜ ነገሮች በልካቸው የተሰፉ ያህል ዕቅድ ተግባር ሊሆን የግድ ሆነ። አጋጣሚው ለመሰረት ምቹና ቀልጣፋ በመሆኑ ቢዝነስ ፕላኑን ስትሰራ የሰበሰበችው መረጃ ዘርፉን ይበልጥ እንድታውቀውና እንድትወደው ዕድል ሰጣት።

መሰረት ብዙ ነገር ለመስራት ያቀደች ቢሆንም፣ ይህን አጋጣሚ ግን ማሳለፍ አልፈለገችም። ውስጧ ስለፈለገው ዕድሉን ለመጠቀም ወስና ዘርፉን ለሚያውቁ ወዳጆቿ አማከረች። ያገኘችው ግብረ መልስም እጅግ አበረታችና ደጋፊ ሆነ፤ የጋርመንት ዘርፉን ለመቀላቀል ማሟላት ያለባትን መስፈርቶች በፍጥነት አሟልታ ጉዞዋን ቀጠለች።

በወቅቱ የስፌት ማሽኖችን ገዝቶ ቤት ተከራይቶ ግብዓቶችን አሟልቶና ሠራተኞችን ቀጥሮ ማሰራት የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ባይኖራትም ከፋይናንስ የበለጠ ወኔና ተነሳሽነት ግን ነበራት።

የጋርመንት ሥራን በፍጹም ፍላጎትና ከውስጥ በመነጨ ተነሳሽነት ለመሥራት የተነሳችው መሰረት፤ መንግሥት አቅም እንደሆናትም አጫውታናለች። ልማት ባንክ ሊዝ ፋይናንስ በሚባል ፕሮጀክት ሥራውን መጀመር የሚያስችል አቅም እንደሚፈጥርላት ተረዳች። ሙሉ አቅሟን አሟጣ ለመጠቀም ከነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ልማት ባንክ የሚጠይቃትን መስፈርት በሙሉ በፍጥነት በማሟላት በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሽኖችን አግኝታለች።



ወ/ሮ መሰረት አውራሪስ

ሁለት ቤተሰቦቿን ጨምራ ኢቲኤም ጋርመንትን አቋቋመች። ለስራ ፍላጎት እንጂ ሙያው ያልነበራት መሆኑን የተረዳችው መሰረት፣ በኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንስቲትዩት በመግባት ለ15 ቀናት መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ስልጠና አግኝታለች።

ስልጠናውን እንደጨረሰች አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር የሚገመቱ 40 የተለያዩ የስፌት ማሽኖችን ከልማት ባንክ ተረከበች። ማሽኖቹን ይዛ ወደ ሥራ የገባችው መሰረት፤ ‹‹ለሥራው አዲስ እንደመሆኔ ሥራ ውስጥ ለመግባት ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፌያለሁ›› ትላለች።

በተለይም ገበያው የሚፈልገውን ከማወቅ ጀምሮ የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ ገበያ ውስጥ ለመግባት ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች። በወቅቱ ለማምረት ያቀደችው የሕጻናት አልባሳት /ማቀፊያ፣ ኮፍያ፣ ካናቴራ፣ ሱሪ፣ ካልሲ/ እና ሌሎችንም በአንድ ጥንድ ለማምረት ነበር። ይሁን እንጂ ወደ ሥራው ስትገባ ጥሬ ዕቃው ብቻ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ ሃሳቧን ለመቀየር ተገደደች።

በዚህም ተስፋ ያልቆረጠችው መሰረት፤ ሌሎች የገበያ ፍላጎቶችን ማማተር ጀመረች። በጥናቷም በትልቁ ገበያ መሀል መርካቶ የሴትና የወንድ የውስጥ ሱሪዎች በስፋት ተፈላጊ መሆናቸውን አረጋገጠች።

እነዚህ የውስጥ ሱሪዎች ከአገረ ቻይና በስፋት ኢትዮጵያ እንደሚገቡ ጠቅሳ፣ ሱሪዎቹን በአገር ውስጥ በተሻለ ጥራት ለማምረት ዝግጅቷን አጠናቅቃ ወደ ማምረቱ ገባች። በዚህ ስራም አንድ ሁለት እያለች 120 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር በሶስት ፈረቃ እያመረተች ገበያውን መቀላቀል ቻለች።

መሰረት በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ኮቪድ 19 ይከሰታል። ይህም አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመግታቱ እንደማንኛውም ሰው የመሰረት ሥራና ማሕበራዊ ሕይወት ጭምር ተናጋ።

ይሁንና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኮቪድን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስን ማምረት የሚችለው ጋርመንት በመሆኑ ችግሩን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክን ጨምሮ የተለያዩ የሕክምና አልባሳትን በማምረት ሥራዋን ማስቀጠል ችላለች።

‹‹የጋርመንት ዘርፍ በቅብብሎሽ የሚሰራ ነው፤ ኮቪድ 19 ደግሞ ንክኪ አይፈልግም። በመሆኑም በወቅቱ ዘርፉ በጣም እየተጎዳ ነበር።›› ያለችው መሰረት፣ በተመሳሳይ ደግሞ ኮቪድ 19ኝን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማምረት የግድ ነበር›› ትላለች። በጥንቃቄ የሕክምና አልባሳትን በማምረት ችግሩን ማለፍ መቻሉን አመልክታለች።

በቫይረሱ ምክንያት ድርጅቱ ሲዘጋ እሷ በተለያዩ የጤና ጥበቃ ቢሮዎች በመሄድ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክን ጨምሮ የሕክምና ባለሙያዎች የሚለብሱትን ሙሉ ልብስ ማምረት እንደምትችል አስረድታለች።

በዚህ ጊዜ የሕክምና ባለሙያዎችን ከራስ ጸጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው የሚሸፍንና ለጥንቃቄ የሚያገለግላቸውን የደህንነት ልብስ ለናሙና ሰርታ አቀረበለች። ልብሱም በየሆስፒታሎቹ በስፋት ተፈለገና 24 ሰዓታት በማምረት ተደራሽ ማድረጉን ተያያዘችው። የአልባሳቱ በከፍተኛ መጠን የመፈለግ አጋጣሚ ችግሩ በተለይም በጋርመንት ዘርፍ ለተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሰፊ የገበያ ዕድል ይዞ የመጣ እንደነበር ነው ያስታወሰችው።

በ2010 ዓ.ም የተቋቋመው ኤቲኤም ጋርመንት ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ በነበረው ኮቪድ 19 ይበልጥ ተነቃቅቶ አሁንም ድረስ የተለያዩ አልባሳትን እያመረተ ይገኛል። በዋናነት ሲጀምር አንስቶ ያመርት የነበረውን የሴትና የወንዶች ጥራት ያላቸውን የውስጥ ሱሪዎች በስፋት በማምረት ከውጭ የሚገባውን መቀነስ ችሏል።

ከዚህ በተጨማሪም ሱፍ ልብሶችን ጨምሮ ቲሸርቶች፣ የአዋቂና የልጆች ቱታዎች፣ ማሊያዎች፣ የጥበቃና የጽዳት ልብሶች፣ የሕክምና፣ የሆቴልና ሌሎች አልባሳቶችንም እንደሚያመርት የጠቀሰችው መሰረት፤ ኢቲኤም ጋርመንት የማያመርተው ምንም አይነት አልባሳት እንደሌሉም ገልጻለች።

ቀደም ሲል ወደ ገበያው በመሄድ ‹‹ምን ይፈልጋል›› በሚል ጥናት በማድረግ ታመርት እንደነበር በማስታወስ፣ በአሁኑ ወቅት ግን በርካታ ደንበኞችን ማፍራት መቻሏን ገልጻለች። ገበያው ወደ ጋርመንቱ እንደሚመጣም ነው ያስረዳችው። እሷ እንዳለችው ከደንበኞቿ የሚደርሷትን የተለያዩ ትዕዛዞች መሰረት በማድረግ እንዲሁም ጨረታዎችን በመሳተፍ አልባሳትን እያመረተች ትገኛለች።

ምርቶቹ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ባሉ ክልሎች እየደረሰ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህም መርካቶ አካባቢ በሚገኙ ነጋዴዎች አማካኝነት በአገሪቱ በአራቱም አቅጣጫዎች ተደራሽ እየሆነ ይገኛል። አልባሳቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች አምስት ኪሎ አካባቢ በሚገኘው የኢቲኤም ጋርመንት ሱቅ እንዲሁም በባዛርና ኤግዚቢሽኖችም ለገበያ ይቀርባሉ።

እሷ እንዳለችው፤ ድርጅቱ ለሚያመርታቸው አልባሳት በሙሉ መቶ በመቶ የጥጥ ጨርቆችን ይጠቀማል። ጨርቆቹም አገር ውስጥ ከሚገኙ ጨርቃጨርቅ አምራች ፋብሪካዎች የሚገኙ ናቸው፤ ሌሎች የጨረታ ሥራዎች ሲመጡም እንደ ትዕዛዙ ከውጭ የሚመጡ ጨርቆችን ከአስመጪዎች እየተረከበች ትሰራለች። ከጨርቆቹ በተጨማሪ ክሮች፣ ማሸጊያዎች፣ ቁልፍ፣ ዚፕና የመሳሰሉት መለዋወጫዎች በሙሉ ከውጭ የሚገቡ ናቸው።

ኢቲኤም ጋርመንት ገበያው የሚፈልገውን ሁሉ የማምረት አቅም ያለው ቢሆንም፣ በቦታ ጥበት በሙሉ አቅሙ እያመረተ አለመሆኑን ወይዘሮ መሰረት ትናገራለች። በቦታ ጥበት ከሥራ ውጭ የሆኑ ማሽኖች እንዳሉም ጠቅሳ፣ በዚህ የተነሳም የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው 120 ሠራተኞች መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑትን ማሰራት እንዳልቻለች አመልክታለች። በአሁኑ ወቅት ለ26 ሴቶችና ለአንድ ወንድ በድምሩ ለ27 ዜጎች ብቻ የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሏን ነው ያስረዳችው።

እሷ እንዳለችው፤ በአሁኑ ወቅት መንግሥት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እየሰጠ ያለው ትኩረት ጥሩ ነው። ያም ቢሆን የጋርመንት ዘርፉ የበለጠ መበረታታትና መደገፍ ያለበት በመሆኑ ከዚህ በበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ኢንዱስትሪዎቹ ጥራት ያላቸውን ምርቶች በስፋት እንዲያመርቱ እንዲሁም ከአገር ውስጥ ባለፈ በውጭ ገበያ ጭምር ተደራሽ መሆን የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅበታል።

መንግሥት ላለፉት አምስት ዓመታት አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከገቢ ግብር ነጻ በማድረግ ትልቅ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል ያለችው ወይዘሮ መሰረት፣ የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንስቲትዩት በበኩሉ ስልጠናዎችን በመስጠት ለዘርፉ ዕድገት ትልቅ እገዛ አድርጓል። አምራች ኢንዱስትሪዎችም በብዙ ተበረታታዋል ብላለች።

የጋርመንት ዘርፍ በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል እና በአብዛኛው ሴቶች የሚሳተፍበት እንደመሆኑ ትልቅ ትኩረት ይፈልጋል ያለችው ወይዘሮ መሰረት፤ እሷም የሥራ ዕድሉን ለሴቶች መስጠቷን ገልጻለች። በተለይ ፋብሪካው በሚገኝበት ሀያት አካባቢ ለሚገኙ ወጣት ሴቶች በሙያው ላይ ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እያሰማራች መሆኗንም ተናግራለች።

ለወጣቶቹ የኪስ ገንዘብ በመስጠት በነጻ ስልጠናውን ትሰጣለች። ወጣቶቹም ባገኙት ስልጠና መሰረት በጋርመንት ውስጥ ከቅንጨባ ጀምሮ እስከ ስፌት ስራ ይደርሳሉ። ይህም አንዱ ማኅበራዊ ኃላፊነትን የምትወጣበት መንገድ እንደሆነ በመግለጽ፤ ሌሎች በጎ ተግባራንም አቅሟ በፈቀደላት መጠን እያደረገች እንደሆነ ነው የጠቀሰችው።

እሷ እንዳለችው፤ ኢቲኤም ጋርመንት የመቄዶኒያ ጎረቤት እንደመሆኑ በመቄዶኒያ ለሚገኙ አረጋውያን የተለያዩ አልባሳትን ያቀርባል። ለአብነትም ድርጅቱ በቅርቡ ከሶስት መቶ ሺ ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው አዳዲስ አልባሳትን በመቄዶንያ ለሚገኙ አረጋውያን አበርክቷል። መንግሥታዊ ለሆኑ ማንኛቸውም ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት አጋርነቱን በተግባር ያሳያል።

ኢቲኤም ጋርመንት በቀጣይ ማስፋፊያ በማድረግ ሥራውን በስፋት ለመሥራት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም ወይዘሮ መሰረት ጠቁማለች። ከጋርመንት ባለፈ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በማቋቋም ለድርጅቷና ለሌሎች ጋርመንቶች ጨርቆችን አምርታ የማቅረብ ሰፊ ዕቅድም አላት። ይህን ዕቅድ ማሳካት እንዲቻልና ኢንዱስትሪው በአገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ እያሳደረ ያለውን በጎ ተጽዕኖ ከፍ ለማድረግ የሁላችንም ጥረት ይቀጠላል ስትልም አረጋግጣለች።

# ነፍሰ ገዳዩ ደፋሪ



አስመረት ብስራት

“በዓለም ዙሪያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሴቶችና ልጃገረዶች የአስገድዶ መድፈር ሰለባ ሆነው ሳሉ ስለዚህ እውነት ዝም ማለት እንዴት እንችላለን?” የሚል ጥያቄ በውስጤ ይመላለሳል። በተለይ የዘንድሮው የ 16 ቀናቱ ዘመቻ መሪ ቃል “ዓለምን ብርቱካናማ እናድርግ፤ በእኩልነት የሚያምን ትውልድ አስገድዶ መድፈርን ይጠየፋል” የሚል ሲሆን በመሪ ቃሉ እንደሰፈረው ከሠብዓዊነት ውጪ የሆነውንና ሴቶች ላይ አካላዊ፣ ሥነልቦናዊ ጉዳትና የማይሽር ጠባሳ የሚያስከትለው አስገድዶ መድፈር መገታት እንዳለበት ሊታመን ይገባል።

በአብዛኛው ሴቶቹ ጥቃት የሚደርስባቸው በሚያምኗቸው ሰዎች መሆኑ ችግሩን አስከፊ ያደርገዋል። ጥቃት ከደረሰም በኋላ በቤተሰቦች በኩል ከማኅበረሰቡ መገለልን በመፍራት፣ በተጠቂዎች በኩል ደፋሪዎች በአብዛኛው የሚያምኗቸው የቤተሰብ አባላት፣ ጎረቤቶች፣ የሃይማኖት አባቶችና የህክምና ባለሙያዎች በመሆናቸው ብናገር ሰው አያምነኝም በሚል ለቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ሳይናገሩ መቅረታቸው፣ አንድም በአጥቂዎች ማስፈራሪያና ዛቻ ስለሚደርስባቸው በቀልን ፍራቻ ዝምታን መምረጣቸው ሪፖርት ለሚደረጉት ጥቃቶች ቁጥር ማነስ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በየእለቱ በተለያየ መልኩ ይህ ጥቃት ቢፈፀምም ተመልክቶ ዝም ከማለት ያለፈ ጥቃትን ቀጥ የሚያደርግ ርምጃ አለመወሰዱ ጉዳዩን አስከፊ አደርጎታል። ስለ ጥቃት በዚህ ልክ ላነሳ የወደድኩት ከአዲስ አበባ ፖሊስ መዝገብ ያገኘሁትን እጅግ አሰቃቂ የሆነ ጥቃት ላካፍላችሁ ስለሆነ ነው። ሰው ሠብዓዊነቱን አጥቶ በደካማ በተለይም ራሷን መከላከል የማትችል አካል ጉዳተኛ ላይ ይህን ያህል ጭካኔ ለማሳደር መድፈሩ እጅግ በጣም ያሳዝናል።

ገና በአፍላ እድሜዋ ማየት የተሳናት ልጅ ለቤተሰብ ሸክም እንደሆነች እየታሰበች በማደጓ ከልክ በላይ የተከፋች ልጅ ነበረች። በእድገቷ ብዙም እንክብካቤ ያልተደረገላት ከመሆኗም ባሻገር ጠባቂ አጥታ ለተለያዩ ጥቃቶች የተዳረገች ልጅ ነበረች። ወጣቷ በተደጋጋሚ በደረሰባት ጥቃት ምክንያት የወንድ ድምፅ ስትሰማ የምትበረግግ አሳዛኝ ፍጥረት ነበረች።

## ምስኪኗ ልጅ

የዛሬ ባለታሪካችን መቀጫ የሻነው ትባላለች። መቀጫ ማየት የተሰናት ወጣት ናት። መኖር ግራ የገባት ቤተሰቦቿ እንደማይፈልጓት የምታሰብ ወጣት ነበረች። ዓይኖቿ ቁልጭ ብለው ቁጭ ቁጭ ከማለታቸው የተነሳ ማየት የተሳናት አትመስልም ነበር። ጠይም የቆዳዋ ቀለም፤ እንደ በረዶ የነጡት ጥርሶቿ፤ ከርደድ ብሎ ጀርባዋ ላይ የወደቀው ጥቁር ፀጉሯ፤ ሁለ መነዋ ቆንጆ የመትባል ለጅ ነበረች። ዓይኖቿ ባለማየታቸው የተነሳ የትምህርት ቤት ደጅን ባትረግጥም ሰዎች የሚያወሩትን ማዳመጥ፤ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ መከታተል የዘወትር ተግባሯ በመሆኑ አእምሮዋ ብሩህ ነበር።

ነገሮችን በቀላሉ የምትረዳ ልጅ ከመሆኗመ በላይ በቻለችው አቅም ሰዎችን ለማስደሰት የምትጥር ተለማማጭ ልጅ ነበረች። በተሰቦቿ በርካታ ልጆች ያላቸው በኢኮኖሚ አቅማቸው ደከም ያሉ ስለነበሩ ብዙም አያስታውሷትም ነበር። ባገኛችው አጋጣሚ ለመታየት ለመስማት ብትፈልግም ነገሬ ያላት ሰውም አልነበረም።

ይህችን ዓይነ ስውር ወጣት ነው እንግዲህ መኖሪያ ቤቷ በመግባት አፏን በጨርቅ ጠቅጥቆ፣ አንገቷን አንቆ በመያዝ የግብረ-ስጋ ግንኙነት በመፈፀም ሕይወቷ እንዲያልፍ ያደረገው ።

“በመጀመሪያ የቤታችንን ውስጥ ሰው ሲገባ እቃ ለመስረቅ የመጣ ሌባ ነበር የመሰለኝ። ከዛ ግን በጭካኔ ሲደፍረኝ ልጅነቴን ሊሰርቅ የመጣ ሌባ መሆኑን አወቅሁ። ከመደፈሬ በላይ ያመመኝ ግን ማየት አለመቻሌን ተገን አድርጎ ማንነቱን እንዳላውቅ ድምጹን ቀይሮ ለአንድ ሰው ብትናገሪ እገድልሻለው ማለቱ ነው።” የምትለው ምስኪን ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመባት አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ግን እስከወዲያኛው እንድታሸልብ አድርጓታል።

ቀድሞ በገጠማት መደፈር ከባድ የሥነልቦና ጉዳት የገጠማት ይህች ልጅ ቁስሏን ለማከም እየጣረች ባለችበት ሰዓት ሌላ ቁስል ተጨመረላት። የሚገርመው ከዚህ ቀደም የተደፈረችው በበተሰቧ እንደሆነ እንደታስብ ያደረጋትን ገጠመኝ ስትናገር “መድፈሩ ሳያንስ ይባስ ብሎም በዚህ እንኳን አገልግይ እንጂ አለኝ። ያኔ ለቤተሰቦቼ የማልጠቅም ሸክም የሆንኩ ስለመሰለኝ በከባድ የበታችነትና የመገፋት ስሜት ውስጥ ነው ያለሁት” ትል እነደነበረ የሚቀርቧት ሰዎች ይናገራሉ።

መጀመሪያ ገና በአስራ አንደ ዓመቷ ከተደፈረች በኋላ ወንድ ሲነካት እጅግ በጣም ትፈራ ነበር። አንድ ጊዜ አሟት ሀኪም ቤት ሄዳ ዶክተሩ ለምርመራ ቲሸርቴን ከፍ ሲያደርገው ተንቀጥቅጣ እንደነበረ አብረዋት የነበሩት በትዝታ ያወራሉ። ቁስሏ ሙሉ በሙሉ አልዳነም ነበርና እግር ከወርች ያሰራት ስጋት ሲያስቃያት ቆይቷል። የጠሉት ይወርሳል ፤ የፈሩት ይደርሳል የሚሉት ነገር ደርሶባት ነው መሰለኝ፤ አሁን ባላሰበችው አጋጣሚ ሕይወቷን ከፍላለች።

ገና በጠዋቱ የእድሜ መጀመሪያ ላይ እሷ እንደምታሰበው በቅርብ ሰው ተደፍራ ፍዷዋን ስትበላ የቆየችው ልጅ ይባስ ብሎ ብቻዋን በተቀመጠችበት ቤት ማንነቱ ያልታወቀ ግለሰብ ገብቶ ሕይወቷን አጠፋው።

## ሞገስ ደሳለኝ

ሞገስ ያደገበት ቤት ለሴት ልጅ ክብር የማይሰጥ ሴት ልጅን እንደተናቀች አድርጎ የሚያስብ ማህበረሰብ ውስጥ ነበር። እሱ እንደሚያስበው የሴት እንቢታ መግደርደር እንጂ አለመፈለግ ነው ብሎ አያስብም ነበር።

“ወንዶች ስሜታቸውን መቆጣጠር አይችሉም”፣ ሴት ልጅ እንቢ ስትልህ መግደርደር ነው” “መጠጥ ጠጥታ ነበር፣ ማን ስከሪ አላት” የሚሉ አስገድዶ መድፈርን እንደ ቀላል እና የተለመደ ነገር የሚቆጥሩ አባባሎች ሲሰማ ያደገው ወጣት ሴትን ልጅ እንደፈለገ የማድረግ መብት ያለው መሆኑን ያስባል። ማኅበረሰቡ ወንድነትን ከሃይለኛነት፣ የፈለጉትን ከማድረግ፣ ከቁጣ እና ከጉልበተኛነት ያዛመደበት የ “ወንድነት” ትርጉምም በደፋሪነት አስተሳሰብ ውስጥ ከቶ እንደልቡ እያደረገ እንዲቀይ አድርጎታል ።

ከዚህ በፊት በፈፀማቸው ጥቃቶች ሳይያዝ ቆይቷል። በሕግ አስፈፃሚዎች እና በህክምና ባለሙያዎች ሳይቀር ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶችና ልጆች በአግባቡ ባለማስተናገዳቸው የተነሳ ተጠቂዎችም የሕግ ድጋፍ ሳያገኙ እሱም በቁጥጥር ስር ሳይውል ቆይቷል።

በአሁኑ ግን ድምፁን አጥፍቶ መኖሪያዋ ቤት ገብቶ አለማየቷን በመጠቀም ሊደፍራት የሞከረው ወጣት ያላሰበው ተከሰቶበታል። ወጣቱ እንደለመደው አድብቶ ከሟች መኖሪያ ቤት በመግባት አፏን በጨርቅ ጠቅጥቆ፣ አንገቷን አንቆ በመያዝ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሲፈፅምባት በመታፈናና በመታነቋ የተነሷ ሕይወቷ ሊያልፍ ችሏል።

ሕይወቷ ማለፉን የተረዳው ልማደኛ ደፋሪ በድንጋጤ ሲደነባበር ነበር ወደ መኖሪያ ቤቱ ከመጡ የጎረቤት ሰው ጋር የተገናኙት። ቤት ወስጥ የተገኘው ሰው ሁኔታው ያላማራቸው ሰው ግራ የተጋባውን ጎረምሳ ጮኸው በአካባቢው ሰዎች በማሲያዝ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለከቱ ዓይነ ስውሯ ወጣት እርቃኗን ተዘርግታ ይመለከታሉ። ያኔ ፖሊስ ተጠርቶ በቁጥጥር ስር እንዲውል አደረጉት።

## የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ የጀርባ ታሪኩን ማጥናት ጀመረ። መሬት ላይ ወድቃ ያገኛትን ወጣት አንስቶ ሆስፒታል ቢያደርሳትም በሕይወት ሊያቆያት አልቻለም። ወጣቷ በአሳዛኝ ሁኔታ ሕይወቷ ማለፉን ከተረዳ በኋላ የተለያዩ ምርመራዎችን ማድረግ ጀመረ።

ወጣቷ በመታፈኗ ምክንያት ህይወቷ ከማለፉም በተጨማሪ ተገዳ መደፈሯንም የሚያመለክት ምርመራ ወጤት ተገኘ። የምርመራ ውጤቱን የያዘው ፖሊስ የዓይን እማኝ ባለማግኘቱ የተነሳ ከተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃል ለመቀበል ወደ ማረሚያ ቤት ተመለሰ።

በምርመራ ክፍሉ ውስጥ የተፋጠጡት ፖሊስና ተጠርጣሪው አተካራ ገጥመዋል። ተጠርጣሪው ምንም አላደረኩም ቢሊም ፖሊስ የአንተ ዐሻራና የዘር ፍሬ በሰውነቷ ላይ ተገኝተዋል፤ ብታምን ይሻላል በሚል ብዙ ከተከራከሩ በኋላ ነበር የእምነት ክህደት ቃሉን የሰጠው።

ከዚህ በፊት በርካታ ሴቶችን እንዲህ ማደረጉን ማስረጃም ስላልተገኘበት ሳይከሰስ መቅረቱን ፖሊስ በምርመራው አገኘ። ይህን የለመደ ወንጀለኛ በአግባቡ ቅጣቱን ያገኝ ዘንድ በቂ ምርመራ በማድረግ ማስረጃውን አጠናቅሮ በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ቀረበ።

## የአቃቤ ህግ ክስ ዝርዝር

ጉዳዩ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶ በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕ/አ/620/2/ሀ/ እና /3/ መሠረት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር እንደቀረበው ሞገስ ደሳለኝ የተባለ ተከሳሽ ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 1፡30 ሲሆን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ሽሮ ሜዳ አዲስ ተስፋ ትምህርት ቤት አካባቢ የ 14 ዓመት የሆነችውን የግል ተበዳይ የምትኖርበት መኖሪያ ቤት በመግባት በጥፊ በመምታት፣ እንዳትጮህ አፏ ውስጥ ጨርቅ በመጠቅጠቅ እና አንገቷን በሁለት እጁ አንቆ በመያዝ በኃይል የግብረ-ስጋ ግንኙነት የፈጸመባትና አፏ ውስጥ ጨርቅ በመጠቅጠቁ እና አንገቷን በማነቁ ምክንያት ትንፋሽ አጥሯት ሕይወቷ እንዲያልፍ በማድረጉ በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋሉ ተመልክቷል።

በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶ በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕ/አ/620/2/ሀ/ እና /3/ መሰረት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ የመከላከያ ምስክሮችን ያሰማ ቢሆንም የቀረበበትን ክስ ሊከላከል ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

**ተከሳሹ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ የቆየ ሲሆን በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ የመከላከያ ምስክሮችን ያሰማ ቢሆንም የቀረበበትን ክስ ሊከላከል ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት በ19 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በ"ፈረንጆች" አቆጣጠር የሚዛቡ መረጃዎች

ዋለልኝ አየለ

በዓለም አቀፍ መጠሪያው "ግሪጎሪያን ካላንደር" ይባላል። በኢትዮጵያ ግን በተለምዶ "በፈረንጆች አቆጣጠር" ሲባል በመደበኛ አገላለጽ ደግሞ "እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር" ይባላል። ሁለቱም ግን አይገልጹትም። ዓለም አቀፍ የቀን አቆጣጠር ስለሆነ በአውሮፓውያን አይወሰንም። ዳሩ ግን የፈለሰፉትና የጀመሩት አውሮፓውያን ስለሆኑ በእነርሱ ስም መጥራታችን ስህተት አይሆንም። አውሮፓውን ነጮችን "ፈረንጅ" እያልን ስለምንጠራ በተለምዶ "የፈረንጆች አቆጣጠር" እያልን እንጠቀመዋለን። ይህ ሁሉ የሆነው ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ስላላት ያን ያህልም የአውሮፓውያኑ ላይ ትኩረት ስለማይደረግ ነው።

ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ቢኖራትም ዘመኑ የቴክኖሎጂ ነውና በዕለት ከዕለት ክንውኖቻችን ውስጥ የአውሮፓውያኑን የዘመን አቆጣጠር ለመጠቀም እንገደዳለን። ዛሬ ላይ ሁሉም ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ‹‹ስማርት›› ስልክ የሚጠቀም ሁሉ ቀን እና ሰዓቱን የሚሞላው በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ነው። በተለይ ሰዓት ወደ ኢትዮጵያ እየተረጎምን ነው የምንጠቀመው። ለምሳሌ፡- ጠዋት 9፡00 (AM) ከሆነ 3፡00 ብለን እንናገራለን ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ከዘመናት በኋላ የኢትዮጵያው አቆጣጠር የመረሳት ዕጣ ፋንታ እንደሚገጥመው ለመገመት ቀላል ነው።

ለጊዜው ግን አንድ ልብ ያልተባለ የሚመስለኝ ነገር በፈረንጆቹ አቆጣጠር የሚዛቡ መረጃዎች ናቸው። መረጃዎቹ የሚዛቡት የፈረንጆች ስለሆነ ወይም አቆጣጠሩ ችግር ኖሮበት ሳይሆን ከአጠቃቀም ችግር ነው። በተለይም በማሽን በሚሰሩ መረጃዎች ሰዎች በግደለሽነት በሚሰሯቸው ስህተቶች ነው። ቀላል ምሳሌ ላንሳ።

ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት በቁጥር ሲቀመጡ በብዛት ከትንሹ ወደ ትልቁ ነው። ይሄ ማለት መጀመሪያ ቀን፣ ከዚያ እዝባር ተደርጎ ወር፣ እዝባር ይዘጋና ዓመተ ምህረቱ ይቀመጣል። ወር በእዝባር ውስጥ ይሆናል ማለት ነው። አልፎ አልፎ ደግሞ ከትልቁ ወደ ትንሹ ሊደረግ ይችላል። ይሄ ማለት ዓመተ ምህረት፣ ከዚያ ወር፣ መጨረሻ ላይ ቀን ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን መረሳት የሌለበት ነገር በቅደም ተከተል መሆኑን ነው።

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ስህተቶች የሚፈጸሙት። አንዳንድ መረጃዎች ላይ ተዘበራርቆ ይቀመጣል። ይህ የሚያጋጥመው በቁጥር ሲቀመጥ ነው። የወሩን ስም በመጻፍ ከሆነ ችግር የለውም። በቁጥር ሲቀመጥ ግን ስህተቶች የሚፈጠሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለምሳሌ፤ በትልልቅ የሸቀጣሸቀጥ መደብሮች (ሱፐር ማርኬት) እና በብዙ የግብይት ቦታዎች ላይ ደረሰኝ ሲቆረጥ ቀኑ ተዘበራርቆ ይጻፋል። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

07/06/2024 ይህን መረጃ የተመለከተ ሰው ጁን (ሰኔ) 7 ቀን 2024 ብሎ ነው የሚረዳው። ምክንያቱም በብዛት የተለመደው ከትንሹ ወደ ትልቁ ነው፤ ከቀን ወደ ወር፣ ከወር ወደ ዓመተ ምህረት ማለት ነው። አልፎ አልፎ ከትልቅ ወደ ትንሽ ይደረጋል፤ እንደዚያ እንዳይገምት ደግሞ ዓመተ ምህረቱ መጨረሻ ላይ ይታያል። ዓመተ ምህረቱ ባለ ብዙ ዲጂት ስለሆነ ከቀን እና ወሩ ጋር አያምታታም። ለማሳጠር 24 ተብሎ ከተቀመጠ ግን እሱም ከቀን ጋር ሊያምታታ ይችላል። ለምሳሌ ከዓመታት በፊት 11/10/12 ተደርጎ የተቀመጠ መረጃ ብናገኝ የትኛው ቀን፣ የትኛው ወር፣ የትኛው ዓመተ ምህረት እንደሆነ አይታወቅም።

> የወሩን ስም በመጻፍ ከሆነ ችግር የለውም። በቁጥር ሲቀመጥ ግን ስህተቶች የሚፈጠሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው

ይህ መረጃ በብዙ ዓይነት አማራጭ ሊያሳስተን ይችላል። ኦክቶበር (ጥቅምት) 11 ቀን 2012 መሆን ይችላል። ወሩን አስቀድመው ከጻፉት ዴሴምበር (ታህሳስ) 10 ቀን 2012 መሆን ይችላል። ዓመተ ምህረቱን አስቀድመው ከጻፉት ጥቅምት 2011 ወይም ታህሳስ 2011 መሆን ይችላል። ዓመተ ምህረት መሃል ላይ ማድረግ አልፎ አልፎም ቢሆን የተለመደ ስላልሆነ ቢያንስ እሱን እንለፈው።

ስለዚህ ከላይ የገለጽኩት 07/06/2024 የሚለው መረጃ ቀኑን አስቀድመው ከጻፉት ጁን (ሰኔ) 7 ቀን 2024 መሆን ይችላል። ወሩን አስቀድመው ከጻፉት ጁላይ (ሐምሌ) 6 ቀን 2024 መሆን ይችላል።

ይህ የመደናገር ችግር የሚፈጠረው ከወራት ወይም ከዓመታት በኋላ ስናየው ነው። ለምሳሌ፤ ደረሰኝ ከሆነ በተጻፈበት ቀን ካየነው የዕለቱን ቀንና ወር ስለምናውቀው አንቸገርም። ከወራት በኋላ ካየነው ግን ተዘበራረቀ ማለት ነው። መረጃው የግድ አስፈላጊ ቢሆን ተቸገርን ማለት ነው። ከደረሰኝ ያለፈ ሌሎች የታሪክና የሌሎች ሰነዶች መረጃዎች ቢሆኑ የተሳሳተ ሁነት ተመዘገበ ማለት ነው።

ይህ ሁሉ እንዳይሆን ወጥ የሆነ ልማድ ቢኖር ጥሩ ነበር። በማሽኖች ላይ ለማሳጠር ሲባል በቁጥር ይቀመጣል፤ በሌሎች ሰነዶች ግን ወሩ በስም ቢጻፍ ይሻል ነበር። ለምሳሌ ዛሬ በአውሮፓውያኑ ቀኑ ጁን (ሰኔ) 15 ነው። ጁን 15 ቀን 2024 ተብሎ ቢቀመጥ ግልጽ ይሆናል ማለት ነው። ከ15 እና 24 ወር ስለማይሆኑ ይህኛው ቀላል ሊሆን ይችላል። ከጁን 13 በፊት በነበሩት ቀናት ቢሆን ግን 12/06/24 ተብሎ የተጻፈው ያሳስታል ማለት ነው።


ስለዚህ ቢቻል ወሩ በስም ቢጻፍ፤ ቦታ ለመቆጠብ ሲባል በቁጥር ሲጻፍ ግን ብዙዎች በሚገምቱት ቅደም ተከተል (ከትንሹ ወደ ትልቁ ማለት ነው) ቢጻፍ መረጃ እንዳይዛባ ያደርጋል። ይሄ ማለት መጀመሪያ ቀኑን፣ በእዝባር ውስጥ ወሩን ማድረግ ማለት ነው።

የፈረንጆች አቆጣጠር ላይ ያተኮርኩት በተለይም እንደ ደረሰኝ ማሽን አይነት የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚሰሩት በዚህኛው ስለሆነ ነው። የኢትዮጵያ አቆጣጠር የሚያገለግለው በሰው በሚጻፉ ነገሮች (በኮምፒተርም ቢሆን) ስለሆነ አስቦ ለመጻፍ ዕድል አለው። ያም ሆኖ ግን የኢትዮጵያው አቆጣጠር ላይም የዚሁ አይነት ስህተቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ደብዳቤዎች ላይ "ቀን" ተብሎ እዝባር እየተደረገ ይጻፋል። የዛሬ ደብዳቤዎች ከዓመታት በኋላ የታሪክ ሰነዶች ናቸውና ቀን እና ወር ሊዘበራረቅ ይችላል ማለት ነው።

ለምሳሌ ዛሬ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሰኔ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ነው። ይህ ቀን በደብዳቤ አናት ላይ ወይም በሌላ ሰነድ ላይ 08/10/16 ተብሎ ተጻፈ እንበል። የኢትዮጵያ አቆጣጠር ላይ ብዙ ጊዜ ከቀን ወደ ወር እና ወደ ዓመተ ምህረት የሚጻፈው በቅደም ተከተል ነው። በማሽን የፈረንጆቹ አቆጣጠር ላይ የለመደ ሰው ግን ከላይ እንደገለጽነው ወሩን ወይም ዓመተ ምህረቱን እያስቀደመ በብዙ መንገድ ሊደናገር ይችላል ማለት ነው። ስለዚህ ቢቻል ወሩ በስም ቢጻፍ፣ ዓመቱ ምህረቱም ሙሉውን ቢቀመጥ (2016 ተብሎ) ይሻላል። የሁለት ዲጂት መቅረት የሚቆጥበው ጊዜና ቦታ የት ያደርሳል?

በአጠቃላይ የዛሬ ሁነቶች የነገ ሰነዶች ናቸውና ነገ በማያስቸግር መንገድ ቢቀመጡ እንላለን።

# ዓለም አቀፍ



## "የአረፋ ኹጥባ" አማርኛን ጨምሮ በ20 ቋንቋዎች እንደሚተረጎም ተገለጸ

### - የ1445ኛው የሃጅ ሥነ ሥርዓት ትናንት በይፋ ተጀምሯል

በጋዜጣው ሪፖርተር

"የአረፋ ኹጥባ" አማርኛን ጨምሮ በ20 ቋንቋዎች እንደሚተረጎም ተገልጿል፡፡ የ1445ኛው የሃጅ ሥነ ሥርዓት በትናንትናው ዕለት በሳዑዲ አረቢያ መካ በይፋ ተጀምሯል።

በዳሁል ሂጃህ ወር ከሚከናወነው የሃጅ ሥነ ሥርዓት ውስጥ በ9ኛው ቀን የሚፈጸመው "የአረፋ" ሥነ ሥርዓት አንዱ ነው።

ታዲያ ይህ "የአረፋ ኹጥባ" "ሥነ ሥርዓት ዘንድሮ በመላው ዓለም ብዙ ተናጋሪ ባላቸው 20 ቋንቋዎች እንደሚተረጎም የሁለቱ ቁዱሳን መስጊዶች አስተዳደር ሃራማይን ሸሪፈይን አስታውቋል።

በአረብኛ ቋንቋ የሚከናወነው የአረፋ ኹጥባ በመላው ዓለም ብዙ ተናጋሪ ባላቸው 20 ቋንቋዎች በመተርጎምም በዓለም ዙሪያ ለ1 ቢሊዮን ሰዎች እንዲደርስ እንደሚደረግም ተገልጿል።

የአረፋ ኹጥባ ተተርጉሞ ከሚተላለፍባቸው ቋንቋዎች መካከል አማርኛ ቋንቋ አንዱ እንደሆነም ተነግሯል።

በተጨማሪም የአረፋ ኹጥባ በእንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይና፣ ማላይ፣ ኡርዱ፣ ፋርሲ፣ ቻይኒዝ (ማናዳሪን)፣ ቱርኪሽ፣ እና የሩሲያኛ ቋንቋዎች እንደሚተረጎም ታውቋል።

እንዲሁም፣ ሃውሳ፣ ቤንጋሊ፣ ስዊድሽ፣ ስፓኒሽ፣ ሳዋሂሊ፣ ጣሊያንኛ፣ ፖርቱጋልኛ፣ ቦስኒያን፣ ማላያላም፣ ፍሊፒኖ እና ጀርመንኛ ቋንቋዎችን ይተረጉማል ነው የተባለው።

ከ7 ዓመት በፊት የተጀመረውና በአረብኛ ቋንቋ የሚከነወነው የአረፋ ኹጥባ በመላው ዓለም ብዙ ተናጋሪ ባላቸው ቋንቋዎች ተተርጉሞ እንዲተላለፍ ሲደረግ ይፍ ለሰባተኛ ጊዜ እንደሆነም ነው የተገለጸው።

የ1445ኛው የሃጅ ሥነ ሥርዓት በትናንትናው ዕለት በሳዑዲ አረቢያ መካ በይፋ ተጀምሯል። ትናንት ምሽት ላይም ሀጃጆች ወደ ሚና ጉዞ ይጀምራሉ ተብሏል።

ዓመታዊውን የሀጅ የጸሎት ሥነሥርዓት ለመታደም ከ1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ሀጃጆች መካ ከትመዋል። በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ ሙስሊሞች የሚታደሙት ዓመታዊ ሥነሥርዓት በሃይማኖቱ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው።

እስልምና ከሚያዛቸው 5ቱ መሰረታዊ ሃይማኖታዊ ግዴታዎች መካከል አንዱ እንደሆነም ይነገራል።

የአረፋ ኹጥባ ብዙ ተናጋሪ ባላቸው 20 ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለ1 ቢሊዮን ሰዎች እንዲደርስ ይደረጋል ተብሏል፡፡

## ችሎት ውስጥ ዳኛ ላይ ተኩስ የከፈተው ፖሊስ ተገደለ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አንድ ከፍተኛ የኬንያ ፖሊስ በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ በሚገኝ ፍርድ ቤት ውስጥ ዳኛ ላይ ከተኮሰ በኋላ መገደሉን ቢቢሲ ዘግቧል።

እንደዘገባው ከሆነ ዋና ኢንስፔክተሩ የማካድራ ዋና ዳኛ በሆኑት ሞኒካ ኪቩቲ ላይ የተኮሱት ዳኛዋ የፖሊሱ ባለቤት በተከሰሱበት ጉዳይ ውሳኔ ካሳለፉ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ነው።

እኝህ ፖሊስ የተናደዱት ዳኛዋ የባለቤታቸውን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸው ነው ተብሏል።

በምዕራብ ኬንያ ሎንዲያኒ ውስጥ የሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ኃላፊ የሆኑት ሳምሶን ኪፕቺርቺር ኪፕሩቶ የተባሉት ፖሊስ ጠብመንጃ በማውጣት ወደ ዳኛዋ ተኩሰው እግራቸውን አቁስለዋል።

በችሎቱ ውስጥ ያሉት ሌሎች ፖሊሶች ወዲያውኑ የአጸፋ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ ከፖሊሶቹ ውስጥ አንደኛው ጥቃት አድራሹን ተኩሶ ገድሏል።

በዚህ ግጭት ሶስት ፖሊሶች የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ፖሊስ ባወጣው ሪፖርት አስታውቋል።

ዳኛዋ እና የቆሰሉት ፖሊሶች ሆስፒታል ውስጥ ህክምና እየተደረገላቸው ነው ተብሏል።

ፍርድ ቤቱ ባወጣው መግለጫ ፍርድ ቤቱ ዋስትና ተስጥቶት ለቀረ እና ለቀረበት ምክንያት በቂ ማብራሪያ ማቅረብ ያልቻለ ግለሰብን ዋስተና ይሰርዛል ብሏል።

ፍርድ ቤቱ "ይህ ውሳኔ ይፋ እንደተደረገ ሰውየው (ፖሊሱ) ወደ ዳኛዋ ተኩሶ ጭኗን አቁስሏል"ብሏል በመግለጫው።

መጀመሪያ ላይ በወጣው ሪፖርት "ተኩስ የከፈተው ተጠርጣሪዋን ያገባው የፖሊስ ባልደረባ ነው" ሲል አመልክቷል።

የብሔራዊ ፖሊስ አገልግሎት እንደገለጸው፤ ፖሊሱ "ባልታወቀ ምክንያት" ወደ ችሎት ገብቷል። ተኩስ እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑ ሁነቶችን ለማወቅ ምርመራ እየተካሄደ መሆኑን አገልግሎቱ ጨምሮ ገልጿል።

በችሎት ውስጥ የተፈጸመው ይህ ክስተት እንዴት ሊሆን ቻለ በሚል ብዙ ኬንያውያን አስደንግጧል።

ፖሊስ ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውጪ የሆነ ግድያ በመፈጸም ቢከሰሰም ፍርድ ቤት ውስጥ እንዲህ አይነት ክስተት እስካሁን አላጋጠጠም። ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ደህንነት ለማስጠበቅ ጥበቃዎችን የሚያጠናክር መሆኑን ገልጿል።

# የአብሮነት ምኩራብ ያስፈልገናል

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አሪታዊው ታራ በካራን የሚኖር ጣኦት አምላኪ ነበር። በቤቱም ለእውነትና ለክብር የሚሆን ስፍራ አልነበረም። ከሁሉም ትልቁን እውነት አጥቶ በማይረባ ሀሳብ የማይረባ ሆኖ የሚኖር ሰው ነበር። የእኛን ከሰላምና ከአብሮነት የራቀ አካሄድ ከዚህ ሰው ታሪክ ጋር አዛምጄ እስከመቼ በታራ ቤት ስል መጣሁ።

ሰው የሕልሙ ፈጣሪ እንደሆነ በርካታ ጠቢባን ይናገራሉ። በዚያው ልክ ሰው የመከራው ፈጣሪም እንደሆነ የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። ሀገር በዜጎች ሀሳብ፣ በትውልድ የበጎነት ስንቅ እንደምትፈጠር ሁላችንንም የሚያግባባ የጋራ መረዳት አለ። በዚህ መረዳት ውስጥም ከዓለም የገዘፈች፣ ከሰው ልጆች የበረታች ኢትዮጵያ የምትባልን ሀገር ፈጥረን እናውቃለን። ከትላንት መለስ ብለን አሁንን ስንቃኝ ግን ትግላችን እንደበፊቱ ለአብሮነት ሳይሆን የብቻ ቤትን ለመስራት የምንፈራገጥ ነው የሚመስለው። ደግሞም እውነት ነው ተንፈራግጠን ከአምና የተለዩ መልከ ውይብ ማንነትን ፈጥረናል።

እኛስ እስከመቼ በሞትና ጦርነት ውስጥ እንኖራለን? መቼ ነው ማብቂያችን? መቼ ነው እንደአብርሃም መጥፎውን ትተን ወደመልካሙ ስፍራ የምናቀናው? ለምንድነው ከንቱ ድካም የማይደክመን? የሕይወት ፈተናዎች ካለመግባባትና ከእርስ በርስ ግጭቶች የሚነሱ ናቸው። ይሄን ሀሳብ አጽንኦት ለመስጠት በሀገራችን የተነሱትን የዜጎች መፈናቀል፣ ስደት፣ ርሀብ፣ ተረጂነት፣ የኑሮ ውድነት፣ የስጋት እንቅስቃሴ፣ የጸጥታ ችግር ሌላም ሌላም መጥቀስ ይቻላል። እኚህ ማኅበራዊ ፈተናዎች ባለመግባባትና ቁጭ ብሎ ባለመነጋገር ጦርነት መር በሆነ አስተሳሰብ የተፈጠሩ ስለመሆናቸው የማይረዳ የለም።

የበላይነት በሚንጸባረቅበት የአሸናፊነት መንፈስ ውስጥ ያለንን ከማጣትና ከመጣል ባለፈ የተቀዳጀነው ድል የለም። ዛሬም ድረስ የትላንትና የከዛ ወዲያ የአፋችንን ፍሬ እየበላን ነው። ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ውስጥ እንደሆኑ ታላቁን መጽሀፍ ቅዱስ ጨምሮ የተለያዩ የእውቀት አፎች ይነግሩናል። ግን አውቀንና ተረድተን ራሳችንን ከስቃይ ትውልዱንም ከጥላቻ አልታደግነውም።

ወደመፍትሄአቸው ስንመጣ የምናገኘው አንድ የድህነት አቅጣጫን ነው። እርሱም በመነጋገር አብሮነትን ማስቀጠል የሚለው ነው። ያሸነፍንባቸውም ሆኑ የተሸነፍንባቸው የወንድማማች ግፊያዎች ዛሬ ላይ ማናችንም ከፊት አላቆሙንም። አቁመውናል? ስለእውነት እናገራለው አላቆሙንም። ይልቅ ማንም ያልከፈለውን የመከራና የስቃይ ዋጋ እያስከፈሉን ነው። አሁናዊ ስቃዮቻችን፣ አሁናዊ መለያየቶቻችን አሸናፊና ተሸናፊ በሌለው የእርስ በርስ ግጭቶታችን የመጡ ናቸው።

ሀገርን መታደግ ሕዝብን መታደግ ነው። ሕዝብን መታደግ ደግሞ ትውልድን መታደግ ሆኖ ከፊት የሚመጣ ነው። እኚህ ሁሉ ልዩ መሳይ አንድ አይነት መልኮች ወደቀደመ ኢትዮጵያዊ መልክና ክብራቸው እንዲመለሱ ሄደን ሄደን የምንወድቅበት ሳይሆን ሄደን ሄደን የምንደርስበት የአብሮነት ምኩራብ ያስፈልገናል። ይሄ እንዲሆን ሀገር ባቀና የጨዋነትና የአንተ ትብስ ልማዳችን ተረከዝ እስከመያዝ በሚያደርስ የክብር መንፈስ ውስጥ በመነጋገር ወጥተን የምንገባበት የእርቅና የተግባቦት እውቀት ያስፈልገናል።

እንዲህ ካልሆነ የምንደርስበት ሩቅ የለም። እንዲህ ካልሆነ የምንደርስበት ህልምና ራዕይ የለንም። ፍቅርና አንድነትን ባጎደለ ምኞትና ሕልም ውስጥ የሚመጣ የተሀድሶ ለውጥ የለም። ሀገራዊም ሆኑ ግለሰባዊ ለውጦች በፍቅር ጀምረው በአንድነት የሚያበቁ ናቸው። ተለያይተንና ተራርቀን ንፋስ የገባባቸው ቀዳዳዎቻችን እንዲጠቡ የፍቅር አፎችና የእርቅ አንደበቶች ያሹናል። እንዴትም ብናስብ እንደ

**ብሄራዊ ምክክሩን ከሀገራችን አልፈን አውዱን አፍሪካዊ ለማድረግ እየተሰራም እንደሆነ ከኮሚሽኑ በኩል የተሰማ ሰሞነኛ መግለጫዎች ያሳያሉ**

እኛ የተቀራረበ ሕዝብ የለም። የታሪኮቻችን መነሻና መድረሻ የአብሮነት ደማቅ ስምን የታከኩ ናቸው።

ከስልጣኔና ከዘመናዊነት ጋር የተያያዘ አንድ ድንቅ ጥበብ አውቃለው..‹ጊዜ የሰውን ልጅ አይቀይረውም› የሚል። ይሄን እውነት ለመረዳት ዝግ ማለት ግድ ይሆናል። በአሁኑ ሰዓት ዓለም በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ጽንፎችን የምታራምድ ናት። ሰው እንደተረዳው ነው። ማንነቱ፣ ታሪኩ፣ ሕይወቱ፣ ሕልሙ ሳይቀር ይሄን እውነት ተደግፎ የቆመ ነው። ምን ለማለት ፈልጌ ነው.. በየትኛውም የሕይወት መንገድ ላይ በጽናትም ሆነ በእንግድጋዴ የምንራመደው በገባን ልክ ነው።

ብዙዎቻችን ዘመንን በተመለከተ ሁለት አይነት አረዳድ አለን። ‹ጊዜ የሰውን ልጅ ይቀይረዋል› የሚልና ‹የሰው ልጅ ጊዜን ይገዛዋል› የሚል። በምንም የሕይወት ደረጃ ላይ እንሁን ሁላችንም ከዚህ እውነት ጀርባ የቆምን ነን። ከሁሉም የሚልቀው እውነት ጊዜ በሰው ልጅ ቁጥጥር ስር ነው የሚለው ነው። ይሄ እውነታ የገባቸው በጊዜ ውስጥ የሚቀይሩት ታሪክ፣ ማንነት፣ ባህል፣ ስርዐት የላቸውም። ማንነታቸውን ተቀብለው ወደፊት የሚራመዱ እግረ ለሞች ናቸው። ይሄ እውነታ ያልገባቸው ግን ትላንትን እየናቁ ዛሬን የሚያደንቁ፣ ታሪክና ማንነታቸው ኋላ ቀር እየመሰላቸው ምንም ባላወቁትና ባልተረዱት የሚደናበሩ ናቸው።

ይሄን እውነት ወደእኛ ስናመጣው ብዙ የትዝብት አክርማን መምዘዝ እንችላለን። ዓለም በሌለው ክብርና ነጻነት ውስጥ የቆምን፣ የሰላምና የአብሮነት ደሴት ተብለን የተደነቅን ሕዝቦች ስለምን ዛሬ ሌላ ሆንን? ከኢትዮጵያዊነት ውጪ ሌላ የማናውቅ፣ ተጨማሪ ስምና መጠሪያ የሌለን ሕዝቦች ዛሬ ስለምን በማይረቡ እልፍ ስሞች ተከበብን? ተመካክሮ በጥቅምት እኩሌታ ወራኢሉ የከተመ፣ ተግባብቶና ተስማምቶ በአጋዴንና በካራማራ የቆመ ሕዝብ ስለምን ዛሬ ሰላም ራቀው? ባህር ማዶ ተሻግሮ ስለሌላው ሰላም የሞገተ፣ ስለሌላው ነጻነት የተከራከረ ሕዝብ ስለምን ሰላም ናፋቂ ወጣው? ሊቀ ነብያት ሙሴን ያበረቱ ዮቶራዊ አፎች፣ የግሪክ ጸሀፍቶች በድርሰቶቻቸው ያሞካሿት ኢትዮጵያ ስለምን ዛሬ ክብር ራቃት?

“ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይቀይርም “ሲል አምላክ በቃሉ ያወሳት ምድር፣ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሄር ትዘረጋለች ሲል የእምነቷን አጽናፍ የመሰከረ ቅዱስ አፍ ዛሬ ስለምን እንዳልነበረች ሆነች? ስለሀገሬ ጥቂቱን ተናገርኩ እንጂ ጥንተ ብኩርናዋንና ገናናነቷን የሚናገሩ እልፍ የታሪክ ሰነዶች አሉ። ዛሬ ለምን ምንም ሆንን? ስለምን ቀለልን? ስለምን ከክብራችን ተንሸራተትን?

ጥያቄዎቻችን ወደ አንድ አቅጣጫ ነው የሚመሩን..የጥንቱን ባህል ስለመሳት፣ መጤ በሆኑ አጉል አስተሳሰቦች ስለመወሰድ ነው የሚነግሩን። ራስወዳድነትንና ከየት እንደተማርነው የማናውቀውን እኔነትን ነው የሚገልጡልን። በብሄርና በዘር ተቧድነን ጣት ቀሳሪነታችንን ነው የሚነግሩን። ለማንም የማይበጅ የኃይልና የእልኸኝነትን ብርታትን ነው የሚያሳብቁን። ታሪክ ማጣመምን፣ እውነትን መሸሽን ነው የሚነግሩን። በትርክት መሸመድመድን፣ በሀሰት መለያየትን ነው የሚጠቁሙን። ተነጋግሮ አለመግባባትን፣ ተወያይቶ አለመስማማትን ነው የሚነግሩን። ለፍቅርና ለይቅርታ የተዘጉ ልቦቻችንን ነው የሚያስታውሱን። ከባህልና ከስርዐት ያፈነገጠ ጊዜ ወለድ ማንነታችንን ነው የሚያንጸባርቁልን።

እስከመች አንቀላፍተን፣ እስከመች የራሳችን ጠላቶች ሆነን እንዘልቀዋለን? የጦርነት ነጋሪት ስንጎስም፣ አታሞ ስንመታ እዚህ ደርሰናል። እስኪ ደግሞ በፍቅር ድካሞቻችንን እንርሳ። ተነጋግረንና ተፈቃቅደን ችግሮቻችንን ካልፈታን የጥንቱን አብሮነት የምንመልስበት ሌላ ሁነኛ መላ የለንም። ከድካሞቻችን ለመበርታት ብቸኛው መዳኛችን እርቀ ሰላም ነው። በእርቅ ሰላም ማውረድ ለእኛ አዲስ ነገራችን አይደለም። ስናስታርቅና ስንመክር፣ ስንገስጽና ስናስተቃቅፍ የኖርን ለዘመናዊው ዓለም ፋና ወጊ የሆንን የስርዐት ቀደምቶች ነን። ልባችንን በእልህና በክፋት ዘግተንው እንጂ ለዛውም ከወንድሞቻችን ጋር፣ ለዛውም አብሮ ከበላና አብሮ ከተዋለደ ሕዝባችን ጋር መተቃቀፍ አይከብደንም ነበር።

አሁን ላይ የሰላም መንገዶቻችንን የዘጉብን የኃይል አስተሳሰቦች ዘመን አመጣሽ ወይም ደግሞ ከዚህ የተሻለ ስም የሚሰጣቸው ናቸው። እንጂማ ማንና ምን እንደነበርን የምናውቅ ነን። ጥንተ መሰረታችን ፍቅርን አምጦ የወለደ ማህጸን፣ አንድነትን አቅፎ ያሳደገ ክንድ ነው። ጥንተ ማንነታችን አብሮነትን እሽሩሩ ያለ፣ ኢትዮጵያዊነትን ያስቀደመ ሀሳብ ነው። ዛሬ በጥላቻና በመለያየት ቆሽሸን የቆምነው አንደበቶቻችን እብለትን፣ እጆቻችን ግፍን፣ ልቦቻችን ጥላቻን ስለተለማመዱ ነው።

በጥላቻ የቆመ ትውልድ እንደ ሎጥ የክብር መንገድ የለውም። በመለያየት የቆመ ሕዝብ እንደ አብረሀም የበረከት ቤት የለውም። ሎጥ ከሰዶም ሲወጣ፣ አብረሀም ከካራን ሲጠራ በፍቅር ልብ በኩል ነው። እኛም የፍቅር ልብ ያስፈልገናል። ከድህነትና ከኋላቀርነት ብሎም ጦርነት እያስከፈለን ካለው አበሳ ለመራቅ ምክክርን እንደሁነኛ አማራጭ ልንቀበለው ግድ ይለናል።

ልዩነት ለምን ተፈጠረ ሳይሆን ልዩነትን እንዴት ማጥበብ እንዳለብን ማወቁ ነው የሚበጀን። ለውይይት ቢሮውን የከፈተ ባስልጣን፣ ለምክክር ፖለቲካውን ያዘጋጀ ፓርቲ ለሀገር ጥፋት የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ለእርቅና ለተግባቦት የተዘጋጀ ማህበረሰብ የልዩነት ጥዶች አዳልጠው አይጥሉትም። የእርቅና የሽምግልና ማኅበራዊ እሴቶቻችን አንድነትን ከማጠንከር ጎን ለጎን አብሮነትን ከማስቀጠል አኳያ የጎላ ድርሻ ነበራቸው። አሁንም ወደዛ የስልጣኔ አፋፍ ለመመለስ ሕዝባዊና ፖለቲካዊ ውይይት ክብር መላሽ ሆኖ ከፊት የሚመጣ ነው።

የሩዋንዳና የደቡብ አፍሪካን የብሄራዊ ምክክር አውድ ስንቃኝ መነሻው የልዩነት ጽንፍ ሆኖ መድረሻው ደግሞ ሀገራዊ ውጥንቅጥ ነበር። በሄዱበት ሁሉን አካታች የምክክርና የውይይት ቅብብሎሽ ችግራቸውን ቀርፈው ሀገራቸውን ወደሰላማዊ ይዞታዋ መመለስ የቻሉበትን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል። በእኛም ሀገር ተመሳሳይ ነገር ስለመንጸባረቁ የኮሚሽኑ ዓመታትን የዘለቀ ዝግጅት ጥቁምታን የሚሰጥ ነው። በሰፊ መድረክ፣ በሰፊ ተሳትፎ ሰፊዋን ሀገራችንን ከአስተሳሰብ ጥበት ለማውጣት እየተሰራ ያለው ስራ የሚደነቅ ሲሆን በእንዲህ አይነቱ አካታችና አሳታፊ፣ ገለልተኛና ነጻ መድረክ ፊት ካልሆነ ወደሰላም የሚያስገባን ቀዳዳ እንደሌለም የሚታመን ነው።

ብሄራዊ ምክክሩን ከሀገራችን አልፈን አውዱን አፍሪካዊ ለማድረግ እየተሰራም እንደሆነ ከኮሚሽኑ በኩል የተሰማ ሰሞነኛ መግለጫዎች ያሳያሉ። ለአንድነት በአንድነት ስንቆም ሰፍተን እንደምንገዝፍ ብዙ ያለፉ ታሪኮቻችን ምስክሮች አሉን። ከእኛ የማሰብና የመዋሃድ አቅም አንጻር ሲታዩ ችግሮቻችን እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም። የሰላም መንገዶቻችንን የዘጉብን እውቀት ማነስ ሳይሆን ለፍቅር አለመሸነፋችን ነበር።

ታሪክና እሴት፣ ወግና ልማድ የሳተ ፖለቲካ ለሀገር አይበጅም። በታላላቅ ባህልና ስርዐት ውስጥ በቅለን ፍሬ አልባ ዛፍ የሆነው ርካብ በሳተ ርምጃችን ነው። ሀገር በመገንባት ሂደት ውስጥ ትልቁ ብቃታችን ሊሆን የሚገባው በምንም የማይሸራረፍ የአብሮነት መንፈስ ነው። ቀጣይ በሚኖረን የእርቅና የተግባቦት መድረክ ላይ እንዲህ አይነቱን መንፈስ በማራገብ ልዩነቶቻችንን ማጥበብ እንችላለን።

ሕይወት የአረዳድ መልክ ነው። እየኖርን ያለነው በተረዳነውና በገባን ልክ ነው። አረዳዳችንን ከኃይል ይልቅ ለሰላም፣ ከጥላቻ ይልቅ ለፍቅር እስካላስገዛን ድረስ ሕልሞቻችን ፍሬ አይቋጥሩም። በአንዳንድ ትርክቶችና አንድነት ጠል ቡድኖች ከመነሻችን ሸሽተን ሌላነትን እየተለማመድን ነው። ከእውነታ የራቀ አረዳድ ትርክት ከማድመጥ ባለፈ ትርክት የማጥራት አቅም የለውም። በሀሰትና በማስመሰል እውቀት ጥራዝ ነጠቆች ሆነን ትውልዱን እየመረዝን ያለነው ባልገባን እውቀት ነው።

አንዳንድ ነፍሶች አሉ..እጅግ በሰለጠነ ዓለም ላይ ቆመው ኢትዮጵያዊነት ያልጠፋቸው። ሀበሻነት ያልተዘነጋቸው። አንዳንድ አእምሮዎች አሉ በዚህ ማንነትን በሚያስት ጊዜ ላይ ተወልደው ታሪካቸውን ያረሱ፣ የመጡበትን ያልተው። አራዳነት ይሄ ነው። ኢትዮጵያዊነት መንፈሱ ይሄ ነው። ዓም እኛን ለመሆን በምትጥርበት ዘመን እኛ ከብቻነት በቀር ምንም የሌላቸውን አውሮፓውያንን ለመሆን የምናደርገው ጥረት እንደ ማንነታችን የሚያስተዛዝበን ነው።

በወሬ ሳይሆን በተግባር፣ በትርክት ሳይሆን በታሪክ ሀገር እንፍጠር። በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር፣ በመለያየት ሳይሆን በማበር ትውልድ እንታደግ። መጪውን ጊዜ በዚህ ለሁላችንም በሚበቃና በሚበጅ እውነትና እምነት፣ ሀሳብና ተግባር ስንቃኘው ብቻ ነው በአዲስ አረዳድ ወደፊት የምንቀሳቀሰው። በቀደመ ሀሳብ ኢትዮጵያን ካላስቀደምን ሌላ የፊተኝነት ሰርጥ የለንም።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለለውጥ ጉዟችን ስኬት ማኅበረሰባዊ ስክነት ወሳኝ ነው!

ለውጥ ሰብዓዊ መሻት ነው። በለት ተለት ህይወታችን የሚያጋጥመን / የሚሰማን ከየትኛውም አሮጌ ነገር ጋር አብሮ ያለመቆየት መነቃቃት ነው። ማኅበረሰባዊ ለውጥም ከዚህ ተጨባጭ እውነት የሚቀዳ፤ የማኅበረሰብ መሻት ነው። አግባብ ባለው መንገድ በጠንካራ ዲሲፕሊን ከተመራ ማኅበረሰብን ወደ ተሻለ ቀጣይ የሕይወት ምዕራፍ ማሻገር የሚያስችል ትልቅ አቅምም ነው።

የሰው ልጅ እንደ አንድ ማኅበረሰብ አሁን የደረሰበት የሥልጣኔም ሆነ የእድገት ደረጃ ላይ መድረስ የቻለው በየዘመኑ በተፈጠሩ የለውጥ መነቃቃቶች እና መነቃቃቶቹ በፈጠሩት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ነው። በቀጣይም ዓለምን ለሰው ልጅ የተሻለች የመኖሪያ አካባቢ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት የተለያዩ የለውጥ መሻቶች ከሚፈጥሩት ፍላጎት የሚመነጭ እንደሚሆን ይታመናል።

በእኛም ሀገር በተለያዩ ወቅቶች በተለያየ መንገድ የተገለጡ የለውጥ መነሳሳቶች /ህሳቤዎች ተስተውለዋል። እነዚህ መነሳሳቶች እንደ ማኅበረሰብ ሕዝባችንን ወደ አንድ ከፍ ያለ የታሪክ ምዕራፍ የማሻገር ማነቃቃት አቅም እንደነበራቸው የታሪክ መዛግብት ያመላክታሉ። ስለ መነቃቃቶቹም ትውልዶች ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ይህም ሆኖ ግን እንደ ማኅበረሰብ የተፈጠሩ የለውጥ መሻቶችን ተፈጥሯዊ መሆናቸውን ካለመረዳት፤ ከዚያም ባለፈ የለውጥ መሻቶችን ተጨባጭ አድርጎ በተግባር ለመተርጎም የተሄደበት መንገድ በለውጥ ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ተቃርኖዎችን መሻገር የሚያስችል ስክነት በመታጣቱ፣ አብዛኞቹ የለውጥ መነቃቃቶች የታሰበላቸውን ያህል ፍሬ ማፍራት ሳይችሉ ቀርተዋል።

በተለይም ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት የመጣንበት መንገድ ያስተናገዳቸውን ሀገራዊ የለውጥ መሻቶች ተጨባጭ ለማድረግ የተሄደባቸው መንገዶች አብዮታዊ የመሆናቸው እውነታ፤ ለማኅበረሰቡ የለውጥ መሻት ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በማኅበረሰብ ውስጥ ተጨማሪ የተቃርኖ እሳቤዎችን በመፍጠር ስለለውጥ ያሉ አስተሳሰቦች አሉታዊ ትርጓም እንዲላበሱ አድርጓቸዋል።

ስለለውጥ የሚያቀነቅኑ ፤ ለለውጥ እሳቤዎች ራሳቸውን የሰጡ እና የሚተጉ ቡድኖች እና ግለሰቦች ወደ አደባባይ ሲመጡም በቀደመው የለውጥ ተሞክሮዎች ጥላ ውስጥ በማስቀመጥ ፤ አብዮታዊ ሆነው የሚገለጡበትን መንገድ የመጠበቅ አዝማሚያዎች በስፋት የሚስተዋሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

እንደ ሀገር ትውልዶች ሲቀባበሉት የመጡት ለሕዝባችን የለውጥ መሻት በመሠረታዊነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት ድህነትን እና ኋላቀርነት ፤ ከዚህ የሚመነጭ ጠባቂነት የፈጠረውን ሀገራዊ ትርክት የመለወጥ ቁጭት ነው፤ ሀገርን እንደ ሀገር ወደቀደመው የከፍታ ርካብ መልሶ የማውጣት መሻት ነው ።

ይህ አይነቱ የማህበረሰብ መሻት ተቃርኖዎች በሚፈጥር አብዮታዊ የትግል መስመር የሚፈታ አይደለም። በተለይም እንደኛ ባሉ ብዝኃነት መለያቸው በሆነ ፤ ብዙ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ባሉበት ማኅበረሰብ ውስጥ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። የቀደሙት የአብዮታዊ የለውጥ ትርክቶቻችንም የሚያመላክቱት ይህንኑ እውነታ ነው።

በእኛ ሀገር ያለውን የለውጥ መሻትን ማስተናገድ የሚቻለው ከሁሉም በላይ ፤ የተለያዩ ፍላጎቶችን ማስተናገድ የሚያስችል ሀገራዊ የአስተሳሰብ መሠረት መገንባት ስንችል ነው። ለዚህ ደግሞ ከተለማመድነው አብዮታዊ አካሄድ ወጥተን ከፍ ያለ ማኅበረሰባዊ መረጋጋት /ስክነት ውስጥ መግባት እና ስክነት ወደሚፈጥረው አርቆ አሳቢነት መሸጋገር ይኖርብናል።

የለውጥ መሻት ተፈጥሯዊ እንደሆነ ፤ ለውጥም ለስኬታማነቱ እና ትርጉም ላለው ዘላቂ ተፈጥሯዊ ሂደቱ ስክነት ይፈልጋል። ስክነት ማኅበረሰባዊ የለውጥ መሻትን በአግባቡ ከመረዳት የሚመነጭ ፤ ራስን የለውጥ አልፋና ኦሜጋ አድርጎ ከማሰብ የሚታደግ ፤ ከዚያ ይልቅ ራስን እንደ አንድ የለውጥ ኃይል አድርጎ ማሰብ የሚያስችል ውስጣዊ አቅም ነው።

ማኅበረሰባዊ ስክነት ዛሬን ከትናንት በማስታረቅ ፤ ነገን በተሻለ ተስፋና ተስፋው በሚወልደው ማኅበራዊ ትጋት መጠበቅና መጨበጥ የሚያስችል ጉልበት ነው ። የለውጥ መሻቶችን ያለብዙ አላስፈላጊ ዋጋ እውን ማድረግ ፤ ትውልድ ተሻጋሪ ማኅበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እሴቶችን ለመፍጠር እና ለመተርጎም የተሻለ ዕድል የሚፈጥር ነው ።

በተለይም አሁን ላይ እንደ ሀገር ከትናንቶች እና ትናንቶቻችን እያስከፈሉን ካሉ ያልተገቡ ዋጋዎች ወጥተን ፤ የጀመርነው አዲስ የለውጥ መንገድ ውጤታማ እንዲሆን ፤ በለውጡ ያሰብነው የመለወጥ መሻታችን እውን እንዲሆን ከሁሉም በላይ ማህበራዊ ስክነት ያስፈልገናል።

ለዚህ ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ አሁናዊ እውነታዎችን ከነገ የለውጥ ተስፋው ጋር አጣጥሞ በስክነት መጓዝ ፤ ማህበረሰባዊ የለውጥ መነሳሳት ማኅበረሰባዊ ከዚያም በላይ ትውልዳዊ ግብ እንዳለው በመረዳትም ፣ ከገነገነ እኔነት ወጥቶ ለማኅበረሰባዊ ማንነቱ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። ለጀመርነው ለውጥ ሁለንተናዊ ስኬትም ያለው መልካም አማራጭም ይኸው ነው!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## የኢትዮጵያውያን መገለጫ እየሆነ የመጣው አረንጓዴ ዐሻራ

እፀገነት አክሊሉ

ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ በዘመቻ እየወጣ የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን ማከናወን ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል፤ ነገር ግን የሥራውን ያህል በመላ ሀገሪቱ አመርቂ ውጤት መጥቷል ለማለት አያስደፍርም። በተለይም ክረምትን ጠብቆ በቁጥ ቁጥ የሚካሄደው የችግኝ ተከላው ለይስሙላ የሚካሄድ በመሆኑ ተጨባጭ ውጤቶችን ሳያመጣ ቆይቷል።

ከአምስት ዓመታት ወዲህ የተጀመረው የአረንጓዴ ዐሻራ ልማት ሥራ በመንግሥት ልዩ ትኩረት ያገኘ በመሆኑና የኢትዮጵያውያን ብርቱ እጆች በጽናት ታሪክ ለመሥራት ቆርጠ የተነሱ በመሆኑ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የችግኝ ተከላ ለዓመታት ሳያሰልስ መቀጠሉ አዎንታዊ ውጤት እንዲያመጣ አስችሏል ። በተለይም ከቁጥ ቁጥ አካሄድ ወጥቶ ባለፉት አራት ዓመታት 32 ነጥብ 5 ሚሊዮን ችግኝ መትከል መቻሉ የስኬቱ አንዱ ማሳያ ነው።

በብሔራዊ ደረጃ የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ ቀን መኖሩን፤ እያንዳንዱ ክልልም በየበኩሉ የችግኝ ተከላውን ቀን ማወጁ፤ የችግኝ ተከላዎቹ በየጊዜው መሪ ቃል አንግበው መነሳታቸው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሩ ሰፊ ሕዝባዊ ንቅናቄ እንዲፈጥር አስችሎታል። በዚህም የተነሳ በሕዝቡ ውስጥ ሰርጾ እንዲገባ እና ሁሉም በያገባኛል መንፈስ እንዲሠራም አስችሎታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ተፈጠረው ስሜት የተተከሉትን ችግኞች ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ እንዲንከባከብም መነሳሳትን ፈጥሮለታል ።

ይህ እንደ ሀገር የያዝነው ችግኝ ተከላ የሚደገፍና የአየር ንብረት ለውጡ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ውጤትም አዎንታዊ እንደሚሆን የዘርፉ ባለሙያዎች የሚስማሙበት ሃቅ ነው፤ ከሙያው ውጪ ያለነውም ብንሆን ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ ያለውን የአየር ንብረት ሁኔታ ብሎም ከዓመት ዓመት ያለውን የአየር ጸባይ ለውጥና መስተካከል በማየት ውጤቱን መረዳት አይከብደንም።

የአረንጓዴ ልማት ሥራው በተጠናከረ ሁኔታ በተጀመረባቸው ጥቂት ዓመታት ውስጥም ኢትዮጵያውያን ስለ ጥቅሙ ተረድተው ከጫፍ ጫፍ በነቂስ ወጥተው ባደረጉት የችግኝ ተከላ መርሀ ግብርም በአንድ ጀምበር ብቻ ከ 669 ሚሊዮን በላይ ችግኝ በመትከል ዓለምን ጉድ ማሰኘት የቻለ ጀብዱም ፈጽመዋል። ይህንን ምርጥ ተሞክሮ በማስፋት ዘንድሮም ከዚህ በላይ ሰርተን ውጤት በማስገኘት ለወዳጆቻችን ደስታን እምነት ላልጣሉብን ደግሞ ግርምትን ማጫር የሁላችንም የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል።

**በዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ 92 ሺህ ሄክታር ደን ይጨፈጨፍ እንደነበር የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በተደጋጋሚ ድርቅ እንዲከሰት ምክንያት ሆኖም ቆይቷል**

በዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ 92 ሺህ ሄክታር ደን ይጨፈጨፍ እንደነበር የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በተደጋጋሚ ድርቅ እንዲከሰት ምክንያት ሆኖም ቆይቷል ። ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ ተጋላጭ የሆኑት ዘርፎችም በተደጋጋሚ ሲጎዱ ተስተውለዋል። የዝናብ ጥገኛ የሆነው የግብርናው ዘርፍ፤ የውሃ አቅርቦቱ፤ ቱሪዝምም ሆነ የደን ይዞታው በአየር ንብረት ለውጡ ክፉኛ ሲጎዱ ቆይተዋል። ይህንኑ ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት ከፍተኛ በጀትና ሰው ኃይል በማሰማራትና በመመደብ አረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ፕሮጀክት ይፋ አድርጎ ላፉት አራት ዓመታት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። እስከ አለፈው አመት መጨረሻ ድረስም 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል ዓለምን ጉድ ማሰኘት ተችሏል።

ኢትዮጵያውያን አረንጓዴ ዐሻራን ባህል እያደረጉት መጥዋል። ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሯ በየአመቱ ብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን በመትከል በዓለም ላይ ታዋቂ ሀገር ሆናለች ። በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል እቅድ ተይዞ ሁሉም የድርሻውን ለመወጣትና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ተፍ ተፍ ማለት ጀምሯል።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃም እንደሚያሳየው ለመርሃ ግብሩ እስካሁን የተዘጋጀው ችግኝ ከታቀደው በላይ ነው ። ይህም የችግኝ ተከላውን ከእቅዱ በላይ ለመፈጸም መንደርደሪያ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ችግኞቹን ለመትከል የሚያስችለው የቦታ ዝግጅትም በመላው ሀገሪቱ 900 ሺ. የሚሆን ሄክታር መሬት ስለመዘጋጀቱም ተነግሯል።

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ንቅናቄው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ በሚቻልበት አማራጭ ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ ከፍ ያለ ከመሆኑ አንጻርም ዘንድሮ ሊተከል ከታሰበው ችግኝ 60 በመቶ የሚሆነው ፍራፍሬና መኖ እንደሚሆን ይጠበቃል። ይህም አርሶ አደሩ ተጨማሪ ገቢ የሚያገኝበትን አማራጭና ገበያን ማረጋጋት የሚቻልበትን ሁኔታም ስለሚፈጥር ይበል የሚያሰኝ ነው።

በአብዛኛው የፍራፍሬ ችግኞች ላይ ትኩረት መደረጉ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፤ የሥርዓተ ምግብ ሽግግር ለማድረግ፤ ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለማስገኘት በተለይም ምርቶቹን ወደ ውጭ በመላክ ለሀገር ከፍ ያለ የውጭ ምንዛሪ በማምጣትም ጥቅሙ ከፍ ያለ ነው።

እንደሀገር በአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ እስከአሁን በተሠራው የመጀመሪያው ምዕራፍ ሥራ በአብዛኛው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ፍራፍሬዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል ውጤቱንም አይተናል፤ በዚህ ሀገራችን በአቦካዶ ምርት በአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃን እንድትይዝ በር ከፍቷል። በሌሎችም ፍራፍሬዎች ላይም ተመሳሳይ ውጤት ለማምጣት መስራት ደግሞ ይጠበቅብናል።

ከሁሉ በላይ ደግሞ የዘንድሮው የችግኝ ተከላ ስራችን ለየት ያለ እንደሚሆን በተደጋጋሚ ተነግሯል፤ እንደ አለፉት ዓመታት በርካታ ችግኞችን በአንድ ቀን ተከልን ብለን ከማለፍ ባሻገር በተለይም በነሃሴ ወር ላይ የምንተክለው ችግኝ ኢትዮጵያን በዓለም ድንቃድንቅ መዝገብ ላይ ያስቀምጣታል የሚል እቅድ ተይዟል። ያለፉት አራት ዓመታት ልምዳችን እንደሚያሳየንም የታቀደውን ለማሳካት ምንም የሚገድ ነገር የለም።

በአንድ ጀንበር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች በመትከል በድንቃድንቅ መዝገብ ላይ የመስፈር ጥረታችን የአንድ ወገን ጥረት ብቻ ሳይሆን የመላው ሕዝብ ብሎም ክልሎችና ሌሎችንም ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ ልክ ተንቀሳቅሰን ግባችንን መምታት ከቻልን ደግሞ ሀገራችን በእስከ አሁኑ ሂደት ትታወቅባቸው የነበሩ የርሃብና የጦርነት ታሪኮች ሁሉ ይፋቃሉ ማለት ነው።

አረንጓዴ ዐሻራ እኛን በዓለም አደባባይ ከፍ ብለን እንድንታይ ከማድረግም በላይ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ጥቅምንም ያነገበ ነው። ብዙ ችግኝ ተክለን የዓለም ድንቃድንቅ መዝገብ ላይ ስንሰፍር ጎን ለጎን ደግሞ በተከልናቸው ዛፎች አካባቢያችንን ከበርሃማነት መከላከል በተከልናቸው ፍራፍሬዎች ደግሞ በምግብ እህል ራሳችንን ከመቻል ጀምሮ ለዓለም ገበያ አቅርበን ዶላር በማግኘቱም በኩል ሚናው የላቀ ነው፡፡

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ተጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ‹‹ጨሞ›› - ልጅ አሳዳጊው ባለውለታ

መልካምሥራ አፈወርቅ

### ልጅነትን በትውስታ...

ደቡብ ምዕራብ ጊዲ ቤንች ዲዙ። ይህ ቀበሌ ሰላማዊት ካህሳይ ልጅነቷን ያሳለፈችበት፣ ክፉ ደግ ያየችበት መንደር ነው። እሷ በአቶ ካህሳይ አባትነት ስትጠራ በምክንያት ነበር። እኚህ አባወራና ቤተሰቦቻቸው ከመጠሪያነት ባለፈ እንደ ልጅ አሳድገዋታል። ዛሬ ሰላማዊት የልጅነት ጊዜ ውል ሲላት ትከፋለች። ልጅነት ለእሷ የእሾህ ላይ መንገድ ነበር። ሳይመቻት ኖራዋለች፣ ሳይደላት አልፋዋለች።

ሰላማዊት ‹‹እከሌ›› የምትለው ቤተሰብ የላትም። እሷና አሳዳጊዎቿ የመገናኘት ምክንያታቸውም ወላጅ አልባ መሆኗ ነበር። በአሳዳጊዎቿ እጅ መውደቋ ብዙ አሳይቷታል። በቤቱ ውላ ብታድርም እንደልጅ መብት ይሉትን አታውቅም። ለእሷ ተሰፍሮ የተሰጣት ግዴታ በጉልበቷ ማገልገል፣ ‹‹አቤት ወዴት፣›› ማለት ብቻ ነው።

ሰላም እንደ እኩዮቿ መማር፣ ትምህርት ቤት መሄድ ትሻለች። ባልንጀሮቿ ቀለም ቆጥረው ዕውቀት ገብይተው ሲመጡ እነሱን መሆን ምኞቷ ነበር። ይህ እውነት ግን ከእሷ ውስጠት አላለፈም። አሳዳጊዎቿ ከስራ ውጭ መማርን አልፈቀዱም። በጉልበቷ እያገለገለች በታዛዥነት ብቻ እንድትኖር ፈረዱባት።

ሰላማዊት ጊዜው ሲገፋ ዕድሜዋ ሲጨምር ሁሉ ነገር መረራት። በአሳዳጊዋቿ ቤት አገልጋይ ሆኖ መኖር ‹‹ይብቃኝ›› ስትል አሰበች። ተኝታ በተነሳች ቁጥር የምትጨነቅበት ጉዳይ ከአንድ ውሳኔ ሊያደርሳት ግድ ሆነ። ከራሷ መከራ ዘክራ የቆረጠችበት ሀሳብ ዕውን ሊሆን አልዘገየም።

### አንድ ማለዳ...

አሁን ትንሽዋ ልጅ ልቧ ተነስቷል። ያደገችበትን፣ ክፉ ደግ ያየችበትን ቤት ርቃ ልትሄድ ነው። እንዲህ መሆኑ የልቧን ዕቅድ ይሞላል፣ ከገጠር ስትወጣ መማር ትችላለች፣ ከቀዬው ስትርቅ ሰርቶ ማግኘት፣ የእሷ ይሆናል። ሰላም እንዳሰበችው ሆነ። ማለዳውን ከቤት ጠፍታ ብዙ ራቀች። የኋላዋን ለጀርባዋ ትታ ወደፊት ገሰገሰች። አሁን ማንም እንዲያስቆማት ‹‹ተይ›› እንዲላት አትሻም። መሄድ መጓዟን ቀጥላለች። ከቆይታ በኋላ እግሯ ከተማ አዝልቆ ሚዛን አማን አደረሳት።

### ሚዛን አማን...

ሚዛን አማን መልካም ከተማ ነች። ታሪኳ ልቆ፣. ውበቷ ደምቆ የምትታይ ድንቅ ስፍራ። አስተውሎ ላያት ተፈጥሮ ለእሷ ያደላ ይመስላል። ብዙዎች የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የአብሮነት ተምሳሌት መሆኗን ይመሰክራሉ። ቀድሞ ሚዛን ተፈሪ ትባል የነበረችው ከተማ ሚዛን አማን ተብላ ከተሰየመች ዓመታትን ቆጥራለች።

ዕድሜ ጠገቦቹ አዛውንቶች ዛሬም ድረስ ስለከተማዋ ታሪክን ያጣቅሳሉ። ቀድሞ ሚዛን ተፈሪ ለመባሏ ምክንያቱ ከአፄ ሀይለስላሴ ስም ጋር ተያይዞ ነው። ስያሜዋን የቸሯት ደግሞ ልጅ እያሱ እንደሆኑ ታሪክ ይጠቁማል። ከተማዋን የቆረቆሩት ፊታውራሪ ዓለማየሁ ፍላቴን ጨምሮ ብዙዎቹ ስለአብሮነት ብዙ አሳይተዋል።

ሚዛን በደርግ ዘመን የከፋ ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳር ጽህፈት ቤት መገኛና መቀመጫ ነበረች። ይህች ከተማ በብዙ ውጣውረድና ለውጥ እየተጓዘች መቀጠሏን እማኞቿ ይናገሩላታል። ከዙሪያ ገባ የሚመጡ እንግዶችን በማስተናገድም የሚያህላት የለም።

የቤንች ሸኮዋ ሚዛን አማን እንደስያሜዋ ናት። ብዙዎችን በጉያዋ አቅፋ አገር አማን ውሎ እንዲያድር ሰላሟን ታሳያለች። በከተማዋ በየጊዜው ከየገጠሩ የሚገባ ምርት ሲፈስባት ይውላል። ፍራፍሬው፣ አትክልቱ በረከቷ ነው። ቡናው፣ ቅመማቅመሙ፣ የጎማው ዛፍ ሲሳይ ከሌሎች ነጥሎ ይለያታል።

እስከዛሬ ያልጎደሉ ወንዝ ፏፏቴዎቿ፣ ምድርን አረንጓዴ እንዳላበሱ ዘለቀዋል። በሰፊው ገበያዋ ተጠይቆ፣ የሚታጣ የለም። ከዓመት እስከ ዓመት ደጂ ሙሉ ነው። ወደዚህች ስፍራ ማንም ጎራ ቢል ደግሞ እንግድነት አይዘውም። በጉልበቱ፣ ሰርቶ፣ በአቅሙ ሮጦ ለማደር ዕድል ከእሱ ጋር ነች።

ሰላማዊት ስለሚዛን አማን ሕይወት ስትሰማ ኖራለች። በዚህ ስፍራ ብትመጣ የልፋቷን አታጣም። ሰርታ ካደረች የላቧን ታገኛለች። እንዲህ ከሆነ የምትጓጓለት ትምህርት አይርቃትም። እየሰራች ትማራለች። ከተማረች ሕይወቷ ይለወጣል፣ ድህነትን ድል ነስታ ራሷን ታሸንፋለች።

ሚዛን አማንና ሰላማዊት በአካል ተገናኝተዋል። እሷ ከተማው ከነበረችበት ሕይወት ነጻ እንደሚያወጣት አልጠፋትም። የማደጎ ኑሮ መልከ ብዙ ነው። የሰው ቤት እንጀራ፣ እንደራስ መሶብ አይቆርሱትም። ሁሌም ግዞተኛና ታዛዥ ሆኖ መኖር ይሰለቻል፣ ሆድ ያስብሳል። አሁን ስለራሷ ሕይወት ልትወስን ነው። ያደገችበትን ቤትና ቀዬ ርቃለች፣ ከአሳዳጊዎቿ ጉያ ወጥታለች።

ሚዛን አማን ያገባት እግሯ ውሎ አድሮ ከፍጻሜው አድርሷታል። በሀያ አምስት ብር ደሞዝ ከሰው ቤት የተገኘላትን ስራ ወዳዋለች። በሰራተኝነት መቀጠሯ ገንዘብ ያስይዛታል፣ ለትምህርት ዕውቀቷ ይበጃታል። ሰላማዊትየልቧ እየሞላ የሀሳቧ እየደረሰ ነው።

### የሀያ አምስት ብር ደሞዝተኛ...

ሰላም በተቀጠረችበት ቤት የሰራተኝነት ስራዋን ጀመረች። አሰሪዋ መልካም ወይዘሮ ናት። ከግዴታዋ የዘለለ ጉልበቷን አትጠይቅም። መላው ቤተሰብ ስለእሷ አሳቢና አዛኝ ሆኗል። ውሎ አድሮ ሰላም ለአሰሪዎቿ ፍላጎቷን አሳወቀች። አሁን እየሰራች መማር፣ ትፈልጋለች። በልጅነቷ ያጣችው እድል ዳግም እንዲያመልጣት አትሻም። በጉልበቷ ብታድርም ፊደል መቁጠር፣ ቀለም መለየት ትሻለች። አሰሪዎቿ ሀሳቧን አልተጋፉም። እየሰራች እንድትማር ይሁንታውን ሰጧት።

### ተማሪዋ...

ሰላም ደብተር ገዝታ፣ እርሳስ እስክሪብቶ አሟልታ ትምህርት ቤት ተመዘገበች። ጥረቷን ያዩ ሁሉ እንደአሰሪዎቿ ‹‹አይዞሽ›› ሲሉ አበረቷት። የሥራ ግዴታዋ ከወጉ አልጎደለም። ኃላፊነቷን እየተወጣች ከትምህርት ገበታዋ ተገኘች። ከሀያ አምስት ብር ደሞዟ ላይ ሰባት ብሩን እያነሳች ለትምህርት ቤት መክፈል ጀመረች። አልሰነፈችም። ዓመቱን ተምራ ከአንደኛ ወደ ሁለተኛ ክፍል ተሻገረች። የውስጧ ፍላጎት፣ የልጅነት ምኞቷ አንድ ሲል ጀመረ። ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ ውሏን አልረሳችም። ዕቅዷን አልዘነጋችም። በአዲሱ ዓመት ደብተሯን ገዝታ ለሁለተኛ ክፍል ተዘጋጀች።

የሀያ አምስት ብር ተከፋይዋ ሰላም አሁን የወር ደሞዝተኛ ናት። በየግዜው ሰባት ብር ለትምህርት ቤቷ እያነሳች ቀሪውን ታስቀምጣለች። የሚተርፋት ሀያ ሶስት ብር ለልብስ ጫማዋ አያንስም። የዛኔ ይህ ገንዘብ ለእሷ ብዙ የሚባል ነበር። የፍላጎቷን ሞልቶ ለቁጠባዋ ይተርፋል።

ሰላም መማሯ አልተቋረጠም። በየዓመቱ ክፍሎችን በብቃት ማለፍ ይዛለች። ዛሬም ዓላማዋ ሩቅ፣ ዕቅዷ ሰፊ ነው። አሁን አራተኛን ተሻግራ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሆናለች። ለከርሞ ደግሞ የሚኒስትሪ ብሔራዊ ፈተና ይቆያታል።

ፊደል ከመለየት ያለፈው የወጣቷ ዕውቀት በብዙ ትልሞች ታጅቧል። ለእሷ ነገ ብሩህ ነው። በጥረቷ ብዙ ታይበታለች። ይህ እንዲሆን የዛሬ መንገዷ ተቃንቷል። እየሰራች ትማራለች። ሰላም አምስተኛ ክፍል እንደገባች አንዲት ሴት አገኘቻት። ይህችን ሴት አሳምራ ታውቃታለች። ልጅነቷ በእጇ ተቃኝቷል። የዛኔ ሕይወት በእሷ አጠገብ ሀዘንና ዕንባ ነበር። ስታሳድጋት በሙሉ ነጻነት አይደለም። ፍቅሯን ነጥቃታለች። ጉልበቷን ብትሻ ትምህርት ነፍጋታለች።

አሁን ፊት ለፊቷ የቆመችው ሴት ይህን የረሳች ይመስላል። ሰላምን መልሳ ለመውሰድ ማባበል ጀምራለች። ሰላማዊት የቀድሞ አሳዳጊዋን አመነቻት። አብረው እንዲኼዱ በጠየቀቻት ጊዜ አልተቃወመቻትም። ሀሳቧን በይሁንታ ተቀብላ በመሄዱ ተስማማች።

አሁን ሰላም ሰባት ዓመታት የኖረችባቸውን መልካም ቤተሰቦች ልትሰናበት ነው። ዳር ያልደረሰው ትምህርቷ ከአምስተኛ ክፍል አላለፈም። ተመልሳ ወደገጠር



ስትገባ ቅር አላላትም። አሳዳጊዋን ተከትላ፣ ልጅነቷን ካሳለፈችበት ‹‹ጊዲ ቤንች ዲዙ›› መንደር አመራች።

### ኑሮ በዲዙ...

ሰላም ከሚዛን አማን ተመልሳ የገጠሩን ሕይወት ጀመረች። ኑሮ በሁለቱ ቦታዎች ይለያያል። የከተማ ቆይታዋ ብዙ አስተምሯታል። ሰርቶ ማደር፣ ጥሮ መቀየር እንደሚቻል አውቃለች። ዛሬ ዕድሜዋ እንደቀድሞው አይደለም። እሳቤዋ ተለውጧል። ዕውቀቷ ጨምሯል። እንደፊቱ በደልን የሚሸከም ትከሻ የላትም።

ዲዙና ሰላም ዳግም ተገናኝተው ሕይወት በልማዱ ቀጠለ። ውሎ አድሮ ከአሳዳጊዋ ጋር እንደታሰበው አልሆኑም። መሀላቸው መግባባት ጠፋ፣ ስምምነት ይሉት ታሪክ ሆነ። ይህኔ ሰላም ቆም ብላ አሰበች። ኑሮ እንዲህ ከሆነ ይከብዳል። ከዚህ በኋላ ሕይወት ከአሳዳጊዎቿ ቤት አይቀጥልም። አሁን የራሷን ትዳር መያዝ፣ ቤት መምራቱ እንደሚበጅ ለውስጧ ነግራዋለች።

### ዳግም በሚዛን...

አሁን ሰላም ሕይወት ክፉ ደግ አሳይቷታል። ከዚህ በኋላ ‹‹እከሌ›› የምትለው የቅርብ ሰው ጎኗ የለም። ሰባት ዓመታት ካሳለፈችበት ቤት ተመልሳ አትገባም። ብዙ የለፋችለት ውጥን ትምህርቷ ዳር ሳይደርስ ተቋርጧል። ሚዛን አማን ሰላምን ልትቀበል ፊት አላዞረችም። እንድትናንቱ እጇን ዘርግታላታለች። የአሁኑ ሕይወቷ ግን ብቻዋን አልሆነም። ለትዳር ካሰበችው ጓደኛዋ ጋር ኑሮን ጀምራለች። በሚዛን ግማሽ ዕድሜዋን የገፋችው ሰላም ለክፉ ደግ አጋጣሚዎች አዲስ አይደለችም። ሁሉን እንደአመጣጡ ችላ አቅሟ የፈቀደውን መስራት ችላበታለች።

### የሶስት ጉልቻ ትኩሳት...

ሰላም ብቸኝነትን ሸሽት የጀመረችው አብሮነት ከትዳር አጋሯ አውሎ ያሳድራታል። ጥንዶቹ ጎጇቸው በልጅ በረከት ታድሶ የመጀመሪያውን ወንድ ልጅ ስመዋል። ኑሯቸው በአንድ ቢዘልቅም መሀላቸው ሰላም ይሉት የለም። መግባባት ርቋቸው በቅያሜ ያድራሉ።

ከመጀመሪያው ልጅ ሶስት ዓመታት በኋላ ሁለተኛው ሕጻን ተወልዷል። የእሱ መምጣት ብቻ ግን የቤቱን ሰላም አልመለሰም። አለመግባባቱ ቀጥሎ። ቅያሜው ብሷል። በዚህ ጅማሬ ያልገፋው ትዳር ወሎ አድሮ በፍቺ ሊቋጭ ግድ አለ። ባልና ሚስት ጎጇቸው ተፈታ፣ የአብሮነታቸው ገመድ ተበጠሰ።

### ሕይወት ከልጆች ጋር...

ሰላም ባሏን ከፈታች ወዲህ የልጆቿ ኃላፊነት በእሷ ትከሻ ወድቋል። ሁለቱ ወንዶች ልጆች በልተው ለማደር፣ ተምረው ለመግባት ተስፋቸው እናት ብቻ ሆናለች። የተሻለ ሥራና ገቢ የሌላት ሰላም ዛሬም ከሚዛን አማን መሀል ልብ አልራቀችም። ያገኘችውን ሰርታ ልጆቿን ታጎርሳለች።

ሰላምን የኑሮ ውድነት፣ የቤት ኪራይ ችግር ይፈትናታል። ነፍስ ያላወቁ ልጆቿ የእሷን እጅ ናፋቂዎች ናቸው። ዛሬ እንደቀድሞው በሀያ አምስት ብር የሚሞላ ኑሮ የለም። ሁሉ ነገር ውድና ፈታኝ ሆኗል። ጊዚያት በጥረትና ሩጫ ተገፍተው ዓመታት ነጎዱ። ሰላም ልጆቿን ለማስተማር ደፋ ቀና ይዛለች።

### ደግ አሳቢው ብላቴና...

የመጀመሪያ ልጇ ዛሬ ጎረምሳ ሆኗል። ከልጅነቱ አንስቶ ለእናቱና ለታናሽ ወንድሙ ሲያስብ ሲተክዝ ኖሯል። በዕድሜው የቀደመ የለም። እናቱ እየሰራች ታኖረዋለች፣ እየለፋች ታስተምረዋለች። ውሎ አድሮ ግን ይህን እውነት መሸከም ከበደው። የእናቱ ልፋትና ሩጫ ውስጡን ያሳዝነው ያደማው ያዘ። የዘወትር ሀሳቡ ከዕድሜው በታች አጫጭቶ አሳየው። በትካዜው ጉዞ አልቀጠለም። ትምህርቱን አቋርጦ የእናቱን ሸክም ሊያቀል ስራዎችን ፈላለገ። እንደሀሳቡ ሆኖ የልቡን አላጣም። እንጨት ቤት እየሰራ ታናሽ ወንድሙን ማስተማር፣ እናቱን መደገፍ ያዘ።

አንዳንዴ ወንድማማቾቹን የሚያስተውሉ ብዙዎች የትልቅነቱን መንበር ለታናሽ ወንድም ይሰጣሉ። የትልቁ የበዛ አሳቢነት ውስጡን ሰብሮት ቆይቷል። ትካዜው ማየሉ አካሉን ጎድቶታል። እንዲያም ሆኖ ያሰበውን ሊያደርግ አልታቀበም። ዛሬ የቤቱ ኑሮ በእሱ ላብ፣ በጉልበቱ ድካም ጸንቷል።

ትልቁ ልጅ ሁሌም ቢሆን ‹‹ለኔ›› ይሉትን አያውቅም። የእጁን አራግፎ ለቤተሰቡ ደስታ ያድራል። የእሱን ጥቅም ትቶ ለእነሱ ማለቱ ደግሞ አንዳች አላከሰረውም። በየቀኑ ምስጋና ልብሱ ነው። ዘወትር የእናቱ ምርቃት ይከተለዋል።

### ጨሞ የቤቱ እህል ውሀ ...

አማን ሚዛን በረከቷ ብዙ ነው። ለሚሰራ፣ ለሚለፋ የድካም ዋጋን አትነፍግም። ሰላማዊት ሕይወቷን ለመግፋት በሚዛን መንገድ ዳርቻ ውላ ታመሻለች። ይህ እውነት የየእለት ግዴታዋ ነው። እንዲህ ካልሰራች ኑሮ ይሉት የለም። ሕይወትን ለመምራት ልጆች አሳድጎ ለማስተማር በዚህ ቦታ መገኘት ግድ ይላል።

ሰላም ከማለዳ እስከ ምሽት የሚያዘልቃት ምክንያት ለደንበኞቿ ቀምማ የምትሸጠው ‹‹ጨሞ›› ነው። ጨሞ በአገሬው የሚዘወተር፣ እንደሻይ ተፈልቶ ‹‹ፉት›› የሚሉት መጠጥ። ጨሞ ለእሷና ለልጆቿ ባለውለታቸው ነው። የአንዱ ኩባያ በረከት ጎዶሎን ይሞላል፣ ችግርን ይፈታል፣ ኑሮን ይገፋል።

ጨሞ ከቡና ቅጠል የሚዘጋጅ ነው። እንደ ሻይ አፍልቶ በፍቅር ለመጠጣት ደግሞ ጥሩ ሙያን ይጠይቃል። ነጭ ሽንኩርት፣ ሚጥሚጣ፣ በሶብላ፣ ድንብላል ለጨሞ ጣዕም መፍጠር ወሳኝ ሆነው ይገባሉ። ይህን መጠጥ ሰላም ብቻ አትሸጠውም። ልክ እንደእሷ መተዳዳሪያ ሊያደርጉት የወደዱ በርካቶች ለገበያ ያቀርቡታል። አሁን ባለው ሸያጭ የአንዱ ኩባያ ዋጋ ከአምስት ብር አልተሻገረም። ሰላም አንዳንዴ ጨሞውን በቀን እስከ ሶስት መቶ ብር ትሸጣለች። እንዲህ ይቅናት እንጂ እንደምታስበው የረባ ተቀማጭ የላትም። መጠጡን ለማዘጋጀት በምትገዛቸው ቅመሞች መልሶ አቅሟ ይፈተናል።

ጨሞ ለእሷና ለልጆቿ ባለውለታ ነው። እሱን ሸጠው በሚያገኙት ገቢ ኑሯቸውን ይደጉማሉ። እሷ ባለቤቷን በፍቺ ከተለየች በኋላ ቋሚ መተዳደሪዋ ይኸው የተቀመመ የቡና ቅጠል ሆኗል። እርግጥ ነው ከልፋት አንጻር ዋጋው አይመጥንም። የአካባቢው ሽያጭ ተመሳሳይ መሆኑ ግን ሂሳብ ለመጨመር አላስቻላትም።

### ቀና ልቦች...

በከተማው ወይዘሮ ሳላይሽን የመሰሉ ልበ ቀናዎች እነ ሰላምን ለመደገፍ ወደኋላ አይሉም። እንዲህ አይነት ሰዎች ሲበረክቱ የኑሮ ሸክም ይቀላል። ልክ እንደወይዘሮዋ ሁሉ የዓይኖችን ዕንባ የሚያብሱ፣ መልካም ሰዎች ከፊት ቀድመው ይገኛሉ። እናትና ልጆች ለዓመታት በኪራይ ቤት ኑሮ ተንከራተዋል። ኪራዩን አሟልቶ ለመስጠት እጅ ሲያጥር ደግሞ አንገት መድፋት፣ መተከዙ አይቀርም። አንዳንዴ ሰላም ሆድ ብሶ ሲመራት በከተማው ማዘጋጃ ቤት ደጃፍ ቆማ ዕንባዋን ታዘራለች። ይህን ከሚያዩት መሀል አንድ ወጣት ኃላፊ ሁሌም አብሯት ያዝናል፣ ያለቅሳል።

ይህ ከልብ የመነጨ ስሜት ውሎ አድሮ ለውጤት መድረሱ አልቀረም። ወጣቱ ለእሷና ለልጆቿ የቀበሌ ቤት እንዲያገኙ አገዛቸው። ዛሬ ሰላም ለአንገቷ ማስገቢያ ጎጆ አላት። ጨሞን ሸጣ ስትገባ በአፎይታ ፈጣሪዋን ታመሰግናለች። ጨሞ የእሷና የልጆቿ እህል ውሀ ሆኗል። እሷ በረከቷን አትንቅም፣ ዕለት በዕለት እሱን ሸጣ ነገን ተስፋ ታደርጋለች።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ እምርታ - በሶማሌ ክልል

ኢያሱ መሰለ


ፎቶ :- ገባቦ ገብሬ

የጎዴ ከተማ ውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ

ከለውጡ በፊት በነበሩት 27 ዓመታት አጋር በሚል አግላይ ስም ተፈርጀው በሀገራቸው ጉዳይ እኩል የመወሰን፣ የመጠየቅና የመጠቀም መብት ከተነፈጉ ክልሎች አንዱ የሶማሌ ክልል ነው። በኢትዮጵያ አዲስ የለውጥ ምዕራፍ ከጀመረ ከ2010 ዓ.ም ወዲህ የሶማሌ ክልል ሕዝብ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን ችሏል።

ለዘመናት በልማት ወደ ኋላ ተጎትቶ የኖረው የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዛሬ ሰላማቸውን አስጠብቀው በልማትና እድገት አበረታች ውጤት እያስመዘገቡ ከሚገኙት ክልሎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ እስከመሆን መድረሱ እየተገለጸ ነው። ሕዝቡ ለበርካታ ዓመታት ሲያነሳቸው የነበሩ የመንገድ፣ የውሃ፣ የመብራት፣ የትምህርት፣ የጤና እና የሌሎችም መሰረተ ልማት ጥያቄዎች መልስ እያገኙ መጥተዋል። አንዳንዶቹም መሰረተ ልማቶች ከለውጡ በፊት ከነበረው ቁመናቸው በእጥፍ እስከማደግ ደርሰዋል።

በቅርቡ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባደረግነው የመስክ ምልከታ ከመሰረተ ልማት አውታሮች አንዱ በሆነው የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ አበረታች ተግባሮች መከናወናቸውን መመልከት ችለናል። ከለውጡ በፊት፤ የሶማሌ ክልል እንዳለው የቆዳ ስፋት እና ከሌሎች ክልሎች እና ከጎረቤት ሀገራት ጋር እንዳለው ሰፊ ወሰን የመንገድ መሰረተ ልማት የተስፋፋበት እንዳልነበር የክልሉ ነዋሪዎችና አመራሮች ገልጸውልናል።

ባለፉት ስድስት ዓመታት ክልሉ ሰላሙን አስፍኖ ፊቱን ወደ ልማት በማዞሩ በተለይም በመንገድ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ውጤታማ ሥራዎች መስራት ችሏል። በዚሁ መሰረት ገጠርን ከከተማ፤ ከተማን ከከተማ ያስተሳሰሩ የአስፋልትና የጠጠር መንገዶች ተሠርተው ለሕዝቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ክልሉ በሚያስተዳድራቸው አስራ አንዱም ዞኖች የሚቀርቡ የመንገድ መሰረተ ልማት ጥያቄዎች እንደ ቅደም ተከተላቸውና እንደ አስፈላጊነታቸው መጠን እየታዩ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። ለአብነት በመስክ ጉብኝታችን ከተመለከትናቸው የመንገድ ግንባታዎች አለፍ አለፍ እያልን የተወሰኑትን እንመልከት።

በክልሉ የመንገድ መሰረተ ልማት ከተስፋፋባቸው ዞኖች አንዱ የኤረር ዞን ነው። ከለውጡ በፊት በዞኑ ምንም አይነት አስፋልት መንገድ አልነበረም። ከለውጡ ወዲህ ግን ሶስት ትልልቅ የአስፋልት መንገዶች ተገንብተዋል።

የመጀመሪያው የኤረር ዞን ዋና ከተማ ፊቅን እና የኦሮሚያ ክልል ባቢሌ ከተማን የሚያገናኘው የአስፋልት መንገድ ሲሆን አስፋልቱ እስከ 170 ኪሎ ሜትር ይረዝማል። ሁለተኛው ከፊቅ - ያሆር- ገርቦ እስከ ጎዴ ድረስ የሚዘልቀው የአስፋልት መንገድ ነው፤ ይህም መንገድ ከጂግጂጋ በስተምዕራብ በኩል መዳረሻውን ጎዴ አድርጎ በርካታ ወረዳዎችን እያካለለና እያስተሳሰረ ይዘልቃል። ሶስተኛው ከፊቅ- ሀመሮ- ኢሜ ድረስ የሚዘልቀው ረዥም የአስፋልት መንገድ ነው።

እነዚህ መንገዶች በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡና እየተገነቡ ያሉ ናቸው። ከእነዚህ አስፋልት መንገዶች በተጨማሪም ክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች ያሠራቸው የጠጠር መንገዶች በርካታ ናቸው።

የፊቅ ከተማን ከባቢሌ ከተማ የሚያገናኘው መንገድ የኦሮሚያን እና የሶማሌ ክልሎችን ያስተሳስራል፤ መንገዶቹ በአጠቃላይ የአካባቢውን የትራንስፖርት ችግር የፈቱ ከመሆኑም ባሻገር የንግድ ልውውጥና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን በማቀላጠፍ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ የአካባቢው የመስተዳዳር አካላትና ነዋሪዎች ገልጸዋል።

መንገዱ በአካባቢው ያለውን ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ከገበያ ጋር ለማገናኘት እንደጠቀመና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ጉልህ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝም ያስረዳሉ። ከአሁን በፊት በአካባቢው ከነበረው የጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ የመሰረተ ልማት ሥራዎችን ማከናወን አስቸጋሪ እንደነበር የጠቀሱት ነዋሪዎቹ፣ ከለውጡ ወዲህ የአካባቢው ሰላም በመጠበቁ መንገድን ጨምሮ በርካታ የልማት ሥራዎች በመሰራታቸው ደስተኛ እንደሆኑ ያመለክታሉ።

በዶሎ ዞን ዋርዴር ከተማ ያገኘናቸው ነዋሪዎች ግን ከተጀመረ ስድስት ዓመታትን የፈጀው የዋርዴር ቀብሪደሃር አስፋልት መንገድ በመዘግየቱ ቅሬታ እንደተሰማቸው ገልጸውልናል።

ዋርዴር በሶማሌ ክልል የዶሎ ዞን ዋና ከተማ ነች። ከቀብሪደሃር ከተማ በስተምስራቅ 125 ኪሎ ሜትር ገባ ብላ የምትገኝ የጠረፍ ከተማ ስትሆን፣ ዶሎ ዞንን ከሌሎች ዞኖች ጋር ታስተሳስራለች። ከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ይስተዋልባታል።

ከቀብሪደሃር - ዋርዴር የሚሠራው የአስፋልት መንገድ ለከተማዋ እድገት ተስፋ የሰነቀና ለነዋሪዎች ደስታን የፈጠረ ቢሆንም፣ መንገዱ ዛሬም ድረስ ባለመጠናቀቁ የአካባቢውን ነዋሪዎችን ቅር አሰኝቷል።

ወይዘሮ ሀምዱ ሁሴን የዋርዴር ከተማ ነዋሪ ናቸው። ዋርዴር ለዘመናት የመንገድ፣ የመብራት፣ የንጽህ መጠጥ ውሃ ጥያቄ የነበረባት ከተማ ስለመሆኗ ያስታውሳሉ። የውሃና የመብራት ጥያቄዎቿ ከለውጡ ወዲህ ባሉት ስድስት ተከታታይ ዓመታት መመለሳቸውን ገልጸው፣ እየተሠራ ያለው አስፋልት መንገድ ተጠናቆ አገልግሎት የሚሰጥበትንም ቀን በናፍቆት እየጠበቁ ስለመሆናቸው ተናግረዋል።

የመንገድ ሥራው የዛሬ ስድስት ዓመት እንደተጀመረ የተናገሩት ወይዘሮ ሀምዱ እስከ አሁን የመዘግየቱ ጉዳይ እርሳቸውን ጨምሮ የከተማዋን ነዋሪዎች ቅር እንዳሰኘ ጠቁመዋል። ‹‹እናት ልጇቿን ከረሜላ አመጣላችኋለሁ እያለች እንደምታባብል ሁሉ አመራሮቻችን ሁሉም ታገሱ ይሉናል›› ያሉ ወይዘሮ ሀምዱ፣ የከተማው ሕዝብ እስከ አሁን ድረስ በትዕግስት እየጠበቀ መሆኑን ተናግረዋል። ሰሞኑን ግን መንገዱ በበጀት ምክንያት ሥራው ተቋርጧል መባሉን መስማታቸውን ጠቅሰው፣ ‹‹የሚመለከተው አካል መንገዱን በፍጥነት አጠናቆልን አፎይ እንድንል ሊያደርገን ይገባል›› ብለዋል።

ወይዘሮ አብሽሮ ሁሩ ሌላዋ አስተያየት የሰጡን የዋርዴር ከተማ ነዋሪ ናቸው። ከለውጡ በኋላ ከተማችሁ ምን ለውጥ አገኘች? ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ ‹‹ወላሂ በአካባቢው ሰላምና ጸጥታ ከሰፈነ በኋላ በርካታ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ውሃ ገብቷል፤ ሆስፒታል ተሠርቷል፤ በተለይ ከቀብሪደሃር ዋርዴር እየተሠራ ያለው የአስፋልት መንገድ አላለቀም እንጂ ቢያልቅ ኖሮ ከተማችን በደንብ ትቀየር ነበር፤ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ በአስቸኳይ መንገዱን እንዲጨርስልን እንፈልጋለን›› ሲሉ ምላሻቸውን ገልጸዋል።

እኛም የነዋሪዎችን አስተያየት ለሚመለከተው አካል ለማድረስ በገባነው ቃል መሰረት በአጠቃላይ በመሰረተ ልማት ግንባታውና በተለይ ነዋሪዎቹ ባነሱት ቅሬታ ላይ ያነጋገርናቸው የዋርዴር ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ መውሊድ ቱርሃ ‹‹ክልሉ ሰላሙን ካረጋገጠ በኋላ የዶሎ ዞን በተለይም በመንገድ ዘርፍ የሚያነሳው የዘመናት ጥያቄ ሊመለስ ጫፍ ደርሷል›› ሲሉ ይገልጻል።

ሕዝቡ በግንባታው መጓተት ቅር የተሰኘበት መንገድ የሚሠራው በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ባለቤትነት መሆኑን ጠቅሰው፣ ግንባታው በተለያየ ጊዜ በመቋረጡ ምክንያት በፍጥነት መጠናቀቅ አለመቻሉን


ወይዘሮ ሀምዱ ሁሴን


ወይዘሮ አብሽሮ ሁሩ


አቶ መውሊድ ቱርሃን

በጋራ መድረክ ገምግመናል ይላሉ። ሥራው 58 በመቶ ደርሶ በበጀት እጥረት ምክንያት ለጊዜው እንደተቋረጠ በግምገማው መድረክ ተገልጾልናል ያሉት የወረዳው አስተዳዳሪ፤ በቅርብ ጊዜ ተጠናቆ ለማኅበረሰባችን አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር እምነታችን ነው።›› ሲሉ ተናግረዋል።

ዋርዴር ከፑንትላንድ በቅርብ ርቀት የምትገኝ የጠረፍ ከተማ እንደመሆኗ እየተሰራ ያለው መንገድ ዋረዴር ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን ድንበር ድረስ ዘልቆ ለቀጠናዊ የንግድ ትስስር እንዲሁም በክልሉና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት እንፈልጋለንም ብለዋል።

ዋርዴር በፑንት ላንድ ከምትገኘው ገርአብ ወደብ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እንደምትገኝ ተናግረው፣ በዚህ አካባቢ የመንገድ መሰረተ ልማት መስፋፋቱ ወደፊት በሀገራቱ መካከል በሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ትስስር አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን ሀገራዊና ቀጠናዊ ፋይዳ ይዞ እንደሚመጣም ተናግረዋል።

በጉብኝታችን በሸበሌ ዞን ጎዴ ከተማ፣ በኮሬይ ዞን ቀበሪደሃር ከተማ፣ በጀረር ዞን ደጋሃቡር ከተማ፣ በሲቲ ዞን ሺኒሌ ከተማና በክልሉ ዋና ከተማ ጅግጂጋ ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገዶች መሰራታቸውንም ተመልክተናል። በዚህም ነዋሪዎች ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸውልናል።

ከመስክ ምልከታችን በኋላ የመንገድ መሰረተ ልማትን በተመለከተ የክልሉ ርእሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሃመድ እንዳብራሩልን፤ ክልሉ ከሰላም እጦት ባሻገር ለረዥም ጊዜ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ብዙም ስላልነበሩት ከፍተኛ የሕዝብ ሮሮ ይሰማበት ነበር።

ከለውጡ በኋላ በተገኘው ሰላም፤ የፌደራል እና የክልሉ መንግሥት ከበጀት አቅርቦት ጀምሮ በሰጡት ትኩረት በተለያዩ ሴክተሮች በርካታ የልማት ሥራዎች መሥራታቸውን ገልጸው፤ በተለይም ከመንገድ መሰረተ ልማት አንጻር ከፍተኛ ለውጥ መታየቱን ጠቅሰዋል።

ከለውጡ በፊት በአንዳንድ ክልሎች በወረዳ ደረጃ የአስፋልት መንገድ ተደራሽነት ጥሩ ደረጃ ላይ ስለመድረሱ ሲገለጽ እንደነበር አስታውሰው፣ በሶማሌ ክልል በዞን ደረጃ ሆነው አስፋልት ያልደረሰባቸው ቦታዎች እንደነበሩም አመልክተዋል። ከለውጡ ወዲህ ክልሉ በተለይም በፌደራል መንግሥት ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ተከትሎ ከሁለት ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የሚሆኑ ከ17 በላይ የአስፋልት መንገዶች መገንባታቸውን አቶ ሙስጠፌ ገልጸዋል።

በበጀት እጥረት እና በኮንትራክተሮች ድክመት ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች መጓተት የታየባቸው የመንገዶች ግንባታዎች ስለመኖራቸውም እሳቸውም ጠቅሰዋል። ከቀብሪደሃር ዋርዴር ያለው የመንገድ ፕሮጀክት የዚህ አንዱ ማሳያ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

በፕሮጀክት ደረጃ ያሉት ጥቂት መንገዶች ሙሉ ለሙሉ አልቀው አገልግሎት ሲሰጡ የንግድ እንቅስቃሴዎችንና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳድጉት አስታውቀው፣ የሕዝቡ እርካታም ከእስከ አሁኑም በላይ እንደሚሆን ጠቅሰዋል።

አቶ ሙስጠፌ እንዳሉት፤ በክልሉ አጠቃላይ ከነበረው አንድ ሺ 200 ኪሎ ሜትር የሚገመት የገጠር መንገድ ላይ ሌላ አንድ ሺ ኪሎ ሜትር በመጨመር እስከ ሁለት ሺ 200 ኪሎ ሜትር የጠጠር መንገድ ተሰርቷል። አንዳንድ ቦታ ላይ መጠናቀቅ የሚጎድላቸው ውስን መንገዶች እንዳሉም አንስተው በተያዘው በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ እየተሠራም ነው ብለዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ የክልሉን ዋና ከተማ ጅግጅጋን ጨምሮ በከተሞች አካባቢ በጣም ከፍተኛ የመንገድ መሰረተ ልማት ችግር ነበር። ከከተማ ልማት አንጻር መንገዶች ወሳኝ መሆናቸው ስለታመነበት በአጠቃላይ ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ አስፋልት ያስፈልጋቸዋል በተባሉ አራት ትላልቅ ከተሞች ማለትም በጂግጂጋ፣ በደጋሃቡር፣ በቀብሪደሃርና በጎዴ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገዶች ተሰርተዋል።

የጂግጂጋ ከተማ ከለውጡ በፊት የነበረው መንገድ ከስምንትና ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ እንደነበር እና በአሁኑ ጊዜ ወደ አርባ ኪሎ ሜትር እንደተሠራ አብራርተው፣ ጎዴ እስከ 16 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ ተሠርቶ ግምሹ ለአግልግሎት ክፍት እንደተደረገ አስታውቀዋል። በቀብሪደሃርና ደጋሃቡርም ከ5 እስከ 6 ኪሎ ሜትር በላይ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገዶች እንደተሠሩ ገልፀዋል።

በአጠቃላይ ክልሉ ካለው የቆዳ ስፋት አንጻር የተገነቡት መንገዶች በቂ ናቸው ማለት እንደማይቻል የተናገሩት ርእሰ መስተዳድሩ፣ ከነበረው ችግር አንጻር ግን በጣም ጥሩ ጅምር ሥራዎች እንደተሠሩ አስታውቀዋል። እነዚህም ሕዝብና መንግሥትን በከፍተኛ ደረጃ ያቀራረቡ እንዲሁም የክልሉን ገጽታ የቀየሩ ስለመሆናቸው አቶ ሙስጠፌ አስታውቀዋል።

# ወርቃማ የሕይወት ሕጎች

አስናቀ ፀጋዬ

በሕይወታችን ውስጥ የምንመራባቸው ሕጎች ወይም መርሆች ቢኖሩ መልካም ነው። ምክንያቱም ሕጎችና መርሆች እንድንለወጥና ቆራጥ እንድንሆን ያደርጉናል። የሚገርመው ነገር በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ያልተፃፉ ሕጎች አሉ። አንዳንዶቹ ጠቃሚ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ጎጂ ናቸው።

ያልተፃፈ ሕግ ማለት አልተደነገገም፣ የሚያስገድደን ሰው የለም ግን ሁሌ እንተገብረዋለን። ለምሳሌ በቀን ሁለቴ ወይ ሶስቴ እንድትበላ የሚያስገድድህ ሰው ወይም ሕግ የለም። ግን ታደርገዋለህ። ለምን? ስለሚጠቅምህ። በዚህ ፅሁፍ የሚቀርቡ ሕጎች አልተፃፉም። ግን ሕግ ናቸው። ሕይወታችን ላይ በጣም ይጠቅሙናል። እንደውም አንዳንዶቹ ሲገለፁ እስከዛሬ እንዴት አልሰማዋቸውም ? ያስብላሉ። እንሆ ወርቃማዎቹ የሕይወት ሕጎቹ....

### 1ኛ. ራስህን ስማወቅ ጊዜ ውሰድ

ምንድን ነው የሚያስደስትህ? በሕይወትህ ምንድን ነው የምትፈልገው? ላንተ ትርጉም የሚሰጥህ ነገር ምንድን ነው? ምን መማር፣ ምን መስራት፣ ምን አይነት ገቢ እንዲኖርህ፣ ምን አይነት ፍቅር ሕይወት፣ ምን አይነት ትዳር እንዲኖርህ ነው የምትፈልገው? ጊዜ ውሰድና አስብ። አንድ አንድ ሰው የሆነ ቀን ተነስቶ ፀሎት ያደርስና «አንተ ለካ መጸለይ ሰላም ይሰጣል» ይልሃል። ከዛ ግን አይደግመውም። ሕይወቱ ላይ አይተገብረውም። አንዳንድ ሰው የሆነ ቀን ደስ ሲለው ስፖርት ይሰራና «አንተ ስፖርት መስራት ለካ ቀለል ያለ ስሜት ይፈጥራል» ይልሃል። አይደግመውም። በዘፈቀደ የምንኖርበት ጊዜ ማብቃት አለበት። ማቀድ አለብን። ምን እንደምንፈልግ ማሰብና ማወቅ አለብን። ወዴት እንደሚሄድ የማያውቅ ሰው ሁሉም መንገድ የሚያደርሰው ይመስለዋል። ራስህን ለማወቅ ግዜ ውሰድ፤ ወሳኝ ሕግ ነው።

### 2ኛ.ያንተ ስራ መዝራት ነው

ያንተ ስራ መዝራት ነው፤ የሚያበቅለው ደግሞ ፈጣሪህ ነው። ያንተ ስራ መልካም መሆን ነው። መልካም ሰው ወደ ሕይወትህ የሚያመጣው ፈጣሪ ነው። መልካም ጓደኛ፣ መልካም ፍቅረኛ፣ መልካም የትዳር አጋር የሚሰጥህ ፈጣሪ ነው። አንተ ብቻ መልካም ሁን። ያንተ ስራ የሚጠበቅብህን ሁሉ ማድረግ ነው። ውጤቱን የሚሰጥህ ፈጣሪህ ነው። ያንተ ስራ መሞከር ነው። የሚያሳካው ፈጣሪ ነው። አየህ! ገበሬ ከዘራ፣ ከኮተኮተና ውሃ ካጠጣ የዘራው እንደሚበቅል እርግጠኛ ነው። አንተም የሚጠበቅብህን ካደረክ ፈጣሪ ሌላውን ያደርጋል። በከንቱ አትጨነቅ። አንተ መቀየር የማትችላቸው ነገሮች ላይ ትኩረት አታድርግ። አንተ የምትቀይራቸው ነገሮች ላይ አተኩር። ያንተ ስራ መዝራት ብቻ ነው።

### 3ኛ. የመጣህበትን አስብ

ብዙ ሰው የሆነ ነገር ይጀምርና የሚያቆመው የቀረውን አስቦ «ውይ! በጣም ብዙ ይቀረኛል» ብሎ ተስፋ ቆርጦ ነው። አንተ ግን የቀረህን ሳይሆን የመጣህበትንና የጨረስከውን አስብ። ብዙ ነገር ጨርሻለሁ፣ ብዙ ነገር አሚልቻለሁ፣ ትንሽ ነው የቀረኝ ማለት አለብህ። የጎደለህን አትይ። ጉድለትህን የምታይ ከሆነ ተስፋ ትቆርጣለህ። አንድ ሰው ወርቅ ለማግኘት ቆፍሮ ቆፍሮ መጨረሻ ላይ አንድ እርምጃ ሲቀረው ተስፋ ቆርጦ ቦታውን ሸጦ ወጣ። ተረኛው ፈላጊ መጥቶ በአንድ እርምጃ ቁፋሮ ወርቁን አገኘ። የመጀመሪያው ሰው ምን ያህል ዘመን እንደሚቆጨው አስቡት። አንተም ለፍተሃል፣ ብዙ ቦታ ደርሰሃል። ታዲያ ለምንድን ነው የቀረህን ነገር አስበህ ተስፋ የምትቆርጠው ? የመጣህበትን አስብ ያኔ ተስፋ ይኖርሃል።

### 4ኛ. እድል የሚመጣው ስሚዘጋጅ ነው

ለምሳሌ አንድ ሰው ሎተሪ እንዲደርሰው ምን ያድርግ ብትባሉ መጀመሪያ ሎተሪ ይቁረጥ ትላላችሁ። አንድ ሎተሪ መቁረጥ ግን በቂ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ስለሚቆርጡ ያ ሰው ላይደርሰው ይችላል። ስለዚህ እድሉን ለማስፋት በርካታ ሎተሪ መቁረጥ ይጠበቅበታል። በጣም ብዙ ሎተሪ ከቆረጠ ምን አልባት ሊደርሰው ይችላል። አያችሁ በሕይወትም በጣም ጠንክሮ የሚሰራ የሚሰራ ሰው፣ ጠንክሮ ገንዘቡን የሚያስቀምጥ ሰው፣ ጠንክሮ እውቀት የሚሰበስብ ሰው እድሉን እያሰፋ ነው። ብዙ ሎተሪ እንደሚቆርጥ ሰው ነው። ምክንያቱም የሆኑ እድሎች ሲመጡ እሱ በገንዘብም፣ በእውቀትም በብዙ ነገር ተዘጋጅቷል። ይጠቀምበታል።

ካልተዘጋጀህ ግን እድሉ ቢመጣ ራሱ ታባክነዋለህ። ይቆጭሃል። «ወይኔ! ገንዘቡን ባስቀምጥ ኖሮ አሁን ይህች ቢዝነስ ታዋጣኝ ነበር» ትላለህ። አሁን አስቀምጥ፤ አሁን ተዘጋጅ! መዘጋጀት በራሱ በራስ መተማመን ይሰጥሃል። ልበ ሙሉነት ይሰጥሃል። ስትዘጋጅ እኔ ነገን አልፈራም ብዙ ነገር ላይ ሂይወቴ ላይ እየበረታሁ ነው፣ እየተለወጥኩ ነው፣ ነገ አያስፈራኝም ትላለህ። ወሳኝ ሕግ ነው እድል የሚመጣው ለሚዘጋጅ ነው።

### 5ኛ. ልታደርገው የምታስበውን ነገር ሁሉ አትናገር

የሚገርም ሕግ ነው። ምክንያቱም ራዕይ የምትኖረው፤ የምታደርገው ነገር እንጂ የምትናገረው አይደለም። ለሰዎች በተናገርከውና በዘራኸው ቁጥር አቅም ታጣላህ። ያወራኸውን ወሬ ብዙ ግዜ አታደርገውም። ባትናገር ጥሩ ነው። በተለይ የሚጠቅምህ ካልሆነ፣ ያ ሰው ሕልምህ ላይ የሚረዳህ ካልሆነ ለምን ትነግረዋለህ? ሰምቶ ዝም ለሚልህ ወይ ደግሞ አትችልም እንደው ቢቀርብህ ለሚልህ ሰው ለምን ትነግረዋለህ? አትንገረው። አንተም ጉልበት ታጣለህ። አንዳንዴ በውስጥ የታመቀና ልውጣ ልውጣ የሚል ሀሳብ አለ። ግን ለራስህ ንገረው። ይህንን ነገር በንግግር አይደለም በተግባር ነው የምገልጠው በል። አንዳንድ ግዜ ህልሞች ወይም ራዕዮች በተግባር የምንተገብራቸው ናቸው። ስራህ ራሱ ጮሆ ይናገር። አንተ መናገር አይጠበቅብህም። የምታስበውን ሁሉ ለሰዎች አትናገር። በጣም ወሳኝ ሕግ ነው።

### 6ኛ. ነፃ ምሳ የለም

ንጉሱ ጠቢባንን ሰብስቦ ለሕዝቤ የሚሆን ጥሩ መልዕክት ፅፋችሁ አምጡ አላቸው። መፅሃፍ አመጡለት። «መፅሃፍማ ረጅም ነው አያነቡትም» አላቸው። አሳጥረው በአስር ገፅ አመጡለት «ይህንን ሁሉማ ማንም የሚያነብ የለም» አላቸው። አሁንም አሳጥረው በአንድ ገፅ አመጡለት። «ይህም በዛ» አላቸው። «በቃ! አንድ አረፍተ ነገር አድርጉት» አላቸው። ጠቢባኑ ተማክረው አንድ አረፍተ ነገር ይዘው መጡ። «ነፃ ምሳ የለም!» የሚል።

ምን መሰለህ አንተ ካለፋህና ካልጣርክ በነፃ የምታገኘው ነገር የለም። በተለይ አጥብቀህ የምትፈልገው ነገር ትልቅ ከሆነ ትልቅ ልፋት ካንተ ይጠበቃል። አንድ ፎቅ ትልቅ እንደሆነ የምታውቀው ፎቁ ሲያልቅ አይደለም። ሲቆፈር ነው፣ መሰረቱ ነው ትልቅ የሚያስብለው። አንተም መዘጋጀት አለብህ። ትልቅ ነገር ከፈለክ ትልቅ ልፋት እንዳለብህ አስብ። በነፃ የምታገኘው ነገር የለም። የሆነ ሰው ከመሬት ተነስቶ አንተ ጎበዝ ነህ ብሎ የመቶ ሺ ብር ደሞዝተኛ አያደርግህም።

የመቶ ሺ ብር ደሞዝተኛ ለመሆን አንተ መቀየር አለብህ። መልፋት አለብህ። አየህ! ስበት የሚሰራው አንተ ከተለወጥክ ነው። አንተ ስትለወጥ የምትፈልጋቸው ነገሮች ወዳንተ ይሳባሉ። ወዳንተ ይመጣሉ። አንተ ትልቅ ነገር የምትፈልግ ከሆነ ትልቅ ነገር የሚገባው ሰው ሁን። ያኔ ሁሉም ይመጣል። ነፃ ምሳ የለም ወዳጄ!

### 7ኛ. ፍርሃትህን መጋፈጥ ተስማመድ

በጣም አጥብቀህ የምትፈልጋቸው ነገሮች ያሉት ከፍርሃትህ ጀርባ ነው። አየህ! ለውጥ ከፈለክና ፍርሃት ከያዘህ በቃ ትልቅ ነገር ሊያመልጥህ ነው። ስለዚህ መለወጥና ራስህን ማሳመን አለብህ። ጥልቅ መሻት ያለው ሰው በፍፁም ፍርሃቱን ይጋፈጣል። የማይፈራና ጥርጣሬ የማይሰማው የለም። ሁሉም ሰው ትንሽዬም ቢሆን ፍርሃት አለበት። ፍርሃትህን የምታሸንፈው ግን በፍላጎትህ፣ በጥረትህና በጥልቅ መሻትህ ነው። ምን ያህል ትፈልገዋለህ ያንን ነገር? ያኔ ዋጋ ትከፍልለታልህ። ያንን ነገር ባታደርግ የምታጣውንና የሚጎድልብህን አስብ። ያንን ነገር ደግሞ ታገኝ የምታደርገውን አስብ። ሽልማቱን፣ ውጤቱንና እርካታውን አስበው። ያኔ አትፈራም። ትደፍራለህ። ታደርገዋለህ። ለአይምሮህ ደግሞ ደፋር እንደሆንክ ንገረው። አይምሮህን ከነገርከው፣ አንተ ጥልቅ ፍላጎት ካለህ የምትፈራው ነገር አይኖርም። ስለዚህ ፍርሃትህን መጋፈጥ አለብህ።

> «በሕይወታችን ውስጥ የምንመራባቸው ሕጎች ወይም መርሆች ቢኖሩ መልካም ነው። ምክንያቱም ሕጎችና መርሆች እንድንለወጥና ቆራጥ እንድንሆን ያደርጉናል። የሚገርመው ነገር በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ያልተፃፉ ሕጎች አሉ። አንዳንዶቹ ጠቃሚ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ጎጂ ናቸው።»

### 8ኛ.ከትናንት ዛሬ መሻል አለብህ

እየኖርክ ነው የምትባለው ስለምትተነፍስ ብቻ አይደለም። ስታድግም ነው። በየቀኑ በትናንሹ ማደግ ጫፍ ላይ ያወጣሃል። ጀምስ ክሊር የተባለ ታዋቂ ራስን የማበልፀግ ፀሃፊ «በየቀኑ አንድ ፐርሰንት ብታድግ በዓመቱ መጨረሻ ላይ 37 እጥፍ ትለወጣለህ» ይላል። ይህ ማለት በየቀኑ አንድ ፐርሰንት ብታነብ ወይ አዲስ ነገር ብትጨምር 37 እጥፍ እውቀት ይኖርሃል። 37 እጥፍ ገቢህ ሊያድግ ይችላል። በሁሉም አቅጣጫ በ37 እጥፍ ታድጋለህ። ትናንሽ ለውጦች ሕይወት ይቀይራሉ። በየቀኑ ማደግ አለብህ። አንድ መስመር፣ አንድ ገፅም ቢሆን ማንበብ አለብህ። ከትናንትህ ጥፋት ዛሬ መማር አለብህ። ዛሬ ምን አበላሸሁ፣ ምን ላስተካክል ማለት አለብህ። ከሰዎች ጥፋት መማር አለብህ። በየቀኑ አዳዲስና ትናንሽ ለውጦች፣ እድገቶች፣ አውቀቶች ያስፈልጉሃል። ከትላንት ዛሬን መሻል አለብህ ወዳጄ!

### 9ኛ.ምንም ነገር ስትሰራ መቶ ከመቶ ሁን

ምንም ነገር በሙሉ ልብህ ማድረግ አለብህ። በግማሽ ልብ የምትሰራቸው ነገሮች ግማሽ ውጤት ነው የሚሰጡህ። የተሟላ ነገር አታገኝም። በተለይ የምታምንበት፣የምትወደው ነገር ሲሆን በሙሉ ሀሳብህ፣ በሙሉ ትኩረትህ መስራት አለብህ። ያ ነው ከሰው በላይ የሚያደርግህ። ውጤት የሚሰጥህ። ስለዚህ ትኩረት በጣም ወሳኝ ነው። ሀሳብህን ሰብስበህ ስትሰራ ጉልበትህ ወደ አንድ አቅጣጫ ይሰበሰባል። ጥሩ ለውጥ ታመጣለህ። ተጠቀምበት! ምንም ነገር ስትሰራ መቶ በመቶ ሁን።

### 10ኛ.ሁሉንም ስማስደስት አትሞክር

መለወጥ ከፈለክ ምርጡ ግዜ አሁን ነው። አየህ! አሁን መለወጥ ካሉብህ ነገሮች ውስጥ አንዱ ሁሉንም ሰው ማስደሰት አለብኝ የሚለውን ሕግ መሰረዝ ነው። ራስህን አስደስት። ለምትወዳቸውና ለምታከብራቸው ሰዎች ቅድሚያ ስጥ። ሁሉንም ሰው አስደስታለሁ ብለህ ግን ብኩን ሰው መሆን የለብህም። አየህ! ካረጀህና እድሜህ ካለፈ በኋላ የሚቆጭህ ካደረከው ይልቅ ያላደረከው ነው። «ምን አለ ይህን ባደርገው ኖሮ! ምን አለ እንዲህ ቢሆን ኖሮ!» ትላለህ። ስለዚህ ሁሉንም ለማስደሰት የምታርገውን ጥረት ከአሁኑ አቁም።

### 11ኛ.ዝም ብለህ ቀጥል

አንዳንዴ ፍላጎት ታጣለህ። ማቆም ትፈልጋለህ። ትሰለቻለህ። ሕይወቱ፣ ትምህርቱ፣ ስራው ትርጉም ያጣብሃል። በቃኝ ትላለህ። ግን ዝም ብለህ ቀጥል። ምን መሰለህ? የምትፈልገውን ለማግኘት አንዳንዴ የማትፈልገውን መስራት ሊኖርብህ ይችላል። ሕይወት እንደዛ ነው። አየህ አንዳንዴ ዝምብለህ መቀጠል ትርጉም ይሰጥሃል። ማቆም ግዚያዊ ስሜት ነው። አሁን ብታቆም ትልቅ ነገር ሊያሳጣህ ይችላል። አልፎ ቆይቶ ነው የሚቆጭህ። ስለዚህ ዝም ብለህ ቀጥል። ጉሙ እስከሚታይህ ሂድ። አንዳንዴ እኮ ጉሙ የሚሸፍንህ፣ የሚጋርድህና ድምበር የሚሆንብህ ይመስልሃል እንጂ አያቆምህም። እስከሚታይህ ሂድ። ማቆም የለብህም። ዝምብለህ ቀጥል።

### 12ኛ.ከምታገኘው ላይ ስፈጣሪህ ስጥ

ክርስቲያን ከሆንክ መባ ወይም አስራት መስጠት አለብህ። ሙስሊም ከሆንክ ደግሞ ዘካ ማውጣት አለብህ። ምን መሰለህ? ለመንግስት ግብር ትከፍላለህ። ደህንነትህን ስለሚያስጠብቅልህ። በሰላም ወጥህ ስለምትገባ። ከሌባ ስለሚጠብቅህ። ወይ ደግሞ መሰረተ ልማት ስለሚሰራልህ። ለመንግስት አስራምስትም ይሁን ሀያና ሰላሳ በመቶ ግብር ትከፍላለህ። አየህ ፈጣሪህ ደግሞ ጤና ሰጥቶሃል። ወጥተህ እንድትገባ፣ ሰርተህ እንድታገኝ ሁሉን ነገር ሰጥቶሃል። እውቀቱን አሁን ያለህን ማንነት ሰጥቶሃል። ስለዚህ መክፈል አለብህ።

### 13ኛ.ከማይመስሉህ ሰዎች ራቅ

አንዳንዴ ማደግህን የምታውቀው በጣም የቅርቤ ናቸው ከምትላቸው ጓደኞችህ መራቅ ስትጀምር ነው። ለምን መሰለህ? እነሱ ካልተለወጡና ካላደጉ አንተ ቆመህ መቅረት የለብህም። ከሚሮጡት ጋር ነው መሮጥ ያለብህ። አንድ አይነት ቀለም ያላቸው ወፎች ናቸው አብረው የሚበሩት። አየህ! ጓደኞችህን መጥላትና መተው አይደለም ያለብህ። ግን እነርሱ ካልተለወጡና ካላደጉ አንተ ቆመህ መቅረትህ ነው። ማደግ አለብህ። ለትንሽ ግዜም ቢሆን ስትርቃቸው ለእነርሱም ቢሆን ትተርፋለህ። አየህ! ውሎህ በጣም ወሳኝ ነው። አሁን አጠገብህ ያሉትን ሰዎች ሕይወትህ ላይ እነርሱን መሆን ትፈልጋለህ? እንደነርሱ ገቢ እንዲኖርህ፣ እንደነርሱ ጥሩ ትዳር እንዲኖርህ ትፈልጋለህ? እንደነርሱ መሆን ከፈለክ ከእነርሱ ራቅ። ከሚመስሉህ ጋር ዋል። የማይመስሉህን ሰዎች ራቃቸው። ሕይወትህን ባዶ ያደርጉታል። ሕይወትህን የሚቀይረው ውሎህ ነው!

## በድጋሚ የወጣ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ

በአፈጻጸም ከሳሽ አቶ በርገነ ሻንካ እና በአፈጻጸም ተከሳሽ አቶ ወንድሙ ቶሩ መካከል ባለው የአፈጻጸም ክስ መነሻነት ሆኖ በሶዶ ከተማ በዋዱ ቀበሌ ቀጠና 02 ሰፈር 06 የይዞታ ምስክር ወረቀት ሽ/908/98 ፣ስፋቱ 200 ካ/ሜትር በሆነው እና በአፈጻጸም ተከሳሽ በአቶ ወንድሙ ቶሩ ስም ተመዝግቦ በሚገኝ በሰሜን የቦታ ቁጥር 205፣በደቡብ የቦታ ቁጥር 207፣በምስራቅ የቦታ ቁጥር 208፣በምዕራብ መንገድ በሚያዋስኑበት ይዞታ ላይ ያለው መነሻ ዋጋ 1,345,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አምስት ሺህ) ብር የሆነው መኖሪያ ቤት በድጋሚ በጨረታ የሚሸጠው በቀን 8/11/2016 ዓ.ም ከረፋዱ 5፡30 - 6:30 ሰዓት ድረስ ሲሆን ቤቱን ለመግዛት የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች የቤቱ መነሻ ዋጋ 5% የባንክ CPO እያስያዘ ቀርቦ እንዲጫረት የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0070099756 የሚታወቀው ኤክስፐረስ ኮሌጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ሚኒስቴር ሰሜን ምዕራብ አነስተኛ ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት እጅ በእጅ /ቫት ያልተጠቀምኩባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር 1851 እስከ 1900 እና 1901 እስከ 1950 ያለው ምንም አገልግሎት ላይ ያልዋለ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑን የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገቡበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ሚኒስቴር ሰሜን ምዕራብ አነስተኛ ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ኤክስፐረስ ኮሌጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 043 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0000015882 የሚታወቀው ሳዱላ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ቦሌ ክፍለ ከተማ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት እጅ በእጅ ቫት ያልተጠቀምኩባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር 1250 እስከ 1750 ያለው ምንም አገልግሎት ላይ ያልዋለ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑን የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገቡበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ቦሌ ክፍለ ከተማ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሳዱላ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 01 በቤት ቁጥር 451 በ 0001490458 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለሚታወቀው ዳንኤል ታደሰ መሳሪያዎችን መገልገያዎችን ሥራ ንግድ ድርጅት በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ከምጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር ከ401- 650 የእጅ በእጅ ደረሰኝ ያልሰተራበት ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸሙ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ለአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርጉልን አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዳንኤል ታደሰ መሳሪያዎችን መገልገያዎችን ሥራ ንግድ ድርጅት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የአዳማ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ በ2017 የበጀት ዓመት የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ለሁለተኛ ጊዜ ፣ የላም ወተት ለአንደኛ ጊዜ ለህሙማን እና ተማሪዎች የሚውል በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ነጋዴዎች መወዳደር ትችላላችሁ።

- የ2016/17 ዓ.ም የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ በዘርፉ ያላችሁ እንዲሁም የዘመኑን የመንግስት ግብር የከፈላችሁ።
- ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
- በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ መመዝገባችሁን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ የምትችሉ ።
- ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዕቃ ግዥ መ/ቤት ድረስ በራሱ ወጪ ማቅረብ የሚችል
- ተጫራቾች የሚያቀርቡትን የጨረታ ሰነድ ኮፒና ኦሪጅናል ለየብቻ በተለያየ ፖስታ ማሸግ አለባቸው።
- ስርዝ ድልዝ ያለው፣ የማይታይ የጨረታ ሰነድ ወይም የዋጋ ዝርዝር ተቀባይት የለውም፡፡
- ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ የውል ማስከበሪያ የአሸነፉበትን ዋጋ 10% ማስያዝ የሚችል።
- ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከኮሌጁ ግዥና ፋይናንስ የስራ ሂደት ክፍል ዘወትር በስራ ሰዓት የማይመለስ 100 /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መውሰድ አለባቸው ።
- ሰነዱ የሚሸጠው ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 25/10/2016 ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ብቻ ነው።
- ጨረታው የሚከፈተው በ25/10/2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡30 ተጫራቾች/ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
- ተጫራቾች የሚሞሉት ዋጋ በመስሪያ ቤቱ ሰነድ ብቻ ላይ መሆን አለበት።
- የጨረታው ማስከበሪያ ለምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች 10,000 (አስር ሺህ ) ብር እና ለላም ወተት 6000 (ሰድስት ሺ) ብር በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ በ"CBE, CBO, እና Sinqe" ባንክ ብቻ ማስያዝ የሚችል መሆን አለበት፡

*መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0228123956 ደውለው መረዳት ይችላሉ፡፡

**የአዳማ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ**

## የምግብ ስንዴ ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ

ኤረር የገ/ህ/ሥ/ዩኒየን የምግብ እህል ስንዴ 7700 ኩ/ል በጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ በመስኩ የተሰማሩ የምግብ ኢንደስትሪዎች ወይም ሕጋዊ ነጋዴዎች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከቀኑ 4፡00 ሰዓት ድረስ የጨረታውን ሰነድ ከጨረታው ዝርዝር መመሪያ ጋር የማይመለስ ብር 100/ አንድ መቶ ብር/ በኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000000769553 ስም ኤረር የገ/ህ/ሥ/ዩኒየን በመክፈል ሰነዱን ከኤረር የግ/ህ/ሥ/ዩኒየን ቢሮ ቁጥር 7/ሰባት/ በመግዛት በጨረታው ሰነድ ላይ የምትገዙበትን ዋጋ በመግለጽ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በመሙላት ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ ቀናት እስከ ቀኑ 4፡00 ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀ ጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው በዚሁ ቀን ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከቀኑ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ ይህ ዕለት በዓል ቢሆን ወይም የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡

- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 5% በሲፒኦ (CPO) ብቻ ማስያዝ አለባቸው።
- የእህሉን ናሙና ቢሮፍቱ በሚገኘው መጋዘናችን ቀርበው ማየት ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች የዘመኑን ግብር የከፈሉበትንና የታደሰ ንግድ ፍቃድ፤ ማህተም በመርገጥ፤ ስምና አድራሻ በመግለጽ ማቅረብ አለባቸው፡፡
- የFinancial and Technical, orginal and copy በሰም በታሸገ ፖስታ ለየብቻ መቅረብ አለበት፡፡
- ድርጅቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ፡- ቢሾፍቱ 0114333758/0912231187/0910756336

**ኤረር የገ/ህ/ሥ/ዩኒየን**